# አዲስ ዘመን

እኘድ

ሐሙስ

84ኛ ዓመት ቁጥር 037 ጥቅምት 7 ቀን 2017 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!





ፎቶ ዳኜ አበራ

## "ኢትዮጵያውያን የኢትዮ ቴሌኮም ድርሻን የመግዛት ዕድሉን ሊጠቀሙበት ይገባል"

**- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)**

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያውያን እጃቸው ላይ የቀረበውን የኢትዮ ቴሌኮም ድርሻን የመግዛት ዕድሉን ሊጠቀሙበት ይገባል ሲሉ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ገለጹ፡፡ በቀጣይ በሆቴል ዘርፍ የአክሲዮን ድርሻ ሽያጭ እንደሚኖርም ጠቁመዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የኢትዮ ቴሌኮም ለኢትዮጵያውያን የ10 በመቶ አክሲዮን ድርሻ ሽያጭ ትናንት ይፋ ሲያደርጉ እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያውያን የኢትዮ ቴሌኮም ድርሻን በሽሚያ ሊገዙ ይገባል። ይህን ዕድልም በአግባቡ መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

ኢትዮ ቴሌኮም ትርፋማ በመሆኑ ስቶክ ማርኬትን ለማለማመድ 10 በመቶው ለሽያጭ ቀርቧል ያሉት ጠቅላይ


**"ኢትዮጵያውያን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል**




ፕሮፌሰር መኮንን አያና

### የማሕቀፍ ስምምነቱ ወደ ተግባር መግባቱ ኢትዮጵያ ላይ የሚቀርቡ ምክንያት አልባ ክሶችን ያስቀራል


ገጽ 4


### የኢትዮጵያ አየር ኃይል የተደራጀ አቅም ለአፍሪካ ሀገሮችም ምሳሌ የሚሆን ነው


ገጽ 4


## አሳሳቢው ሕገወጥ የሰዎች ዝውውርና መፍትሔው

**ፋንታነሽ ክንዴ**

ዜና ትንታኔ

ሥርቶ መለወጥን ዓላማ ያደረጉ ኢትዮጵያውያን በተለያየ መልኩ ከሀገር ይወጣሉ፡፡ ከፊሎቹ ሕጋዊ መንገድ ተከትለው መዳረሻቸውም ታውቆ ወደ ተለያዩ ሀገራት ገብተው ወደ ሥራ ይሠማራሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ በሕገወጥ ደላሎችና መልማዮች አማላይ ቃላት ተታለው አስቸጋሪ ሁኔታዎችንና ሞትን ተጋፍጠው ባሕር አቋርጠው ለስደት ይዳረጋሉ። ለተለያዩ አካላዊና ሥነልቦናዊ ጉዳቶች የሚዳረጉትም ቁጥራቸው ቀላል አይደለም።

ዜጎች በሀገር ሥርቶ መለወጥን ምርጫቸው እንዲያደርጉ ካልሆነም ሕጋዊ መስመርን ብቻ ተከትለው ከሀገር መውጣት እንዳለባቸው ተደጋግሞ ሲነገር ይደመጣል፡፡ መንግሥት በበኩሉ የሀገር ውስጥ የሥራ ዕድል ፈጠራን ከማስፋት ጎን ለጎን የውጭ ሀገር የሥራ ስምሪትን ለማስፋት እየሠራ ይገኛል፡፡

በ2016 በጀት ዓመት ከ345 ሺህ ዜጎች በላይ አስፈላጊውን መስፈርት አሟልተው ወደ ተለያዩ ሀገራት አቅንተዋል። በተያዘው በጀት ዓመትም 700 ሺህ ዜጎችን



ወደ ተለያዩ ሀገራት ለማሰማራት ውጥን ተይዟል።

ለመሆኑ መደበኛ ያልሆነ ፍልሰት በዜጎች ላይ እያደረሰ ያለው ጉዳት ምንድነው? ሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውርን ለመከላከል እየተሠሩ ያሉ ሥራዎችስ ምን ይመስላሉ? በሚሉ ጉዳዮች ላይ የዘርፉ ባለሙያዎች


**አሳሳቢው ሕገወጥ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል**

















ወይዘሮ ያስሚን ወሀብረቢ

# የኢትዮጵያ ምርት ገበያ የግብይትና የክፍያ ሥርዓቱን አዘምኗል

**መዓዛ ማሞ**

አዲስ አበባ፡ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ የግብይትና የክፍያ ሥርዓቱ መዘመኑን የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ገለጸ።

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትር ዴኤታ ወይዘሮ ያስሚን ወሀብረቢ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ አካዳሚ በአምስተኛ ዙር በአራት ዘርፎች ያሠለጠናቸውን 85 ሠልጣኞች ከትናንት በስቲያ ሲያስመርቅ እንደተናገሩት፤ ተቋሙ የግብይት እና የክፍያ ሥርዓቱን በማዘመን ውጤታማ ሥራ እየሠራ ነው።

ተቋሙ እያከናወነ ከሚገኘው ሥራ በተጨማሪ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ አካዳሚን በማቋቋም በዘርፉ እውቀት ያለው ኃይል እያፈራ መሆኑን ገልጸው፤ አካዳሚው የተጣለበትን ኃላፊነት በመወጣት ለ5ኛ ጊዜ እያስመረቀ መሆኑን ተናግረዋል።

እንደ ሚኒስትር ዴኤታዋ ገለጻ ተመራቂዎች የኢትዮጵያን የወጪ ንግድ ከማሳካት አንጻር ትልቅ ኃላፊነት ይጠብቃቸዋል።

ከገበያው ተጠቃሚ ለመሆን እና የተሻለ ገቢ ለማግኘት ጥራትን ማስጠበቅ የግድ መሆኑን ተናግረው፤ ተመራቂዎች ጥራትን በማስጠበቅ ሚናችሁ አይተኬ ነው ብለዋል።

አካዳሚው በጥራት ቁጥጥር እውቀት ያለው የሰው ኃይል ለማፍራት ታስቦ የተቋቋመ መሆኑን ገልጸው፤ በቀጣይም በርካታ የጥራት ቁጥጥር ባለሙያዎችን እንደሚያፈራ አመላክተዋል።

የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ወንድማገኝ ነገራ በበኩላቸው እንደተናገሩት በኢትዮጵያ ምርት እና ምርታማነት እያደገ ስለመጣ በየጊዜው አዳዲስ ምርቶች የግብይት ሥርዓቱን ይቀላቀላሉ።

እንደ አገር በግብይት ሥርዓቱ ጥራት ላይ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራ መሆኑን ጠቁመው፤ በአካዳሚው እየተሰጠ ያለው ሥልጠና ስለጥራት ያለውን ግንዛቤ የሚያሳድግ መሆኑን ገልጸዋል።

ስለጥራት በሚገባ የተረዱ ባለሙያዎችን ማፍራት ተወዳዳሪነትን እና ገቢን እንደሚያሳድግም ጠቁመው፤ ስለጥራት ማወቅ ገቢን እና ተወዳዳሪነትን እንደሚያሳድግ የሚያሳደግ ስለሆነ የተሰጠው ሥልጠና ስለ ጥራት ያለውን ፅንሰ ሀሳብ የሚያጎለበት መሆኑን አመልክተዋል።

የኢትዮጵያ ምርት ገበያ በ16 ዓመታት ያካበተውን ከፍተኛ ልምድ ሌሎች እንዲቀስሙት በማሰብ አካዳሚውን በ2015 ዓመተ ምሕረት ማቋቋሙን ተናግረው፤ ከሀገር ውስጥ በተጨማሪ በአንጎላም ሥልጠና መሥጠቱን አመላክተዋል።

ሠልጣኞቹ በቡና ጥራት ቁጥጥርና ቅምሻ፣ በጥራጥሬና ቅባት ጥራት ቁጥጥር፣ በኤሌክትሮኒክስ ግብይት እና በኤሌክትሮኒክስ የጨረታ ሥርዓት ከአንድ ሳምንት እስከ 3 ወራት ሥልጠና የተከታተሉ መሆናቸው ታውቋል። ሥልጠናው በቀን፣ በማታ እና በቅዳሜና እሁድ ፕሮግራሞች መሥጠቱም ተገልጿል።

# በከፍተኛ ውጤት የተገለጠ ጥረት

**ዳግማዊት አበበ**



ተማሪ ሲፈኔ ተክሉ

ሲፈኔ ተክሉ ትባላለች፡፡ በ2016 የትምህርት ዘመን የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ብሔራዊ ፈተና በተፈጥሮ ሳይንስ 575 ያመጣች ናት፡፡ ይህም የሀገሪቱ ከፍተኛ ውጤት ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ ተማሪ ሲፈኔ በኦግዚሊየም ካቶሊክ ትምህርት ቤት ተማሪ የነበረች ሲሆን ጊዜን መሠረት ያደረገ እቅድ በማውጣት ረዘም ላለ ጊዜ ማንበቤ ለዚህ ውጤት አብቅቶኛል ስትል ትናገራለች፡፡

ሲፈን፤ ብዙውን ጊዜ ትምህርት ላይ ትኩረት ሰጥቶ መቆየት፣ በቡድን ማጥናት በተለይም ደግሞ ፈተና ላይ የሚቀርቡ ሁሉም የትምህርት ዓይነቶችና ምዕራፎች ብዛት በመለየትና ጊዜን በአግባቡ መጠቀም ለዚህ ውጤት መምጣት ምክንያት ሆኗል ትላለች ፡፡

ያመጣሁት ውጤት ከግል ጥረቴ በተጨማሪ የቤተሰብና መምህራኖች ድጋፍ ትልቅ አስተዋፅዖ ነበረው ብላለች፡፡

በዩኒቨርሲቲ ቆይታዋ አፕላይድ ኒውትሬሽን በማጥናት የሥርዓተ ምግብ ባለሙያ መሆን እንደምትፈልግ ገልጻ፤ አሁን ላይ በዩቲዩብና በተለያዩ ሌሎች ፕሮጀክቶች ተማሪዎችን ለማገዝ በማስተማር ላይ እንዳለች ታስረዳለች።

ፈተና የሚወጣበት ምዕራፍ ስለማይታወቅ በተቻለ መጠን ሁሉንም ምዕራፎች ለመሸፈን ተማሪዎች ጥረት ማድረግ ይኖርባቸዋል የምትለው ተማሪ ሲፈኔ፤ ለዚህም ቀጣይ ተፈታኞች ጊዜያቸውን በማጣጣም በእቅድ ማጥናት ጥሩ ውጤት እንዲያመጡ ይረዳቸዋል ስትል መክራለች፡፡

ተማሪ ፍሪና ሠላምም የኢትዮ ፓረንት ትምህርት ቤት ተማሪ ስትሆን ያመጣችው ውጤት 538 ነው ይህም በማኅበራዊ ሳይንስ ከፍተኛ ውጤት ያስገኘች አስብሏታል።

ያገኘሁት ከፍተኛ ውጤት የጥረቴ ፍሬ ነው የምትለው ተማሪዋ እስከ መጨረሻው የፈተና ሰዓት ድረስ ከእኔ የሚጠበቀውን አድርጌአለሁ ስትል ያለፈውን ጊዜ ታስታውሳለች፡፡

በመምህራን በኩል የነበረው ድጋፍ ከፍተኛ መሆኑ ይህን ውጤት እንዳመጣ ረድቶኛል፡፡ በተለይም መምህራን ዓመቱን ሙሉ ለሀገር አቀፍ ፈተናው እንድንዘጋጅ የተለያዩ ጥረቶችን ሲያደርጉ ቆይተዋል ብላለች፡፡

በቀጣይ በዩኒቨርሲቲ ቆይታዋ ምን መማር እንዳሰበች ያልወሰነችው ተማሪዋ ሕዝብን የሚጠቅም ሀገርን የሚያኮራ እንዲሁም እራሴን የሚያስደስት ቦታ ላይ እንደምሠራ ቃል እገባለሁ ስትልም ተናግራለች፡፡

የቀጣይ ተፈታኞች ጥናቱ እንዲሁም ፈተናው ቀላል እንደማይሆን አሳስባ ከእነሱ የሚጠበቀውን ሁሉ ማድረግ እንዳለባቸውም ምክረ ሃሳቧን አስቀምጣለች፡፡

ትምህርትን በአግባቡ ከማጥናት ባሻገርም በፈተና ሰዓትም ምንም አይነት ፍራቻም ሆነ መወዛገብ ሳይኖር በተረጋጋ መንፈስ ወደ ፈተና ቢገቡ እንደኔ ጥሩ ውጤት ማምጣት ይችላሉ ብላለች፡፡

ተማሪዎቻቸውን ሙሉ በሙሉ ካሳለፉ የአዲስ አበባ ከተማ ትምህርት ቤቶች አንዱ የሆነው የየኔታ አካዳሚ ጄኔራል ማናጀር ወይዘሮ ጥሩወርቅ አየለ፤ ትምህርት ቤቱ በ2015 እንዲሁም በ2016 የትምህርት ዘመን 12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ተማሪዎችን ሙሉ በሙሉ ማሳለፍ ችሏል ይላሉ፡፡

የኔታ አካዳሚ ተማሪዎች ላይ ከስር የሚሠራ በመሆኑ ይህ ውጤት ሊገኝ ችሏል ያሉት ወይዘሮ ጥሩወርቅ ትምህርት ቤቱ ከጥሩ ትምህርት ከመስጠት ባለፈ ሥነምግባር ላይ በትኩረት ይሠራል ሲሉ ይገልጻሉ፡፡

በተለይም ሀገር አቀፍ ፈተናው ላይ በቂ ዝግጅት መደረጉንና ተማሪዎች ብዙ ያለፉ ዓመት ፈተናዎች እንዲሠሩ መደረጉን ገልጸው፤ የመጣው ውጤት የምንጠብቀው ነው ይላሉ፡፡

ሌሎች ትምህርት ቤቶች ከኔታ አካዳሚ በተለይም ተማሪዎች ላይ ከስር ጀምሮ መሥራትና ከትምህርቱ በተጨማሪ ሥነምግባር ላይ መሥራት እንደሚገባ ተሞክሮ መውሰድ ይኖርባቸዋል ብለዋል፡፡

በ2016 የትምህርት ዘመን ለሀገር አቀፍ ፈተና ከተቀመጡ 674 ሺህ 823 ተማሪዎች ውስጥ 36 ሺህ 409 ወይም 5 ነጥብ 4 በመቶ የማለፊያ ውጤት ማግኘታቸው ትምህርት ሚኒስቴር ማስታወቁ ይታወሳል፡፡

በአዲስ አበባ በ2016 ዓ.ም 21 ነጥብ 4 በመቶ ተማሪዎች የማለፊያ ውጤት ማምጣታቸውንና ከባለፈው ዓመት ጋር ሲነጻጸር የ5 በመቶ እድገት መመዝገቡን የአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ አስታውቋል፡፡

ከሰሞኑ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በ2016 የትምህርት ዘመን በ12ኛ ክፍል መልቀቂያ በሀገር አቀፍ ፈተና 500 እና ከዚያ በላይ የሆነ ውጤት ላስመዘገቡ 484 የከተማዋ ተማሪዎች እንዲሁም ተማሪዎቻቸውን ሙሉ በሙሉ ላሳለፉ የከተማዋ ትምህርት ቤቶች እውቅናና ሽልማት አበርክቷል፡፡ ተማሪ ሲፈኔ ተክሉና ተማሪ ፍሪና ሠላም ሽልማቱ ከተበረከተላቸው ተማሪዎች ውስጥ ግንባር ቀዳሚዎቹ ናቸው፡፡

በዚሁ ዓመት ፈተናውን ከወሰዱ ተማሪዎች መካከል ከ600 በተፈጥሮ ሳይንስ ከአዲስ አበባ ኦግዚሊየም ካቴድራል 575 በሴት ተማሪ በማኅበራዊ ሳይንስ ከኢትዮ ፓረንትስ 538 ከፍተኛ ውጤት መመዝገቡ ተገልጿል፡፡

# ከቡና፣ ሻይና ቅመማ ቅመም የወጪ ንግድ 522 ሚሊዮን ዶላር ያህል ገቢ ተገኘ

**ነፃነት ዓለሙ**



አዲስ አበባ፡- በ2017 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሦስት ወራት የቡና ሻይና ቅመማ ቅመም ምርት የወጪ ንግድ 522 ሚሊዮን ዶላር ያህል ገቢ መገኘቱን የቡናና ሻይ ባለሥልጣን አስታወቀ።

ባለስልጣኑ ለኢፕድ በላከው መግለጫ እንዳመለከተው፤ በበጀት ዓመቱ ሦስት ወራት 115 ሺህ 851 ቶን በላይ የቡና ሻይና ቅመማ ቅመም ምርት ወደ ውጭ በመላክ 522 ሚሊዮን ዶላር የሚጠጋ ገቢ ተገኝቷል፡፡

አፈጻጸሙ ባለፈው በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ከተላከው ጋር ሲነጻጸር በመጠን 69 በመቶ እና በገቢ የ46 በመቶ ጭማሪ መመዝገቡን አስታውቋል።

ከገቢው ከፍተኛ ድርሻ የሚይዘው ቡና ሲሆን፤ በበጀት ዓመቱ ሦስት ወራት 115 ሺህ 174 ነጥብ 75 ቶን ቡና በመላክ 519 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር መገኘቱን ባለሥልጣኑ ገልጿል። አፈፃፀሙ ከባለፈው በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር በመጠን 70 በመቶ እና በገቢ 47 በመቶ ጭማሪ መመዝገቡን አመላክቷል።

በ2017 በጀት ዓመት ሦስት ወራት የተላከው ቡና በመዳረሻ ሀገራት ሲታይ ጀርመን በመጠን 28 ሺህ 398 ነጥብ 68 ቶን የኢትዮጵያን ቡና በመቀበል አንደኛ ደረጃ ላይ እንደምትገኝ ተጠቁሟል።

ሳዑዲ ዓረቢያ 16 ሺህ 838 ቶን በላይ ቡና እንዲሁም ቤልጂዬም 12 ሺህ 503 ቶን በላይ የኢትዮጵያን ቡና በመቀበል ሁለተኛና ሦስተኛ ደረጃ የያዙ ሀገራት መሆናቸው ታውቋል።

ከአሜሪካ፣ ደቡብ ኮሪያ፣ ጃፓን፣ ዩናይትድ ዓረብ ኤሜሬትስ፣ ጣሊያን፣ ጆርዳን እና ፈረንሳይ የኢትዮጵያን ቡና በመግዛት ከአራተኛ እስከ 10 ያለውን ደረጃ ይዘዋል።

ዜና

# ምክክር ለኢትዮጵያ አማራጭ የሌለው ምርጫ

ውብሸት ሰንደቁ

ዜና ሐተታ

የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን በሶማሌ ክልል ጅግጅጋ ከተማ የአጀንዳ የማሰባሰብ የምክክር ምዕራፍ መድረክ እያካሄደ ነው።

ምክክሩ ከዚህ በፊት በአዲስ አበባ እና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች እንዲሁም በሐረሪ፣ በአፋር፣ በሲዳማ፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ ጋምቤላ እና በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልሎች መካሄዱም የሚታወስ ነው።

ሆኖም በሀገራዊ ምክክር ሂደቱ እጅግ ተማምነው የራሳቸውን አስተዋፅዖ ለማበርከት ከሚታትሩት መሳ ለመሳ የምክክሩን ፋይዳ በጥርጣሬ የሚያዩትም አልጠፉም።

ለመሆኑ ለኢትዮጵያ ከሀገራዊ ምክክር የተሻለ አማራጭ ይኖራታል?

ገራድ መሐመድ ገራድ ኩልምዬ የሀገር ሽማግሌ እና በሶማሌ ክልል ዋና የጎሳ መሪ ናቸው።

እርሳቸው እንደሚሉት ባለፉት 100 የሚሆኑ ዓመታት እንደ ሶማሌ ሕዝብ በጥይት እሩምታ የተሰቃየ ክልል የለም። ለዚህ መንስዔው የምክክር በር አለመከፈቱ ነው፡፡

የምክክር በሮች ክፍት አለመሆናቸውን ተከትሎም በንግግር መፍትሔነት ላይ ተስፋ የቆረጡ ብዙ ወንድሞቻችን የትጥቅ ትግልን መርጠዋል የሚሉት ኩልምዬ፤ ሀገራዊ ምክክር በሠላም አብሮ ለመኖርም ሆነ ስለዕድገት ለማሰብ አማራጭ የሌለው ምርጫ መሆኑን ይጠቁማሉ፡፡

የሶማሌ ክልል ሕዝብ፣ ኢትዮጵያ ሶማሌን ያካተተ መልክ እንዲኖራት ይፈልጋል ያሉት ዋና የጎሳ መሪው፤ የክልሉ ሕዝብ ጥቅምም እኩል ሊከበርለት እንደሚገባ ያነሳሉ።

ሕዝቡ ከሌሎች ወንድም ሕዝቦች ጋር ተባብሮና ተከባብሮ ለመኖር እንደሚፈልግ በመግለፅ፤ ሀገሪቱ አርብቶ አደር አርብቶ አደር የሚሸት ፖሊሲ እንዲኖራት ማድረግ እንደሚገባ ይናገራሉ። ይህንን ለማድረግ የሚቻለውም ምክክር ሲኖር ነው ባይ ናቸው፡፡

ኩልምዬ እንደሚሉት፤ የሱማሌ ክልል እኔን የማይመስል ሀገር ነው እያለ ወደ ትጥቅ ትግልና ግጭት በመግባት የተለያዩ ችግሮች የማይጠፉበት አካባቢ ሆኖ መቆየቱ የሚታወቅ ነው። በዚህም ምክንያት የሰው ሕይወት ሲጠፋ ቆይቷል።

እንደዚህ ዓይነት ችግሮችንም ለመፍታት ሀገራዊ ምክክሩ በወሳኝ ጊዜ የመጣ ነው ሲሉም ያስረዳሉ። እንዲያውም መቅደም ነበረበት ይላሉ፡፡

ሁሉንም ኢትዮጵያዊ የሚመስል ሀገረ መንግሥት እና ሀገር እንዲኖረን ሀገራዊ ምክክሩ እጅግ አስፈላጊ ነው ብለውም፤ ለዚህም ሁሉም የየድርሻውን ለመወጣት በመረባረብ ለስኬት ሊያበቃው ይገባል ሲሉ ጥሪያቸውን ያቀርባሉ፡፡

ሀገራዊ ምክክሩ የሀገራችን አጀንዳ ነው የሚሉት የሀገር ሽማግሌው፤ እንደ ኢትዮጵያዊነታችን በምክክሩ ያገባናል ብለዋል።

መመካከር ሲቻል የሶማሌን ክልል መልክ ያካተተ ሀገር እንዲመሠረት፤ ፖሊሲና ሕጎቿ የሱማሌን ክልል ሕዝብ ግምት ውስጥ ያስገባ ሀገር እንዲኖር እና ጠንካራ ሀገረ መንግሥት ግንባታ እንዲካሄድ መንገዶች ይኖራሉ ሲሉም ያስረዳሉ፡፡ ከወንድም ሕዝቦች ጋርም በሠላም ለመኖር የሚያስችል መንገድ መፍጠር የሚቻለው በምክክር እንጂ በግጭት አለመሆኑን መረዳት እንደሚገባ ነው የሚናገሩት።

ባለፉት 100 የሚሆኑ ዓመታት የክልሉ ሕዝብ በግጭቶች የተነሳ በርካታ መከራዎችን እንዳየ ጠቅሰው፤ ችግሮች በዚህ መንገድ የሚፈቱ ቢሆን ኖሮ ቀደም ብለው ሊፈቱ ይችሉ እንደነበር ጠቁመዋል።

ሆኖም በአሁኑ ወቅት ችግሮች መቶ በመቶ የሚፈቱት በመወያየት እና በሠላማዊ መንገድ መሆኑን በማመን ትጥቅ ትግል ሲያደርጉ የነበሩ ኃይሎች ሁሉ ወደ ሠላማዊ ትግል ገብተዋል ብለዋል። ይህም ምክክሩ የፈጠረው ተስፋ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

ሌሎች ክልሎች ከዚህ ትምህርት ሊወስዱ እንደሚገባ ጠቅሰው፤ ሰው ከሞተ እና ንብረት ከወደመ በኋላ ለውይይት ከመቀመጥ ሰው ሳይሞት እና ንብረት ሳይወድም ችግሮችን በጠረጴዛ ዙሪያ መፍታት ይገባል ሲሉም ያሳስባሉ። እንደ ሀገርም ከውይይት የተሻለ አማራጭ የለም ሲሉ ያክላሉ።

ሀገራዊ ምክክር ለምን አስፈለገ የሚል ጥያቄ ሁሌ ይነሳል የሚሉት ደግሞ የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ኮሚሽነር መላኩ ወልደማርያም ናቸው።

"ሀገራዊ ምክክር ያላስፈለገ ለኢትዮጵያ ምን ሊያስፈልጋት ይችላል?" ሲሉም ጥያቄውን በጥያቄ ይሞግታሉ።

ኢትዮጵያ እንደሀገር ከዚህ የበለጠ ነገር ሊያስፈልጋት አይችልም ያሉት ኮሚሽነሩ፤ የምክክሩ ዓላማም እስከዛሬ እርስ በርስ ሲያጨራርሰን ከኖረው አዙሪት እንውጣ የሚል መሆኑን ያብራራሉ።

በኢትዮጵያ ውስጥ ከዚህ በፊት ከተሠሩ፤ አሁን እየተሠሩ ካሉ እና ለወደፊት ከሚሠሩ ፕሮጀክቶች ሁሉ የሀገራዊ ምክክር አጀንዳን የሚያክል አይኖርም ሲሉም ያስረዳሉ።

ምክክሩ ሀገራዊ መግባባትን ለማምጣት ይረዳል የሚሉት ኮሚሽነር መላኩ፤ ይህም አለመግባባትን፣ እንደሀገር ልጅ አለመተያዬትን እና በየጊዜው የሚፈጠሩ ችግሮችን በዘላቂነት ለመፍታት የሚያስችል ነው ሲሉ ያስገነዝባሉ።

እንደ ኮሚሽነር መላኩ ገለፃ፤ ኢትዮጵያ በጦርነት እና በግጭት አዙሪት ውስጥ ነው ያለችው። ከዚህ አዙሪት መውጣት ይገባል።

ከአዙሪቱ መውጣት የሚቻለውም ሀገራዊ መግባባት መፍጠር ሲቻል መሆኑን በመግለጽ፤ ሀገራዊ መግባባት መፍጠርም የፀና ሀገረ መንግሥት ለመመሥረት ይጠቅማል ሲሉ በአመክንዮ ያስረዳሉ።

በተጨማሪም በምክክር የሚፈጠር ሀገራዊ መግባባት አዲስ የፖለቲካ ሥርዓት ለመቅረፅ ያስችላል ሲሉ ነው ያሉት።

ከዚህም ባሻገር ሀገራዊ ምክክሩ ትክክለኛ የሆነ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመዘርጋት እንደሚረዳ በመግለፅ፤ ከሁሉ በላይ ግን ሀገራዊ ምክክር ኢትዮጵያ የተሰኘች ሀገር የሁላችንም ኢትዮጵያውያን እንደሆነች ለማረጋገጥ ያስችላል ይላሉ።

ይህች ሀገር የእኛ የኢትዮጵያውያን ሀገር ናት፤ ዜጎቿም እኛ ኢትዮጵያውን ነን የሚሉት ኮሚሽነሩ፤ ይህንን ለማረጋገጥ የሀገራዊ ምክክሩ ቁልፍ ሚና ይጫወታል ነው ያሉት።

ምክክሩ ሰዎች የማይሞቱባት፣ የማይፈናቀሉባት ይልቁንም ዜጎች ተምረው ለከፍተኛ ደረጃ የሚበቁባት በሁሉም ዘርፍ ተሠማርተው ያለምንም መሸማቀቅ እና ስጋት የሚኖሩባት ሀገር እንድትሆን የሚያስችል መሆኑንም ነው የሚያነሱት።

ምክክሩ ይሳካል፤ መሳካትም አለበት ያሉት ኮሚሽነር መላኩ፤ ከምክክር ውጪ ሌላ ምርጫ የለም ሲሉ አፅንዖት ይሰጣሉ።



ገራድ መሐመድ ገራድ ኩልምዬ



ኮሚሽነር መላኩ ወልደማርያም



ኦሊቪያ ፒ ሊቪንግስቶን



ናስታሲያ ቲ ባውድ ኒጄንጋ



ንዩግማ ኦፓክፓጆር ጀምስ

# የአፍሪካ መዲና በአፍሪካ ወጣቶች ዕይታ

ዳግማዊት አበበ

ዜና ሐተታ

ከሰሞኑ ለሦስት ቀናት የቆየ የአፍሪካ አንድ ሺህ የወጣቶች ጉባዔ በአዲስ አበባ ተካሂዷል። ትኩረቱን የምግብ ሥርዓትና አግሮኢኮሎጂ ላይ ያደረገው ጉባዔ ላይ ለመታደም ከተለያዩ 45 በላይ የአፍሪካ ሀገራት የመጡ ከ250 በላይ ወጣቶች አዲስ አበባ ገብተዋል፡፡

ወጣቶቹ በጉባዔው በአፍሪካ የተረጋገጠ የምግብ ዋስትና እንዲኖር የመከሩ ሲሆን በቆይታቸው በከተማዋ የተሠሩና በመሠራት ላይ የሚገኙ የተመረጡ የልማት ሥራዎችን ጎብኝተዋል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅትም የልማት ሥራዎቹን ሲጎበኙ ያገኛቸውን የላይቤሪያ፣ ጋናና የኬንያ ወጣቶችን በጎበኟቸው የልማት ሥራዎች ዙሪያ ያላቸው አስተያየት ጠይቋል፡፡

ኦሊቪያ ፒ ሊቪንግስቶን ጉባዔው ላይ ለመሳተፍ ከላይቤሪያ የመጣች ወጣት ናት፤ ኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ እንደመጣች የገለጸችው ኦሊቪያ፤ በአዲስ አበባ ያለው የሕንጻ ግንባታዎችና በከተማዋ እየተሠራ ያለው የኮሪደር ልማት እንዳስደነቃት ትናገራለች፡፡

ኦሊቪያ፤ አዲስ አበባ በጣም ውብና በከተማዋ በተለያዩ ቦታዎች የተገነቡት ፓርኮች እና የመዝናኛ ቦታዎች ለነዋሪዎችም ሆነ ለጎብኚዎች በጣም ሳቢ መሆናቸውን ገልጻ፤ የላይቤሪያ መንግሥት በከተሞች በማስዋብ ረገድ ይህን ተሞክሮ ከኢትዮጵያ ወስዶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል ብላለች፡፡

በጉባኤው ላይ ሲነገረን የነበረውን ኢትዮጵያ የአረንጓዴ ዐሻራ ችግኝ ተከላ ንቅናቄ በጉብኝቴ ወቅት ከጠበኩት በላይ ሆኖ አግኝቼዋለሁ የምትለው ኦሊቪያ፤ ወደ ሀገሬ ይዤ የምመለሰው አንደኛው ተሞክሮ ነውም ብላለች፡፡

አረንጓዴ ዐሻራ ንቅናቄው በተለይም ትኩረቱን ለምግብ የሚሆኑ ችግኞች ላይ አድርጎ ከሠራ ኢትዮጵያ በምግብ እራሷን ለመቻል እያረገች ያለችውን ጥረት ያሳካል፡፡ ንቅናቄው በዋናነትም በአሁኑ ጊዜ በዓለም ላይ ያለው የአየር ንብረት ለውጥ ቀውስ ለመከላከል ትልቅ ሚና ይኖረዋል ስትልም ተናግራለች፡፡

ከአስር ዓመት በፊት ወደ ኢትዮጵያ እንደመጣችና የአሁኑ ለሁለተኛ ጊዜ እንደሆነ የምትናገረው ደግሞ ኬኒያዊቷ ወጣት ናስታሲያ ቲ ባውድ ኒጄንጋ ናት፡፡ ከተማዋ ላይ ካለፈው ጊዜ ካየችው ብዙ መሻሻሎችና እድገት መመልከቷንም ገልጻለች፡፡

ከጉብኝቴ ሁሉ በተለየ ያስደነቀኝ የኢትዮጵያ ታሪኮችና ባሕሎች በአግባቡ ተሰንደው መቀመጣቸው ነው ያለችው ወጣቷ፤ በተለይም ኢትዮጵያ በቅኝ ላለመገዛቷ ማሳያ የሆነው የዓድዋ ድል መታሰቢያ ሙዚየም አስደንቆኛል ብላለች፡፡

ኢትዮጵያ ከሌሎች አፍሪካ ሀገራት ልዩ የሚያደርጋት በርካታ ነገሮች አሏት፡፡ የአፍሪካ ኅብረት መቀመጫ መሆኗ፣ ምግቦቿ እንዲሁም የበርካታ ብሔሮች መገኛ መሆኗ ዋነኞቹ ናቸውም ትላለች፡፡

ሌላኛው በጉብኝት ወቅት ያገኘነው ከጋና የመጣው ንዩግማ ኦፓክፓጆር ጀምስ በበኩሉ፤ ወደ ኢትዮጵያ ሲመጣ የመጀመሪያው እንደሆነና ከጉብኝቱ በርካታ ዝርያ ያላቸው ዕፅዋቶችን መመልከቱ እንዳስደሰተው ገልጿል፡፡

ከተማዋን አረንጓዴ ለማድረግ እየተሠሩ ያሉ ሥራዎች የሚበረታቱ ናቸው ያለው ጀምስ፤ በተለይም በአንድነት ፓርክ ሁሉንም ብሔሮች ለመወከልና ለማስተዋወቅ የተሠራው ሥራ አስደንቆኛል፡፡ ይህም ኢትዮጵያ አንድነቷ የጠነከረ መሆኑን እንድረዳ አድርጎኛል ይላል፡፡

የተሠሩ የልማት ሥራዎች ለጎብኚዎች ምቹና የቱሪዝም ኢንዱስትሪው እንዲያድግ የሚረዳ ነው ያለው ወጣቱ፤ የኢትዮጵያ መንግሥት ፕሮጀክቶችን ሲሠራ የኢትዮጵያን ብሎም አፍሪካን ታሪክና ባሕል በሚወክልና በሚገልጽ መልኩ መሆን አለበት ሲል አስተያየቱን ሰጥቷል፡፡

የአፍሪካ ሀገራት የቱሪዝም ዘርፉን ለማሳደግ ያለውን ቢሮክራሲ ማቅለል እንደሚያስፈልግና በሁሉም የአፍሪካ ሀገራት ተዟዙሮ መጎብኘት ለሁሉም ዜጋ ቀላል መሆን አለበትም ይላል ጀምስ፡፡

# በመዲናዋ በከተማ ግብርና

## - ከአንድ ሺህ 300 በላይ ዜጎች የሥራ ዕድል ተፈጥሯል
## - ከ120 ሚሊዮን በላይ እንቁላል ተገኝቷል

አማን ረሺድ

አዲስ አበባ፡- በመዲናዋ ባለፉት ሦስት ወራት በከተማ ግብርና ከአንድ ሺህ 300 በላይ ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ ዕድል መፈጠሩን፤ ከዘጠኝ ሺህ ቶን በላይ የሥጋ ምርትና ከ120 ሚሊዮን በላይ እንቁላል መገኘቱን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን አስታወቀ፡፡

በኮሚሽኑ የኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ወንደሰን አካሌ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ በ2017 በጀት ዓመት በእንስሳትና በዕፅዋት ሃብት ልማት በግለሰብ፣ በማኅበራት እና በተቋማት ሰፋፊ የከተማ ግብርና ሥራዎች እየተሠሩ ይገኛል፡፡

በአዲስ አበባ በከተማ ግብርና ዘርፍ በሩብ ዓመት ለሦስት ሺህ ዜጎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ ባለፉት ሦስት ወራት ለአንድ ሺህ 330 ዜጎች አዲስ የሥራ ዕድል እንዳገኙ ጠቁመው፤ በዚሁ ዘርፉም ሰባት ሺህ 628 ቶን የሥጋ ምርት ለማግኘት ታቅዶ ከዘጠኝ ሺህ 378 ቶን የሥጋ ምርት መገኘቱን ተናግረዋል፡፡

እንዲሁም 132 ሚሊዮን 941 ሺህ በላይ እንቁላል ለማግኘት ታቅዶ ከ120 ሚሊዮን በላይ ማግኘት መቻሉን አመልክተው ፤ 900 ቶን የዶሮ ሥጋ ለማግኘት ታቅዶ አንድ ሺህ 442 ቶን ሥጋ ማግኘት ተችሏል ብለዋል፡፡

በተጨማሪም በወተት፣ በማር ፣ በዓሣ ምርት፣ በግቢ፣ በማሳና በጓሮ አትክልት ልማት ከእቅድ በላይ መከናወኑን አቶ ወንደሰን ጠቁመዋል፡፡

የሥራ ዕድሉ የተፈጠረው በእንስሳት እርባታ፣ በጓሮ አትክልትና ፍራፍሬ ልማት እንዲሁም በተለያዩ የግብርና ሥራዎች መሆኑን አስረድተዋል።

ኮሚሽኑ ወደሥራ ለሚሰማሩ ዜጎች የተለያዩ ሙያዊ ድጋፎችን እንደሚያደርግ አውስተው፤ በግብርና ዘርፍ የሥራ ዕድል ተጠቃሚ መሆን የሚፈልግ ማንኛውም ዜጋ ተደራጅቶ በመምጣት ምቹ ሁኔታውን ሊጠቀም እንደሚገባ አንስተዋል፡፡

በከተማ ግብርና የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ኮሚሽኑ በትኩረት እየሠራ መሆኑን ገልጸው፤ በቀጣይ በዘርፉ እየተሰጡ ያሉ የአቅም ግንባታ ሥልጠና፣ የግብዓትና ቴክኖሎጂ አቅርቦት፣ የሙያና ቴክኒክ ድጋፍና የልምድ ልውውጦች ተጠናክሮ እንደሚቀጥል አመላክተዋል፡፡

በዶሮ እርባታ፣ በወተት ላም፣ በከብት ማደለብ፣ በአትክልት ልማት፣ በችግኝ ማፍላትና በሌሎች የሥራ መስኮች ዜጎች በምርጫቸው ወደ ቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች በመግባት የክህሎት መር ሥልጠና እንዲወስዱና ወደሥራ እንዲሠማሩ እየተደረገ መሆኑን አቶ ወንደሰን አስረድተዋል።

# ዜና

# የማሕቀፍ ስምምነቱ ወደ ተግባር መግባቱ ኢትዮጵያ ላይ የሚቀርቡ ምክንያት አልባ ክሶችን ያስቀራል

**ሞገስ ፀጋዬ**

አዲስ አበባ፡- የናይል ተፋሰስ የትብብር ማሕቀፍ ስምምነት ወደ ተግባር መግባቱ በዓባይ ውሃ ኢትዮጵያ ላይ የሚቀርቡ ምክንያት አልባ ክሶችን የሚያስቀር መሆኑን በአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ የውሃ ሀብት ምሕንድስና ትምህርት ክፍል መምህርና ተመራማሪ ፕሮፌሰር መኮንን አያና አስታወቁ፡፡

ፕሮፌሰር መኮንን አያና ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የናይል ተፋሰስ የትብብር ማሕቀፍ ስምምነት ወደ አስገዳጅ ተግባር መግባቱ የዓባይ ውሃን ለብቻቸው የሚጠቀሙ ሀገራትን የበላይነት የሚያስቀር ነው፡፡ በአንጻሩ ደግሞ የተፋሰሱ ሀገራትን የጋራ ተጠቃሚነትን ያረጋግጣል። ተፋሰሱን በጋራ የመጠበቅና የማልማት ሥራዎችን ሕጋዊ ማሕቀፍ እንዲኖራቸው የሚያደርግ ጭምር ነው፡፡

የማሕቀፍ ስምምነቱ ወደ ተግባር መግባቱ ኢትዮጵያ ወንዙን በመጠቀም ለመልማት የምታደርገውን ጥረት ሕጋዊ ከማድረጉ በላይ በየጊዜው የሚቀርቡባትን ክሶች ውድቅ የሚያደርግና የሚያስቀር መሆኑን ገልጸዋል፡፡

እንደ ተመራማሪው ማብራሪያ፤ የናይል ተፋሰስ የትብብር ማሕቀፍ ስምምነት የተጀመረው እ.ኤ.አ ከ1997 ጀምሮ ነው፡፡ የናይል ቤዚን ኢኒሼቲቪ ለአስር ዓመታት ስምምነትና ውይይት ተደርጎበታል፡፡ ይህም በአባል ሀገራት መካከል መተማመን እንዲፈጠርና መወያየት እንዲችሉ አስችሏል፡፡ በመጨረሻም የናይል ተፋሰስ የትብብር ማሕቀፍ ስምምነት ወደ አስገዳጅ ተግባር መግባቱ የቅኝ ግዛት ውሎችን ውድቅ በማድረግ የጋራ ተጠቃሚነትን እንደሚያረጋግጥ ነው፡፡

የናይል የትብብር ስምምነት ተፈጻሚ መሆን የኢትዮጵያን የመልማት መብት ሌሎችን በማይጎዳ መልክ መሆኑን ያረጋግጣል ያሉት ተመራማሪው፤ ኢትዮጵያ ሁሌም ዓለም አቀፍ መርሆችን አጥብቃ ታከብራለች፡፡ የስምምነት ማሕቀፉ ተቋማዊ ሰውነት የሚኖረው በመሆኑ ለኢትዮጵያ ያለው ትርጉም ትልቅ ነው ብለዋል፡፡

የትብብር ማሕቀፍ ስምምነቱ ወደ አስገዳጅ ተግባር መግባቱ አግባብነት የሌላቸው ውንጀላዎችን ተቀባይነት ያሳጣል ያሉት ምሑሩ፤ በበላይነት እንጠቀም ከሚሉት ሀገራት ውጭ ለሁሉም የተፋሰሱ ሀገራት ጉልህ ጠቀሜታ እንዳለውም ገልጸዋል፡፡

በዓለም ላይ ሁለትና ከሁለት ሀገራት በላይ የሚያቋርጡ 276 ያህል ወንዞች መኖራቸውን የሚገልጹት ፕሮፌሰሩ መኮንን፤ ብዙዎች ግጭት የለባቸውም፡፡ ግጭት የሚስተዋልባቸው ድንበር ተሻጋሪ ወንዞች ኮሚሽን መሥርተው በጋራ ማስተዳደር በመቻላቸው ችግሮችን ቀርፈዋል፤ የጋራ ተጠቃሚነታቸውንም አረጋግጠዋል፡፡ የኢትዮጵያ ፍላጎትም ይሄው መሆኑን አስገንዝበዋል፡፡

የናይል ተፋሰስ የትብብር ማሕቀፍ በይፋ ወደ ተግባር መግባቱ የኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ የጥረት ውጤት መሆኑን አመልክተዋል፡፡

እንደ ፕሮፌሰር አያና ገለጻ፤ ግብጽና ሱዳን የትብብር ማሕቀፉን አንቀበልም እያሉ ነው፡፡ የዓባይን ወንዝ ለብቻቸው የሚጠቀሙበት በመሆኑ የጋራ ተጠቃሚነትን አልፈለጉትም፡፡ በቅኝ ግዛት ወቅት የወጡ ስምምነቶችን በማስጠበቅ የኢ- ፍትሐዊ ተጠቃሚነታቸውን የማስቀጠል ፍላጎት አላቸው፡፡

ነገር ግን ኮሚሽኑ ወደ ሥራ ሲገባና በእኩልነት ላይ የተመሠረተ አጠቃቀም ላይ ዕቅድ አውጥቶ መሥራት ሲጀምር እንደሚጠቅማቸው በመገንዘብ ተገደውና ወደው ሊፈርሙና ሊያፀድቁ ይችላሉ ብለዋል፡፡

ወንዙን በትብብር የመጠበቅና የመጠቀም ጉዳይ ለሁሉም የተፋሰሱ ሀገራት አዋጭ ነው የሚሉት ፕሮፌሰሩ፤ ግብፅና ሱዳን አምነውና ተገደው ወደ ኮሚሽኑ ይገባሉ። ኬንያ፣ ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ፣ ሱዳን ፈርመው ያላፀደቁ ሀገራት በመሆናቸው ኢትዮጵያ የማግባባት ሥራ መሥራትና ኮሚሽኑንን ማጠናከር እንዳለበት ጠቁመዋል፡፡

ግብፅን ከማሳመን ፈርመው ያላፀደቁ ሀገራት እንዲያፀድቁ ማድረግ ጥሩ አማራጭ መሆኑን አመልክተው፤ ኢትዮጵያ ዲፕሎማሲያዊ ሥራዋን በማጠናከር የፈረሙ ሀገራት እንዲያፀድቁ በማግባባት ውኃውን በብቸኝነት መጠቀም የሚፈልጉ ሀገራት ጉልበትን ማመናመን ይኖርባታል ነው ያሉት፡፡

የናይል ተፋሰስ የትብብር ማሕቀፍ በይፋ ወደ ተግባር በመግባቱ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተሰሚነት እንደሚኖረው ገልጸው፤ የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲያዊ ጥረቷን ውጤታማ መሆኑን አንዱ ማሳያ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

# "ኢትዮጵያውያን...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ሚኒስትሩ፤ ስቶክ ማርኬት በይበልጥ ጥቅም ላይ መዋል ስላለበት ኢትዮጵያውያን ዕድሉን ሊጠቀሙበት እንደሚገባ ገልፀዋል።

ከኢትዮ ቴሌኮም የ10 በመቶ ድርሻ ለሽያጭ ቀርቦ በሚገኘው ትርፋማነት ደግሞ ሌሎች ሥራዎችን ማከናወን ይቻላል ሲሉ አመላክተዋል። በዲጂታል ኢትዮጵያ ሥራዎች የታየው ውጤታማነት ለዚህ የአክሲዮን ሽያጭ አብቅቶናል በቀጣይም በሆቴል ዘርፉ የድርሻ ሽያጭ ይኖራል ሲሉ ጠቁመዋል።

በቀጣይም በሆቴል ዘርፍ ኢንቨስትመንቱን ለማስፋፋት የአክሲዮን ድርሻ ሽያጭ እንደሚኖር ጠቁመው፤ የካፒታል ማርኬት ልምምድና የአክሲዮን ድርሻ በመሸጥ ኢንቨስትመንትን በጋራ ማከናወን የሚቻልበትን ልምድ ማዳበር እንደሚገባ አስገንዝበዋል።

የምዕራፍ አንድ የአክሲዮን ሽያጩ ትናንት በቴሌ ብር አማካኝነት የተጀመረ ሲሆን፤ የአንድ አክሲዮን ብር 300 ሲሆን ዝቅተኛው የአክሲዮን መጠን 33 በመሆኑ ዝቅተኛው የአክሲዮን ግዥ 9ሺህ 900 ብር መሆኑ ይፋ ተደርጓል።

በአክሲዮን ሽያጩ እያንዳንዳቸው 300 ብር ዋጋ ያላቸው 100 ሚሊዮን መደበኛ አክሲዮኖች ለሽያጭ የቀረቡ ሲሆን መደበኛ አክሲዮኖች ከዝቅተኛው 9 ሺህ 900 ብር ወይም 33 አክሲዮኖች ጀምሮ እስከ ከፍተኛው 999 ሺህ 900 ብር ወይም 3 ሺህ 333 አክሲዮኖች መግዛት ይቻላል፡

ኢትዮ ቴሌኮም ወደ ሼር ካምፓኒነት መቀየሩን የተቋሙ ኃላፊ ፍሬሕይወት ታምሩ አስታውቀዋል።

የ10 በመቶ የአክሲዮን ሽያጩ ከትናንትና ጀምሮ እስከ ታኅሣሥ 25 ቀን 2017 ዓ.ም ድረስ ይቆያል፡፡ ይሁንና አጠቃላይ የአክሲዮን ድርሻው መጠን ከተጠቀሰው ቀን በፊት ተሸጦ ከተጠናቀቀ እስከተገለጸው ቀን ድረስ ላይቆይ እንደሚችል ታውቋል፡፡

# የኢትዮጵያ አየር ኃይል የተደራጀ አቅም ለአፍሪካ ሀገሮችም ምሳሌ የሚሆን ነው

**አዲሱ ገረመው**

ቢሾፍቱ፡- የኢትዮጵያ አየር ኃይል በቴክኖሎጂ የተደራጀ አቅም ለአፍሪካ ሀገሮችም ምሳሌ እንደሚሆን ተጠቆመ። በአፍሪካ መከላከያ ሚኒስትሮች ጉባኤ ኢትዮጵያ አፍሪካዊ አጀንዳን ማሳካት የምትችልበትን አቅም ማሳየቷ ተመልክቷል።

የአፍሪካ መከላከያ ሚኒስትሮች ጉባኤ ተሳታፊዎች በትላንትናው እለት የኢ.ፌ.ዴ.ሪ አየር ኃይልንና የቢሾፍቱ አውቶሞቲቭ ኢንዱስትሪን ጎብኝተዋል።

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ መከላከያ ሚኒስትር ኢንጂነር አይሻ መሐመድ በጉብኝት መርሐ ግብሩ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፣ ከጉባኤው አጀንዳዎች አንዱ የአቅም ግንባታ ሥራዎችን በጋራ ማከናወን ላይ ያተኮረ ነው። ኢትዮጵያም እንደ ሀገር ረጅም እድሜ ያስቆጠሩ ተቋማት ያሏት ሲሆን፣ የኢትዮጵያ አየር ኃይል አንዱ መሆኑን ጠቅሰው፣ በተቋሙ ውስጥ ያለውን የተደራጀ አቅም ለሌሎችም ምሳሌ ሊሆን የሚችል ነው።

ኢትዮጵያ በተለይም ባለፉት ስድስት ዓመታት በፀጥታው ዘርፍ የተደረገውን ሪፎርም በአግባቡ የተጠቀመችበትና ያሳየችበት ነው። በፀጥታ ተቋማት ውስጥ የተደረጉ የሪፎርም ሥራዎች ተቋማቱ ከኢትዮጵያ አልፎ አፍሪካዊ ተቋም የመሆን አቅም እንዳላቸው ተናግረዋል። ከዚህ ውስጥም የኢ.ፌ.ዴ.ሪ አየር ኃይል አንዱ ነው ብለዋል።

በአየር ኃይሉ ሌሎች አፍሪካውያን ሥልጠና ማግኘታቸውን አስታውሰው፣ ትብብሩና በየሀገሩ ያለውን አቅም መጠቀም ፋይዳው ጉልህ መሆኑን ያመላክታል ነው ያሉት። ተቋሙ እድሜ ብቻ ሳይሆን ትልቅ አቅም ያለውና በተለይም በአሁን ወቅት በቴክኖሎጂ የተደራጀና በበርካታ የልማት ሥራዎች ላይ የራሱን አስተዋፅዖ እያበረከተ እንዳለ ገልጸዋል።

ይህ የተቋም ቁመና ኢትዮጵያ እንደለመደችው የሁሉንም ሀገራት አየር ኃይሎች አሊያም በዘርፉ መሠልጠን ለሚፈልግ ሁሉ ማሠልጠን እንደምትችልና ከዚህ ቀደም ያላት ፍላጎት ያልተቀየረ መሆኑን ጠቅሰዋል።

ቅድሚያ ለአፍሪካ እንደምትሰጥ በመግለጽ፣ ተባብሮ መሥራት ከተቻለ አንድ አፍሪካዊ የተጠባባቂ ኃይል ሊኖር ይችላል ተብሎ የተቀመጠውን ግብ ማሳካት እንደሚቻል ጠቁመዋል። ጉብኝቱም ኢትዮጵያ ይህንን ሕልም ማሳካት እንደሚቻል ያሳየችበት እንደሆነም አመላክተዋል።

በመከላከያ ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን የአውቶሞቲቭ ኢንዱስትሪውና የሎጂስቲክ አቅም ምን ያህል እያደገ እንደመጣና ይህንንም አቅም ለሚፈልጉ ሀገራት በጥገናም ሆነ በማዘመን ረገድ ኢትዮጵያ ማገዝ እንደምትችል ነው የገለጹት። በዚህም ማንኛውም ደረጃ ያለው አፍሪካዊ አጀንዳ መሳካት እንደሚቻል በተግባር የታየበት ነው ያሉት።

ከጉባኤው ጎንን ለጎንን አልጄሪያ፣ ሊቢያና ሱዳንን ጨምሮ ከተለያዩ ሀገራት ጋር አብሮ መሥራት በሚቻልባቸው ጉዳዮች ላይ ፍሬያማ የጎንዮሽ ውይይቶች መደረጋቸውንም ሚኒስትሯ ገልጸዋል። በዚህም ውጤታማ ወታደራዊ የዲፕሎማሲ ሥራዎች መከናወናቸውን ተናግረዋል።

የዩጋንዳ መከላከያ ሚኒስትር ጃኮብ አቦት፣ ኢትዮጵያ ያሰናዳቸው የአፍሪካ መከላከያ ሚኒስትሮች ጉባኤ እንዲሁም የአየር ኃይሉ ጉብኝት ታሪካዊ ነው ብለዋል። ኢትዮጵያ ለአፍሪካ አጀንዳ በቁርጠኝነት እየሠራች መሆኗን ያየንበት ነው ሲሉ ገልጸዋል።

የደቡብ አፍሪካ የመከላከያ ሚኒስትር ዴኤታ ባንቱ ሆሎሚጋ በበኩላቸው ኢትዮጵያ የአፍሪካ መከላከያ ሚኒስትሮች ጉባኤን ማዘጋጀቷ አሕጉራዊ እና ቀጣናዊ የሠላምና ፀጥታ ጉዳዮችን ለማጠናከር አይነተኛ ሚና ያለው ነው በማለት፣ ሀገሪቷ በወታደራዊ ዘርፍ ያላት ትልቅ አቅምም ለሌሎች አቻ ሀገራት ትምህርት የሚሰጥ መሆኑን ገልጸዋል። ሁለቱ ሀገራት ትብብራቸውን የሚያጠናክሩበት መድረክ እንደነበረም አንስተዋል።

የአፍሪካ መከላከያ ሚኒስትሮች ጉባኤ "አፍሪካ በጠንካራ አንድነት፣ ለሁለንተናዊ ፀጥታና ሠላም" በሚል መሪ ሀሳብ በኢትዮጵያ አስተናጋጅነት ከትላንት በስቲያ ጀምሮ እየተካሄደ ሲሆን፣ የጉባኤው ተሳታፊዎች በትላንትናው እለት ቢሾፍቱ በሚገኘው የኢ.ፌ.ዴ.ሪ አየር ኃይል በመገኘት የሥልጠና እና የጥገና ማዕከላትን እንዲሁም የበረራ ትምህርት ቤትን ጎብኝተዋል።

በጉብኝቱ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ መከላከያ ሚኒስትር ኢንጂነር አይሻ መሐመድን ጨምሮ ከአፍሪካ ሀገራት የተውጣጡ የመከላከያ ሚኒስትሮች፣ ከፍተኛ ወታደራዊ መኮንኖችና ወታደራዊ አታሼዎች ተሳትፈዋል።

# አሳሳቢው ሕገወጥ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ሃሳባቸውን ሰጥተዋል።

በፍትሕ ሚኒስቴር የብሔራዊ የፍልሰት ትብብር ጥምረት ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ አብርሃም አያሌው እንደሚሉት፤ ሕጋዊ አማራጮችን ለማስፋት ዜጎች ሥልጠና ወስደው፤ በሕጋዊ ድርጅቶች ተመልምለው እንዲሄዱ ማድረግ ይገባል። ዜጎች ኢትዮጵያ የሁለትሽ የሥራ ስምምነት ወደ ፈረመችባቸው ሀገራት እንዲሄዱ እየተሠራ ነው፡፡

በዚህም በ2015 ዓ.ም ከ106 ሺህ በላይ ዜጎች፣ በ2016 ዓ.ም ደግሞ ከ345 ሺህ በላይ ዜጎች በሕጋዊ መንገድ ወደ ተለያዩ ሀገራት ለሥራ ተሠማርተዋል፡፡ ካለው ችግር አንጻር ግን አሁንም ብዙ መሥራት ይጠይቃል ይላሉ፡፡

ዛሬም ድረስ በርካታ ዜጎች ሕጋዊ መስመርን ሳይከተሉ ወደ ተለያዩ ሀገራት እንደሚሄዱ የሚጠቁሙት አቶ አብርሃም፤ በዚህም በሕገወጥ ደላላዎችና መልማዮች፣ አዘዋዋሪዎች፣ ድንበር አስተላላፊዎች፣ ተቀባዮች እና በዝባዦች እጅ ይወድቃሉ፡፡ በየደረሱበትም ለእንግልት፣ ለመብት ጥሰትና ለሞት ይዳረጋሉ ሲሉ ይገልጻሉ።

ፍልሰት የሚቆም ነገር ስላልሆነ መደበኛውን መንገድ ማስፋት፣ ተደራሽነቱን ማረጋገጥና ፍትሐዊ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ የሚሉት ኃላፊው፤ መደበኛ ያልሆነውን ፍልሰት ለመከላከል ደግሞ አደረጃጀት፣ ሕግና የአሠራር ሥርዓት መዘርጋትን ይጠይቃል ባይ ናቸው፡፡

አቶ አብርሃም እንደሚያስታውቁት፤ መንግሥት በሰው የመነገድና በሕገወጥ መንገድ ሰዎችን ድንበር የማሻገር ወንጀሎችን ለመከላከል የሚያስችል አዋጅና ሕጎችን አውጥቷል። የውጭ ሀገር ሥራ ስምሪትን ለመምራት የሚያስችል አዋጅ እንዲሁም ረቂት የፍልሰት ፖሊሲም ተዘጋጅቷል፡፡

አደረጃጀትን ከመፍጠር አኳያም በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚመራ ብሔራዊ ምክር ቤትም ተቋቁሟል፡፡ ፍትሕ ሚኒስቴር የሚመራው ብሔራዊ የፍልሰት ትብብር ጥምረትም ተቋቁሞ እየሠራ ነው ይላሉ፡፡

ሥራው የሁሉንም ተቋማት ትብብር የሚጠይቅ በመሆኑ የብሔራዊ የፍልሰት ትብብር ጥምረት ጽሕፈት ቤት የሚያስተባብራቸው በስድስት ተቋማት የሚመሩት ስድስት የሥራ ቡድኖች እንዳሉም ይጠቁማሉ፡፡

ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር በዓለም ላይ ከጦር መሣሪያና አደገኛ ዕፅ ዝውውር ቀጥሎ ከፍተኛ ገንዘብ የሚዘዋወርበት ነው የሚሉት አቶ አብርሃም፤ በዓመት ከ150 ቢሊዮን ዶላር በላይ የሚንቀሳቀስበት ቢዝነስ መሆኑ ይገልጻሉ፡፡

ይህን ወንጀል ለመበጣጠስ ሀገር ውስጥ ያሉ የወንጀል መከላከልና ሕግ ማስከበር ተቋማት ጠንካራ ትስስር ይፈልጋል። ለዚህም ፌዴራል ፖሊስ ይህን ወንጀል ለመመርመር ራሱን የቻለ ክፍል አቋቁሟል፡፡ ዓቃቤ ሕግም ይህንን ወንጀል ለመመርመርና ለማስረዳት ራሱን የቻለ አደረጃጀት አቋቁሟል። ፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤትም ራሱን የቻለ ችሎት አቋቁሟል ይላሉ፡፡ በዚህም ብዙ ወንጀለኞች ተይዘው ቅጣት እንደተላለፈባቸው ይጠቁማሉ።

ወንጀለኞቹ ሀገር ውስጥ ብቻ ስላልሆኑ ከሌሎች ሀገራት ጋር ትብብር ማድረግም አስፈላጊ መሆኑን የሚገልጹት አቶ አብርሃም፤ በዚህም ከጂቡቲ ጋር የጋራ የወንጀል ምርምራ ቡድን ለማቋቋም የመግባቢያ ስምምነት ተፈርሟል፤ ከኬንያ ጋርም ንግግር ተጀምሯል፤ ከሌሎች መተላለፊያና መዳረሻ ሀገራት ጋርም ንግግር ለማድረግ ሥራዎች እየተሠሩ ነው ሲሉ ያስረዳሉ፡፡

ለማኅበረሰቡ በሕገወጥ የሰዎች ዝውውር አስከፊነት ላይ ያለውን ግንዛቤ ለማሳደግ የተለያዩ ተግባራት እየተከናወኑ መሆኑን የሚጠቁሙት ኃላፊው፤ የሀገር ውስጥ የሥራ ዕድልን በማስፋት ወጣቶችን በሀገር ውስጥ ለማስቀረትና ተመላሾችን ተጠቃሚ በማድረግ ተመልሰው እንዳይሄዱ ለማድረግ ጥረቶች መጀመራቸውን ይገልጻሉ።

በሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር መከላከልና የተመላሽ ዜጎች ድጋፍና ክትትል መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ ደረጀ ተግይበሉ በበኩላቸው፤ ሕገወጥ ፍልሰትን ለመከላከል የተለያዩ ሥራዎች እየተሠሩ ነው፡፡ በሀገር አቀፍ ደረጃ ክትትል የሚደረግበት የግንዛቤ ማስጨበጫ እና የማኅበረሰብ ንቅናቄ ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛል።

መደበኛ ያልሆነ ፍልሰትን ስደትን መከላከያ አንዱ መንገድ መደበኛ ስምሪትን ማስፋፋት ስለሆነ የውጪ ሀገር ሥራ ስምሪትን ለማስፋት ጥረት እየተደረገ ነው። ከዚህ ውጪ ለተለያዩ ችግሮች የተጋለጡ ዜጎች ሲኖሩ ወደሀገር የመመለስ፣ መልሶ የማቋቋምና ከማኅበረሰቡ ጋር የማቀላቀል ሥራዎች ይሠራሉ ይላሉ፡፡

በዓመት ከ150 እስከ 200 ሺህ የሚደርሱ ኢትዮጵያውያን በተለያዩ መንገዶች ከሀገር እንደሚወጡ መረጃዎች ያሳያሉ የሚሉት መሪ ሥራ አስፈጻሚው፤ ሰዎች የተሻለ ሕይወት ፍለጋ የሚያደርጉት ፍልሰት የሚቆም አይደለም፤ ይልቁንም ፍልሰቱ በመደበኛ ሥርዓት እንዲሆን ማድረግ ይገባል ሲሉ ያስገነዝባሉ።

በሕገወጥ መንገድ የሚሄዱ ዜጎች ለተለያዩ አስከፊ ችግሮች እንደሚዳረጉ የሚጠቅሱት አቶ ደረጀ፤ በሕገወጥ አዘዋዋሪዎች እጅ ወድቀው ለጉልበት ብዝበዛ ፣ ለግዳጅ ጋብቻ፣ ለሰብዓዊ መብት ጥሰትና የሰውነት ክፍሎች ስርቆት እንደሚያጋጥማቸው ይጠቁማሉ። በተጨማሪም የአካል ጉዳት፣ የጀልባ መገልበጥና ሆን ተብሎ ወደ ውሃ አካላት መወርወር አደጋዎች ሕይወታቸውን የሚያጡበት ሁኔታም ይስተዋላል ይላሉ፡፡

ይህን ተከትሎም በየዓመቱ ከ130 ሺህ በላይ ዜጎች የተለያዩ ጉዳቶችን አስተናግደውና ተይዘው ወደሀገር ይመለሳሉ፤ መንገድ ላይ የሚቀሩትና የሚሞቱትም በርካታ መሆናቸውን ይገልጻሉ።

ከሕገወጥ የሰዎች ዝውውር የሚጠቀሙት ሕገወጥ አዘዋዋሪዎችና ደላሎች ብቻ መሆናቸውን የሚያነሱት አቶ ደረጀ፤ ወደተለያዩ ሀገራት ሄደው መሥራት የሚፈልጉ ዜጎች ሕጋዊ ሥርዓቶችን ብቻ ተጠቅመው መሄድ እንዳለባቸው ይጠቁማሉ።

በመደበኛው አሠራር ውስጥም በደላሎች የሚታለሉ ዜጎች መኖራቸውን የሚጠቅሱት መሪ ሥራ አስፈጻሚው፤ በቅርብ ጊዜም ወደታይላንድ እንወስዳችኋለን በማለት የተለያዩ ቴክኖሎጂ የተማሩ ዜጎችን በመመልመል ማይናማር ወደሚባል ሀገር መወሰዳቸውን ነው ያሳወቁት።

ከወሰዷቸው በኋላም ጉልበታቸውን አዕምሯቸውን የመበዝበዝና በተለያዩ ሕገወጥ ተግባራት እንዲሳተፉ እያደረጓቸው ነው፡፡ ስለሆነም ዜጎች በሕግ የታወቁት በመንግሥት ሥርዓት ውስጥ ያሉ ሂደቶችን ተከትለው መሄዳቸው አጠያያቂ ጉዳይ መሆን የለበትም ሲሉ ይገልጻሉ።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የግብርናውን ዘርፍ ለማዘመን !

ሀገሪቱ በ2016 በጀት ዓመት በተለያዩ ዘርፎች ውጤታማ አፈጻጸሞችን ማስመዝገብ ችላለች። ውጤቶቹ የተመዘገቡት ደግሞ በብዙ ውጣ ውረዶች ውስጥ ታልፎ መሆኑ ነው። መንግሥት ይህን አፈጻጸም በተለያዩ ወቅቶች በተለያዩ መንገዶች ሲገልጽ ቆይቷል። አዲሱ የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ታዬ አፅቀ ሥላሴ በቅርቡ በተካሄደው 6ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና የፌዴሬሽን ምክር ቤት 4ኛ ዓመት የሥራ ዘመን የመክፈቻ ስብሰባ ላይም ጠቅሰውታል።

ይህ ውጤታማ አፈፃፀም ከተመዘገበባቸው ዘርፎች መካከል የግብርናው ዘርፍ አንዱ ነው። ፕሬዚዳንቱ እንዳስታወቁት፤ በግብርናው ዘርፍ በበጀት ዓመቱ 6ነጥብ 9 በመቶ እድገት ተመዝግቧል፤ 700 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ከዋና ዋና ሰብሎች ማግኘት ተችሏል። የስንዴ ምርት እጅግ የሚያኮራና ልምድ የተቀመረበት መሆኑን ፕሬዚዳንቱ ጠቁመው፣ ስንዴ በመኸር 122 ሚሊዮን ኩንታል፣ በመስኖ ደግሞ 107 ሚሊዮን ኩንታል ማምረት መቻሉንም አመልክተዋል። የዚህ የስንዴ ልማት ስኬት ሀገሪቱ በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ስንዴ ለሁለተኛ ጊዜ ለውጭ ገበያ መላክ ያስቻለ መሆኑን ጠቅሰው፣ የበቆሎና የሩዝ ምርታማነትን ለመጨመር እየተሠራ መሆኑንም አስታውቀዋል።

በግብርናው ዘርፍ ለተመዘገበው ውጤት በርካታ ምክንያቶች ሊጠቀሱ ይችላሉ፤ ከእነዚህ መካከልም በዘር የሚሸፈነውን መሬት ማስፋፋት አንዱ ነው። በዚህም በኩልም ትልቅ ለውጥ መታየቱን ፕሬዚዳንቱ አስታውቀዋል። ፕሬዚዳንቱ እንዳሉትም፤ በ2015 በጀት ዓመት የታረሰው መሬት 20 ሚሊዮን ነጥብ 3 ሄክታር ነበር፤ ይህን አኃዝ በ2016 በጀት ዓመት በአምስት ሚሊዮን ሄክታር በማሳደግ ከ26 ነጥብ ሁለት ሚሊዮን በላይ ሄክታር መሬት ታርሷል።

መንግሥት ይህን ዕድገት በ2017 በጀት ዓመትም ለማስቀጠል በትኩረት እንደሚሠራ ፕሬዚዳንቱ አስታውቀዋል። ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የግብርና ዘርፍ ለመገንባት ትኩረት ሰጥቶ እንደሚሠራ አስታውቀው፣ በእዚህም በተለይ ለመስኖ ልማት ትኩረት በመስጠት የመስኖ ሜካናይዜሽን ሥራዎች እንዲጠናከሩ እንደሚደረግ አመልክተዋል።

መንግሥት በዘርፉ የተመዘገበውን ዕድገት አድንቆ፣ በቀጣይም በግብርናው ዘርፍ ላይ ውጤታማ ሥራ ለመሥራት አቅጣጫ ማስቀመጡ የዘርፉን ምርትና ምርታማነት ይበልጥ ለማሳደግ ያለውን ቁርጠኝነት አጠናክሮ መቀጠሉን ያመለክታል። የዘርፉን ምርትና ምርታማነት በሜካናይዜሽን አገልግሎት ይበልጥ ለማረጋገጥ፣ የመስኖ ልማቱን አጠናክሮ ለመቀጠልም ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል።

እስከ አሁንም በመንግሥት ቁርጠኝነትና ክትትል የመኸርና የበልግ የግብርና ሥራን በማጠናከር፣ በመኸርና በበልግ ተወስኖ የኖረውን የግብርና ሥራ በመስኖ ይበልጥ እንዲጠናከር በማድረግ በዘርፉ በአጭር ጊዜ ውስጥ ታሪክ ማስመዝገብ ተችሏል። በስንዴ ልማት በመኸርና በመስኖ እየተገኘ ያለው ምርት ለእዚህ በአብነት ይጠቀሳል። በዚህም ብዙ የውጭ ምንዛሪ ተመድቦ ከውጭ ይመጣ የነበረውን ስንዴ በሀገር ውስጥ የስንዴ ምርት መተካት ተችሏል። ሀገሪቱ የውጭ ምንዛሪ ይዛም ስንዴ ለመግዛት እንዳትችል ጫና ይደርስባት እንደነበር ይታወቃል። በስንዴ ላይ የታየው ለውጥ ይህን ጫናም ማስቀረት ችሏል። የስንዴ ፍላጎትን በራስ አቅም መሸፈን የመቻል ነፃነትን አጎናጽፏል።

ይህ ምርታማነት የመጣው መንግሥት ለዘርፉ ያደረገውን ድጋፍና ክትትል ተከትሎ ነው። ይህን ዘርፍ በመደገፍ ብዙ ማትረፍ እንደሚቻል መንግሥት በጽኑ ይታመናል። ለእዚህም ማዳበሪያ በድጎማ እያቀረበ ያለበት ሁኔታ፣ በሜካናይዜሽን ማሽነሪዎች እና በብድር አቅርቦት ላይ በትኩረት የተሠራበት ሁኔታ በአብነት ይጠቀሳሉ። ሀገር በውጭ ምንዛሪ እጥረት በተፈተነችባቸው ባለፉት ዓመታት ለግብርናው ዘርፍ ምን ያህል ቅድሚያ በመስጠት ማዳበሪያ ሲያቀርብ እንደነበር ይታወቃል።

መንግሥት እንዳለፉት ዓመታት ሁሉ በዚህ ዘርፍ ላይ ትኩረት አድርጎ ለመሥራት አቅጣጫ ማስቀመጡ የምግብ ዋስትናን ከማረጋገጥና የውጭ ምንዛሪ ማስገኘት አንድ ነገር ሆኖ የተረጂነትን አመላካከትንም ለመስበር ለተያዘው አቅጣጫም አቅም ይሆናል። የስንዴ መስኖ ልማቱ ተጠናክሮ ይቀጥላል። እንደ ሩዝ ባሉት ሰብሎች ላይም የስንዴውን ታሪክ ለመድገም እየተሠራ መሆኑ ይታወቃል። በእነዚህ ምክንያቶችና ዘርፉ ገና ብዙ ሊሠራበት የሚችል ብዙ እምቅ አቅምም ያለው ከመሆኑ ጋር በማያያዝ በተቀመጠው አቅጣጫ መሠረት መሥራት ከዘርፉ አካላት ሁሉ ይጠበቃል።

ሀገር እጅ አጥሯት በውጭ ምንዛሪ እጥረት ሳቢያ ያላከናወነቻቸውን የግብርናውን ዘርፍ ሥራዎች ለመሥራት አሁን ምቹ ሁኔታ እንዳለ ይታሰባል። በቅርቡ ወደ ትግበራ የገባው የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ የዘርፉን ልማት ለማፋጠን የሚያስፈልገውን የውጭ ምንዛሪ ለማግኘት ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥር ይጠበቃል። በዚህም ለሜካናይዜሽን አገልግሎት በወሳኝ መልኩ መስፋፋት መሥራት ያስፈልጋል። ይህ ሲሆን የዘርፉን እቅድ ማሳካትም ብቻ ሳይሆን ከተቀመጠው እቅድም በላይ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ ይቻላል።

አሁን ባለው ተነሳሽነት፣ ቁርጠኝነትና ክትትል ላይ ይህም ማድረግ ሲቻል ባለፉት ዓመታት በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ ምርትና ምርታማነትን ሲያሳድግ የቆየው የግብርናው ዘርፍ ውጤታማነቱ ከእስከ አሁኑም የላቀ ሊሆን እንደሚችል ጥርጥር የለውም። በተለይ ለዘርፉ ምርትና ምርታማነት እድገት ወሳኝ ሚና ለሚጫወተው የሜካናይዜሽን አቅርቦትና ለሌሎች የመስኖ ልማት ሥራዎች ለሚያስፈልጉ ቴክኖሎጂዎችና ለመሳሰሉት የውጭ ምንዛሪ ማቅረብ ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባል።

**አዲስ ዘመን**

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

<u>የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ</u>
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

<u>ዋና አዘጋጅ</u>
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

<u>አድራሻ</u>
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

<u>የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ</u>
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

<u>የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር</u>
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

<u>የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ</u>
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

<u>የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች</u>
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

<u>የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል</u>
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

<u>የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ</u>
ስልክ - 011-1-26-43-39

<u>ማከፋፈያ</u> ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የላቀ ዕድገትን የወጠነው የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ

**ፌኔት (ከመሳለሚያ)**

በኢትዮጵያ ካለፉት ስድስት ዓመታት ወዲህ ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያዎችን በመተግበር ሊናቁ የማይችሉ የኢኮኖሚ ዕድገቶች ተመዝግበዋል። የቅርቡን ማለትም ከ2016 ዓ.ም እስከ 2018 ዓ.ም ይተገበራል ተብሎ የታቀደው ሁለተኛው የኢኮኖሚ ማሻሻያን ተከትሎ፤ በ2016 ዓ.ም በሁሉም ዘርፎች የኢኮኖሚ መነቃቃት በመፍጠሩ 8 ነጥብ 1 በመቶ የኢኮኖሚ ዕድገት ማስመዝገብ ተችሏል።

ይህንን በተመለከተ አፅንዖት ሰጥተው የተናገሩት የፕላንና ልማት ሚኒስትሯ ፍፁም አሰፋ (ዶ/ር)፤ ኢትዮጵያ ኢኮኖሚዋን በሚፈትኑ ትልልቅ ችግሮች ውስጥም ሆና፤ የሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራም በመተግበሯ ባለፈው ዓመት ግብርና በ 6 ነጥብ 9 በመቶ ማደግ ችሏል። የዋና ዋና ሰብሎች ዘርፍ ዕድገትም 7 ነጥብ 8 በመቶ የተመዘገበ ሲሆን፤ የኢንዱስትሪ ዕድገትም ዘጠኝ ነጥብ ሁለት በመቶ ማድረስ ተችሏል። የአገልግሎት ዘርፍም እንዲሁ 7 ነጥብ 7 በመቶ ማደግ የቻለ ሲሆን፤ በአጠቃላይ 8 ነጥብ 1 በመቶ የኢኮኖሚ ዕድገት ማስመዝገብ ተችሏል ብለዋል።

ይህ ዕድገት የተመዘገበውም በኢትዮጵያ ከተከሰቱ ግጭቶች፣ ከኮቪድ ወረርሽኝ የከረመ ተፅዕኖ እና ከአየር ንብረት መዛባት ተፅዕኖ አንፃር ሲታይ ትልቅ ነው። በተጨማሪ በዓለም አቀፍ ደረጃ በሀገራት ኢኮኖሚ ላይ ተፅዕኖ እያሳደሩ ያሉ የሀገራት ጦርነቶች በዋናነት ለዓለም ከፍተኛ የስንዴ ምርትን በማቅረብ በተመሰከረላቸው በሩሲያ እና በዩክሬን መካከል የሚካሄደው ጦርነትን ተከትሎ በየሀገራቱ የተከሰተውን የዋጋ ንረት በመቋቋም የመጣ ውጤት መሆኑ ሲታይ እጅግ ትልቅ መሆኑን መካድ አይቻልም። እናም ይህ ሁሉ ተደማምሮ ሲታይ ኢትዮጵያ የቀረፀችው ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ለኢትዮጵያ ዕድገት እና ብልፅግና ተኪ የሌለው ሚናን እየተጫወተ መሆኑ እሙን ነው።

የኢኮኖሚ ማሻሻያው ቀጣዩን የኢትዮጵያን የዕድገት ደረጃ ከፍ እንዲል ከማድረግ ባሻገር፤ ገበያን ማረጋጋት፣ የዕዳ ጫናን ማቃለል እና ገቢን ማሳደግ ላይ እያስገኘ ያለው ጠቀሜታ ከፍተኛ በመሆኑ ትልቅ ተስፋ ተጥሎበታል። የዓለም አቀፉ የገንዘብ ድርጅት (አይ ኤም ኤፍ)ም በባለሙያዎቹ ያካሔደው ጥናት ይህንኑ አረጋግጧል።

> **የኢኮኖሚ ማሻሻያው ቀጣዩን የኢትዮጵያን የዕድገት ደረጃ ከፍ እንዲል ከማድረግ ባሻገር፤ ገበያን ማረጋጋት፣ የዕዳ ጫናን ማቃለል እና ገቢን ማሳደግ ላይ እያስገኘ ያለው ጠቀሜታ ከፍተኛ በመሆኑ ትልቅ ተስፋ ተጥሎበታል**

ይህን ተከትሎ ከሰሞኑን የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ታዬ አፅቀ ሥላሴ በዓመቱ የትኩረት ነጥቦች ዙሪያ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና ለፌዴሬሽን ምክር ቤት ባቀረቡት የመክፈቻ ንግግር ላይ እንደገለፁት፤ በተያዘው ዓመት በዋና ዋና የኢኮኖሚ ዘርፎች ላይ ያሉትን ችግሮች በማቃለል 8 ነጥብ 4 በመቶ የኢኮኖሚ ዕድገት ማስመዝገብ የሚቻልበት ምቹ ሁኔታ መፍጠር እንደሚገባ አስቀምጠዋል። ካነሷቸው ነጥቦች መካከል የኢንቨስትመንት እና የንግድ ከባቢን ማሻሻል፤ የዘርፎች ምርታማነት እና ተወዳዳሪነትን ማሳደግ እና የመንግሥትን የመፈፀም አቅም ማጎልበት ትኩረት የሚሰጣቸው መሆናቸውን ገልፀዋል።

በእርግጥ የኢኮኖሚ ዕድገትን በተመለከተ ኢትዮጵያ በምታደርገው ብርቱ ጥረት የውጭ ምንዛሪ ግኝትን እና የውጭ ኢንቨስትመንት ፍሰትን እንዲሁም በሀገር ውስጥ የገንዘብ እንቅስቃሴን ለማሳለጥ የተወሰዱ እርምጃዎች የሚያበረታቱ ውጤቶችን በማስመዝገብ ላይ ናቸው። በተለይ በቅርቡ የተደረገው ሁሉን አቀፍ የኢኮኖሚ ማሻሻያ ለበርካታ ዓመታት ማነቆ ሆኖ የቀጠለውን የውጪ ምንዛሪ ችግር ለመፍታት እና ኢኮኖሚው ወደ ሚፈለግበት ደረጃ ለማሻሻል የሚረዳ መሆኑም በመታየት ላይ ነው።

ቀደም ሲል ውጪ የሚልኩ አምራቾችን የሚጎዳና ሽቀጥ አስገቢዎችን የሚያበረታታው እና ሀገርን የሚጎዳ አካሔድ፤ በተቃራኒው ሀገርን በሚጠቅም የኢኮኖሚ እድገትንም በሚያረጋግጥ መልኩ መስመር እየያዘ ይገኛል። እርምጃው ኢ-መደበኛ የንግድ አሠራሮችን ለማስቀረት ምቹ ሁኔታን በመፍጠር ላይ ሲሆን፤ በተለይ በሕገወጥ መንገድ የሚፈሱ እና የሚተላለፉ የውጪ ምንዛሪ ሒደቶችን በሕጋዊ መንገድ ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ እያስቻለ ነው።

ይህ ሂደት ራስን ከመቻል ጋር ተያይዞ መንግሥት ከያዘው አቅጣጫ አንፃር የሀገሪቱ ኢንዱስትሪዎች የገበያ ድርሻ ከፍ በማድረግ የገጠመንን የንግድ ሚዛን መዛባት እና የዕዳ ጫናን በዘላቂነት ለመፍታት ያስችላል። ለውጪ ኢንቨስተሮችም ምቹ ሁኔታ በመፍጠር ረገድ ከፍተኛ ሚና የሚጫወት ሲሆን፤ ይህም የሥራ ዕድልን ከመፍጠር በተጨማሪ ምርትና ምርታማነትን በማጎልበት፤ አምራችና ተጠቃሚን የሚያግዝ እና የሚያበረታታ ምቹ መደላድል ለመፍጠር ይረዳል።

በተጨማሪ የውጪ ምንዛሪ ችግርን ለመፍታት ተግባራዊ የተደረገው የገንዘብ ፖሊሲ ባንኮች ከዲያስፖራ የሚያገኙትን ገቢ ለማሳደግ፤ ኢኮኖሚያችንን ዘመናዊ ከማድረግ ባሻገር ድጋፎችን ለማግኘት እንደሚረዳም ታውቋል። ይህንን በተመለከተ የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ታዬ አፅቀ ሥላሴም እንዳሳወቁት፤ በቀጣይ ዓመት ከልማት አጋሮች እና ከዓለም አቀፍ የፋይናንስ ተቋማት ኢኮኖሚያችንን የሚደግፍ እና ለዕድገታችን ማስፈንጠሪያ 27 ቢሊዮን ዶላር ለማሰባሰብ የሚያስችል ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል። ከዚህ ቀደም ተቋርጦ የነበረውን በሦስት ዓመት የሚተገበረው የስድስት ቢሊዮን ዶላር የቀጥታ ድጋፍ ለመተግበር የሚያስችል ዕድል መገኘቱንም ጠቁመዋል።

የኢኮኖሚው ማሻሻያውና ይህንንም ተከትሎ እየተወሰዱ ያሉ እርምጃዎች በተለይም የውጪ ምንዛሪውን በተመለከተ የተወሰደው መፍትሔ፤ ኢትዮጵያ ከቀረው የዓለም ሀገራት ጋር ያላትን እና እያደገ የመጣውን ትስስር ለማጠናከር እንደሚያስችላት ተጨባጭ ውጤት ማግኘት ተችሏል።

በሀገር ውስጥም የኢኮኖሚው ማሻሻያውን ተከትሎ ጠንካራ ተቋማዊ አቅም መፍጠር የሚገባ ሲሆን፤ ፕሬዚዳንቱ እንዳመላከቱት፤ ይበልጥ የላቀ ውጤት ለማስመዝገብ ኢንቨስትመትን በሚያበረታታ መልኩ ከባቢ ሁኔታን ማሻሻል ያስፈልጋል። በአገልግሎት ዘርፍ የሚታየውን ሰፊ ኢ-መደበኛነት በመቀነስ እና ወደ መደበኛነት በመቀየር፣ በፋይናንስ ዘርፍ የታየውን መነቃቃት ማስቀጠል ይገባል። እነዚህን በትክክል ማድረግ ከተቻለና ወደ ጠንካራ የዲጂታል አገልግሎት ማምራት ላይ ትኩረት ከተሰጠ፤ የኢኮኖሚ ዕድገቱን ይበልጥ ማሳደግ የማይቻልበት ሁኔታ አይኖርም።

በአጠቃላይ ያደሩ እና የተወሳሰቡ ችግሮች አሉታዊ ተፅዕኖ ቢያሳድሩም፤ የሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያ ሥርዓት በመተግበሩ ኢኮኖሚው 8 ነጥብ 1 በመቶ ማሳደግ ተችሏል። የተወሳሰቡት ችግሮች ባይኖሩ ምን ያህል ዕድገት ሊመዘገብ እንደሚችል ሲታሰብ አጓጊ ውጤት እንደሚመጣ መተንበይ ከባድ አይሆንም። ይህ አጓጊ ውጤት በትክክል መገኘት እንዲችል፤ የተወሰኑ ተቋማት እና የመንግሥት አካላት ብቻ ሳይሆኑ ባለሀብቶች እና መላው ኢትዮጵያውያን የየራሳቸውን ሚና መጫወት ይጠበቅባቸዋል።

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ

# “የትብብር ማሕቀፍ ስምምነቱ ለኢትዮጵያ ትልቅ ስኬት ነው”


ኢንጂነር ሀብታሙ ኢተፋ (ዶ/ር)
የውሃና ኢነርጂ ሚኒስትር

አስቴር ኤልያስ

ኢትዮጵያን ጨምሮ የላይኞቹ የዓባይ ወንዝ ተፋሰስ ሀገራት በኢ-ፍትሃዊ የውሃ ክፍፍል ሕግ ተጠፍንገው አንድ ምዕተ ዓመት ለተቃረበ ጊዜ ቆይተዋል። በተለይ ኢትዮጵያ ከምድሯ የሚነሳውን የዓባይ ወንዝ እንዳትነካ በታችኞቹ ሀገራት በተለይም በግብጽ ሲፎከርባትና ሲዛትባት ከርሟል።

ይሁንና ኢትዮጵያ ይህን የቅኝ ገዥዎችን ሕግ “ይሁና” ብላ ዝም ማለትን ምርጫዋ አላደረገችም። ለሕዝቧ ይበጃል ያለችውን የሃይድሮ ኤሌክትሪክ ኃይልን መስጠት የሚያስችል ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብን እውን አድርጋለች፤ በዚህ ብቻ ሳያበቃ ተቀባይነት በሌለውና ሁለት ሀገራትን ብቻ ተጠቃሚ የሚያደርገውን ሕግ ውድቅ ሊያደርግ የሚችልና በፍትሃዊነት ላይ የተመሰረተ አጠቃቀምን መሰረት ያደረገ የናይል ወንዝ ተፋሰስ የትብብር ማሕቀፍ ስምምነትን የተፋሰሱ ሀገራት እንዲፈርሙና እንዲያጸድቁ በማድረግ ከሰሞኑን ወደ ሕጋዊ ሰነድ አሳድጋዋለች።

ይህንኑ የናይል ወንዝ ተፋሰስ የትብብር ማሕቀፍ ስምምነት ሕጋዊ መሆንን በተመለከተ የኢፌዴሪ የውሃና ኢነርጂ ሚኒስትር ኢንጂነር ሀብታሙ ኢተፋ (ዶ/ር) ከትናንት በስቲያ ለጋዜጠኞች መግለጫና ማብራሪያ የሰጡ ሲሆን፣ ይህንኑ እንደሚከተለው አጠናቅረን አቅርበነዋል። መልካም ንባብ።



ፎቶ፡- ሑዲሽ አብርሃ

**የትብብር ስምምነት ማሕቀፉ እንደምታ**

የናይል ወንዝ ተፋሰስ የትብብር ማሕቀፍ ስምምነት ከ17 ዓመት በላይ ሲታሰብበት የነበረና ሲሰራበትም የቆየ ሲሆን፣ ከጥቅምት 3 ቀን 2017 ዓ.ም ጀምሮ ሕጋዊ ሰነድ፣ ሕጋዊ ማሕቀፍ ሆኖ ይቀጥላል። በስምምነቱ ላይ በተለይ ሀገራችንን የሚጠቅም ልማት በተለያየ ጊዜ በዓባይ ላይ ማልማት እያሰብንና እየፈለግን በተለያየ ምክንያት ሳይሆንልን ቀርቷል፤ ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ በዋናነት የኢትዮጵያን ስም በማጠልሸትና እንዳንጠቀምም አሳሪ ሕጎችን በማስቀመጥ ይደረግ በነበረው አካሔድ ነው። በአሁኑ ወቅት ግን ስምምነቱ፣ የነበረውን አሳሪ ሕግ ሽሮ ለኢትዮጵያውያንም ለሌሎች ሀገሮችም ጭምር ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያበረክት ነው፡፡ በመሆኑም ለእኛ ደግሞ ተጠቃሚነቱ ላይ የአንበሳው ድርሻ እንድንወስድ የሚያደርግ ነው።

## ስምምነቱ፣ የነበረውን አሳሪ ሕግ ሽሮ ለኢትዮጵያውያንም ለሌሎች ሀገሮችም ጭምር ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያበረክት ነው

በዚህ ስምምነት ላይ አስራ አምስት ዋና ዋና መርሆዎች አሉ። እነዚህ ዋና ዋና መርሆዎች በሶስት ቦታ ብንከፍላቸው አንደኛው በተለይ ወደ አራት የሚሆኑት ዋና ዋና መርሆዎች የመጠቀም መብት ጉዳይ ጋር የተገናኙ ሃሳቦች ያለቡት ነው። ሁለተኛው ጉዳይ ይህን የውሃ ሀብት መጠበቅ፣ መንከባከብና ተፋሰሱ ላይ ልማቶችን በማካሔድ ዘላቂ አገልግሎት የሚሰጥ በማድረግ ላይ ኃላፊነትን የሚሰጥ፣ ሁሉንም የተፋሰሱ ሀገራት ኃላፊነት የሚሰጥ፣ የሚያስገድድ ሥርዓት በውስጡ ይዟል።

ሶስተኛው ጉዳይ መረጃዎችን በመከፋፈል የልማት እቅድ፣ የውሃ ፍሰት መጠን የተለያዩ በተፋሰሱ ላይ ያሉትን ማንኛውንም መረጃ እያንዳንዱ የተፋሰሱ አባል ሀገራት እርስ በእርሳቸው መረጃ እየተለዋወጡ እንዲሄዱ የሚያግዝ መርሆዎችን ይዟል። እነዚህ መርሆዎች በ45 አንቀጾች የተደገፉ ናቸው። 45ቱን አንቀጾች ብናይ የመጀመሪያዎቹ 15ቱ፤ 15ቱን መርሆዎች የሚመልሱ ሲሆን፣ የቀሩት 30 የሚሆኑቱ ደግሞ ከሕግ እና ከተቋም አሰራር ጋር የተገናኘ በቀጣይ ምን እንደሚሆን የሚገልጹ ናቸው።

ስለዚህ የዚህኛውን የናይል ወንዝ ተፋሰስ ትብብር ማሕቀፍ ስናወራ ከትርጉሙ ጀምረን ምን ምን እንዳለው አይተን፤ በተለይ ለኢትዮጵያ ጠቀሜታው ምንድን ነው? ብለን ብናይ ብዙ ነው። በታችኛው የዓባይ ወንዝ ተፋሰስ ያሉ ወንድሞቻችን ግብጽና ሱዳን እነርሱን ብቻ ተጠቃሚ የሚያደርግ ነባር ሕጎችን ይዘው የመጡ ናቸው። ይህ ሲሆን በተለይ ኢትዮጵያ ከ85 በመቶ በላይ ለዓባይ (ለናይል ወንዝ) እያወጣች ምንም ሳትጠቀም ወይም ደግሞ ኢትዮጵያ እንዳትጠቀም ሲደረግ ቆይቷል፤ ይህ ስምምነት ግን የነበረውን ሥርዓት በትልቁ ቀይሮ እኛም የመጠቀም መብት እንዲኖረንና ሌሎቹም መጠቀም እንዲችሉ የሚያደርግ ነው።

በተለይ ለኢትዮጵያውያን ስንል የነበረው፤ እኛ እኩል እና በፍትሃዊነት የመጠቀም መብት ይኖር የሚል ነው። እንዲያ ስንል እኩል ውሃ መጠቀም ሳይሆን የመብቱን እኩልነት ነው የማናየው። ከዚያ በኋላ ባዋጣነው ልክ ደግሞ መጠቀም ያስፈልገናል። ስለዚህ በጣም ትልቅ የውሃ መጠን ወደ ናይል ወንዝ ይፈስሳል። በዚያው ልክ ለመብራት (ሃይድሮፓወር )፣ ለመስኖ፣ ለመጠጥ ውሃ ለማንኛውም ሥራዎች ለመጠቀም ከፍተኛ እድል ሰጥቶናል። በዚህም ኢትዮጵያውያን ልንኮራበት ይገባናል።

በዚሁ አጋጣሚ የዛሬ 15 እና 16 ዓመት ይህ ሃሳብ ሲጠነሰስ የነበሩ ከፍተኛ ባለሙያዎች፣ ሚኒስትሮች፣ መሪዎች ሊመሰገኑ ይገባል። እኛ ኢትዮጵያውያን አንዱ የጀመረውን ማስቀጠል ልማዳችን ነው። እኛ ዛሬ ስኬቱን ስናጭድ ትናንት በጣም ብዙዎች ዋጋ ከፍለውበት ነው። ከባለሙያ፣ ከሚዲያና ከመንግሥት አመራር ጀምሮ ይህ ማኀቀፍ እንዲሳካ ከፍተኛ ድርሻ ያበረከቱ ወገኖቻችን አሉና ይመሰገናሉ።

እነርሱ ብቻ ሳይሆኑ አጎራባች ሀገሮች በተለይ ደቡብ ሱዳን እውነት ለመናገር በቅርብ ጊዜ በሚያስገርም ሁኔታ ስምምነቱን ተመልክተው በፍጥነት እንዲጸድቅና ሕግ እንዲሆን በማድረጋቸው በትልቁ ይመሰገናሉ። በዚሁ አጋጣሚ የደቡብ ሱዳን አምባሳደር በጉዳዩ ላይ ያበረከቱት አስተዋጽኦ ከፍ ያለ ነው። በተለየ ሁኔታ ደግሞ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትራችን ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በመሪዎች ደረጃ በሚደረጉ ስብሰባዎች ላይ ድርሻቸው የጎላ ነበር። ሌሎች ኢትዮጵያውንም በየደረጃው ያበረከቱት አስተዋጽኦ ከፍ ያለ ነው።

ይህ ማሕቀፍ ለእኛ ትልቅ ስኬት ነው። ባሳካነው ልክ ቅሬታ ያላቸው የሚመስሉ የታችኛው ተፋሰስ ሀገራት ወገኖቻችን ደግሞ አሉ። የዚህ ማሕቀፍ ዋና ዓላማ ማንንም ለመጉዳት አይደለም። እኛም መጠቀም፤ እነሱም መጠቀም መብታቸው ነው። ትልቁ ነገር በትብብርና በጋራ ማልማት በጋራ ማደግና በመተጋገዝ መሥራት ሲሆን፣ የተፋሰሱን ሀገራት ዜጎች እኩል ተጠቃሚ ማድረግ ማስቻል መሆኑን በዚሁ አጋጣሚ ማስገንዘብ እወዳለሁ።

**ማሕቀፉን በተመለከተ ቀጣይ ሥራ**

በቀጣይ የምንሰራቸው አንደኛውና ትልቁ ሥራችን የዚህ ማሕቀፍ ከጥቅምት 3 ቀን 2017 ዓ.ም ጀምሮ ሕግ መሆን የሚያግዘን የዓባይ ወንዝ ኮሚሽን ወይም ደግሞ ናይል ሪቨር ቤዚን ኮሚሽን ምስረታን ነው። እንሰራ የነበረው እስካሁን ባለን ኢኒሼቲቭ ነው፤ ኢኒሼቲቭ የተባለው ናይል ቤዚን ሲሆን፣ በአስሩ ሀገሮች ውስጥ ያለን ተሰባስበን (አስር ያልኩት ኤርትራ ስለማትመጣ ነው) በየዓመቱ የውሃ ሚኒስትሮች ስብሰባ እናደርጋለን፤ ምን ላይ እንደምንወያይም እንነጋገራለን። ሃሳቦችንም እንቀያየራለን። ስብስቡ በኮሚቴ ደረጃ ነው።

አሁን የዚህ ማሕቀፍ መጠናቀቅ ትልቁ ድርሻ በቀጣይ ለሚኖረን ኮሚሽን የራሱን መሰረት መጣሉ ላይ ነው።

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

# ወቅታዊ

# "የትብብር ማሕቀፍ ስምምነቱ...

ከገጽ 6 የዞረ

በቀጣይ በሁሉም ሀገሮች የሚሰሩ የልማት ሥራዎችን የሚያስተባብር ያ ኮሚሽን ይሆናል። ኮሚሽኑ የሚያግዝ፣ የሚመራም ይሆናል። ለእሱ ደግሞ ኢትዮጵያ ከፍተኛ ድርሻ እየበረከተች ትገኛለች። በተለይ ኢኒሼቲቩ እዚህ እንዲደርስ ጭምር በየዓመቱ የምናወጣው ወጪ ከማንም በላይ ነው፤ ከየትኛውም ሀገር በላይ ትልቁን ወጪ የምታወጣው ኢትዮጵያ ናት። ከዚህም የተነሳ የትብብር ማሕቀፉን በዚህ ደረጃ ማሳካት ችለናል።

በአጭር ጊዜ ደግሞ የኮሚሽኑ መቋቋም ትልቁ የምንጠብቀው ጉዳይ ሆኖ ከዚያ በተረፈ ደግሞ በሌሎችም ዓለም ላይ ያለው ኮሚሽን ተመሳሳይ ልምድ ያላቸውንም ልምድ የምንቀስም ይሆናል።

## ማሕቀፉን ከነበሩ ስምምነቶች የሚለየው

የናይል ተፋሰስ የትብብር ማሕቀፍ ከሌሎቹ የሚለው በፊት የነበረው ሕግ አቃፊ ባለመሆኑ ነው። ውሃውን ሁለት ሀገራት ብቻ የተካፋፈሉበት ሁኔታ ብቻ ነበር። በዚህ መልኩ የቀደመው ስምምነት የላይኞቹ ተፋሰስ ሀገራትን የረሳ ሕግ ነበር። ይህ ሕግ ተቀባይነትም የለውም። ተቀባይነት የሌለው ምክንያት ሁለቱም የታችኞቹ ተፋሰስ ሀገራት ለናይል ወንዝ ምንም አስተዋጽኦ አያደርጉም።

ኢትዮጵያ 86 በመቶ አስተዋጽኦ ስታደርግ የምትጠቀመው የውሃ ሀብት ምንም አልነበረም። ሁለተኛው በሌሎቹ ነጭ ዓባይ በምንላቸው ላይም በዚያ ደረጃ ላይ ችላ ተብሏል። ስለዚህ የበፊቱ ስምምነት አቃፊ ያልሆነና የተወሰኑ አካላትን ብቻ ተጠቃሚ የሚያደርግ ነው። እናም የታችኛው አካባቢ ያሉ ሀገሮች ዓባይን በባለቤትነት እንዲያስተዳድሩ መብት የሰጣቸው ነው። የትብብር ማሕቀፉ በተለየ ሁኔታ በዓባይ ወንዝ ላይ አስተዋጽኦ ያላቸው ሀገሮች በዚያ ልክ እንዲጠቀሙ የሕግ ማሕቀፍ እንዲሆን ያስፈለገበትና ወደሥራም የተገባበት ምክንያት ለዚህ ነው።

ስለዚህ በፊት የነበረው ሕግ የቅኝ ገዥ ሕግ ነው። የቅኝ ገዥ ሕግ ደግሞ ከዚህ በኋላ የሚያስኬድ አይሆንም፤ ምክንያቱም አፍሪካ ከቅኝ ግዛት ነፃ ወጥታለች። ከአሁን በኋላ መሥሪያ ቤትም አይኖረውም። በዚያ ደረጃ ሲታሰብም በጣም አግላይ ሕግ ነበር። ይህ የአሁኑ ግን አቃፊ ሕግ ነው።

በሌላ በኩል ግብጾች ከሰሞኑን መግለጫ አውጥተዋል። ባወጡት መግለጫ ጉዳዩን አሳዩ እንጂ በተለያየ ጊዜ በምናደርጋቸው ስብሰባዎች ሁለቱም ሀገሮች ማለትም ግብጾችም ሆኑ ሱዳኖች አቋማቸውን ያንጸባርቁ ነበር።

እኛ እያልን ያለነው ውሃን የታችኞቹ ሀገራት በብቸኝነት አይቆጣጠሩ ነው። የታችኞቹ ሀገራት ጽንሰ ሐሳብ ውሃውን በብቸኝነት እንጠቀም ነው፤ በላይኞቹ ሀገሮች አካባቢ ያለን ሀገራት የምንለው ደግሞ በጣም ፍትሃዊ በሆነ መንገድ የመጠቀም መብት እናግኝ የሚል ጽንሰ ሐሳብ ነው።

የታችኞቹ ሀገራት አካሔድ ዓለም ላይ ካለው ተሞክሮም በጣም በሚገርም ሁኔታ የሚፋለስ ነው። ለምሳሌ ሚኮንግ (Mekong River) ወንዝ የሚባል ኢሽያ ውስጥ አለ። በዚህ ወንዝ ተፋሰስ ያሉ "ሚኮንግ ወንዝ ኮሚሽን" እንዲቋቋም የሚፈልጉት የታችኞቹ ሀገራት ናቸው። ምክንያቱም ውሃ ከላይ ስለሚመጣ ማለት ነው። እኛ ዘንድ ደግሞ ነገሩ የተገላቢጦሽ ሆኖ ነው የታየው፤ ካለው ሕግም ጭምር የሚጻረር ሆኖ ነው የተገኘው።

በግብጽ በኩል ሰሞኑን ይፋ የተደረገውን ሃሳብ አስተውለናል። ኢትዮጵያ ያላት አቋም በማንኛውም ጊዜ ለመነጋገር በሯ ክፍት መሆኑ ነው። በተለይ ኢኒሼቲቩ ወደኮሚሽን ከመጣ በኋላ እነሱ ከእኛ ጋር ይቀጥላሉ፤ አንገፋቸውም። ምክንያቱም ኢትዮጵያ ፍትሃዊነትን እየፈለገች ኢ-ፍትሃዊነትን ለማስፈን አትሔድም።

ስለዚህ ፍራቻ ካላቸው በቀጣይ በሚኖሩ መድረኮች ላይ በዚሁ አጋጣሚ የሱዳንም የግብጽም ወንድሞቻችን በተለይ ሁለቱ አቻዎቼ የውሃ ሚኒስትሮች ወደ መድረኩ መጥተው በሃሳብ መነጋገር ሌሎቹንም አፍሪካዊ ወንድሞቻቸውን ማቀፍ እንዲችሉ ጥሪዬን ማስተላለፍ እፈልጋለሁ።

## የትብብር ማሕቀፉ ካሉት አንቀጾች መካከል በይደር ስለተቀመጠው አንቀጽ

በትብብር ማሕቀፉ አንቀጽ 14 ቢ ላይ ያለው በይደር የታለፈው የደህንነት ጉዳይ ነው። ወደ ኮሚሽኑ የሚመጣ አካል ሲመጣ አንዱ ሃሳብ የሚሆነው ይኸው ነው ማለት ነው። ይህ ማለት የውሃ ደህንነትን ለሁሉም ሀገሮች እንዴት አድርገን ነው ተጠቃሚ በሚያደርግ ደረጃ ላይ



እያበሰልን የምንሔደው በሚል ታስቦ የገባ ነው። ስለዚህ የማንኛውም አባል ሀገር ጥያቄ ችላ የሚባል ሳይሆን በዚህ ውስጥ ተካትቶ የሚሄድ መሆኑንም ለማሳየት በሕግ ማኅቀፉ ላይም ስላስቀመጥን መብታቸው ነው ማለት ነው።

## የተፋሰሱ ሀገራት ውሃን በጋራ ከመጠቀም አኳያ

በጋራ መጠቀምን በተመለከተ አስቀድሜ ያነሳኋቸው አንቀጾች ላይ በግልጽ ተቀምጧል። እያንዳንዱ አባል ሀገር ሲያቅድ ምን እንደሚሰራ በጋራ ስምምነት እንስማማበታለን ማለት ነው። ስለዚህ ኢትዮጵያ ላይ ለምሳሌ ለመስኖ ካቀድን ምን ያህል እንደምናወጣ ምን ያህል እንደምንጠቀም ስለሚታወቅ የታችኞቹ ደግሞ በዚያው ልክ ራሳቸውን ያስማማሉ።

እንዲህ ስናደርግ የታችኞቹ አይጠቀሙ ማለት አይደለም። የእነርሱንም ታሳቢ አድርጎ ጠቅላላ በዓባይ ላይ ያለው የውሃ መጠን ስንት እንደሆነ ታይቶ እያንዳንዱ ሀገር ለዚያ እንዲሆነው በድርሻው ልክ መጠቀም በሚያስችል ደረጃ ላይ ቴክኒካል ማየትን ይጠይቃል ማለት ነው።

ለምሳሌ የሕዳሴ ግድብን ወስደን ብናይ በጣም በተሳካ ሁኔታ ጨርሰን ስንቀመጥ ባለፉት ዓመታት ሲራገቡ የነበሩ አሉባልታዎች እንደሚጎዳቸውና እንደማይጠቅማቸው እንዲያውም አደጋ እንደሚያመጣባቸው ተብሎ ሲነገር የሰነበተ ጉዳይ ነው። ዛሬ እነርሱ ከሚሉት በተገላቢጦሽ እኛ ባልነው ልክ ተፈጽሞ እናገኘዋለን። ሕዳሴ ሕዳሴ ሆኗል። እነርሱ የሚፈልጉት የውሃ መጠን ምንም ሳይቀንስባቸው ይልቁኑ እነርሱን ተጠቃሚ በሚያደርግ ደረጃ ጎርፍ ሆኖ በየዓመቱ እንደሚሰማ የሚታወቅ ነው። ካርቱም ላይ ችግር ነበር። በዚህ ዓመት ይህ ሁሉ ዝናብ ዘንቦ ካርቱም በጎርፍ አልተጎዳም። ለምን ቢባል የሕዳሴ ግድብ በቂ ውሃ በመያዙ ነው ማለት ነው። ስለዚህ ተጠቃሚ ናቸው።

በጋ ላይ ብናይ ከሕዳሴ በፊት የነበረው የውሃ መጠን የሚሄድላቸው አራት ወይም አምስት እጅ ነው። ከሕዳሴ በኋላ ተጠቃሚ ነው የሚያደርጋቸው። ስለሆነም ኢትዮጵያም ትጠቀማለች፤ እነርሱም ይጠቀማሉ። በዚህ መልኩ ልማቱም ጥቅሙም የጋራ ይሆናል ማለት ነው። ስለዚህ ቲዎሪ ብቻ ሳይሆን በተግባር መሬት ላይ ስላለን የትብብር ማኅቀፉ የሚደግፈው ይህን ነው። የሚያጠናክረውም ይህንኑ ነው፡።

## ዓባይን ከኃይል ማመንጫነት ባሻገር

እንግዲህ በማንኛውም ፕሮጀክት ላይ የመጀመሪያው ትልቁ ሥራ የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ይደረጋል። በትብብር ማሕቀፉ ላይም አንዱ አንቀጻችን ይህ ነው። ማንኛውም የሚሰራ ሥራ ኢትዮጵያ የምታለማው፤ ሱዳን የምታለማው፤ ዑጋንዳ የምታለማው በታችኞቹ የተፋሰሱ ሀገራት ላይ ምንም ተጽዕኖ ማድረስ መቻል የለበትም። በዚህ ደረጃ መሰረት ፕሮጀክቶች እየተገመገሙ ያልፋሉ።

ይህ ትልቁ ነገር ሲሆን፣ እዚያ አካባቢ ምን ያህል መሬት ለመስኖ እንደሚለማ ማየት በጣም ያስፈልጋል። ሌላው ልማት የሚካሔደው ውሃ ስላለ ብቻ አይደለም፤ መሬቱ ለመስኖ የሚመች መሆኑን ማየት በጣም ያስፈልጋል። እዛ አካባቢ የምናለማቸው እና ለዚያ አካባቢ መሆን የሚችል የሰብል ዓይነቶች መኖራቸውም ጥናት ማድረግ ያስፈልጋል። እኛ እስካሁን ባለን መረጃ በዓባይ ተፋሰስ ውስጥ በጣም ብዙ አቅሞች አሉ። በተለይ በታችኛው አካባቢ ብናይ ወደ ዳቡስ አካባቢ በጣም ትልቅ ሥራዎች አሉን። ወደ በለስ አካባቢም በጣም ሰፊ መሬት አለን። ይህንን ደግሞ ኢትዮጵያ የመጠቀም መብት አላት።

ነገር ግን ስንጠቀም ውሃውን አድርቀን ሳይሆን ቴክኖሎጂን በጣም መሰረት ባደረገ መልኩ እና ውሃ በሚቆጠብ መንገድ ነው። ስለሆነም ልማቶቻችን የታችኞቹን ታሳቢ አድርገን የምንሰራቸው ሥራዎች ይሆናሉ፤ በዚህ መልኩም ይቀጥላሉ ማለት ነው። ግብርና ከተባለ እርሻ ብቻ አይደለም። ዓሳ እርባታ ትልቁን ድርሻ ይይዛል፡፡ ግድቦች ካሉ እኛ ዓሳ እዚያ አካባቢ እያመረትንና ትክክለኛ ሥራ እየተፈጠረ ለሌሎች ሀገሮችም በረከት ሆነን ኃይልም እያመነጨን መጠቀም እንችላለን።

## ውሃ ማልማትን በተመለከተ

ውሃውን በተመለከተ ምንም የማያመነጩ ሀገራት አሉ፤ ነገር ግን ተጠቃሚ ናቸው። እኛ በዚያ ልክ ውሃ እንዲያመነጩ አናስገድድም። ምክንያቱም ጉዳዩ የተፈጥሮ ጉዳይ ነው፤ ዜጎች ናቸው፤ የእኛ ወንድሞች ናቸው። ከዓባይ/ ናይል የመጠቀም መብትም አላቸው ማለት ነው። ስለዚህ እዚህ ጋ እኛ በምናደርጋቸው ሥራዎቻችን ውሃንም እኛ እናጎለብታለን። እናለማለን፤ ለምሳሌ አረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብር ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትራችን የዛሬ አምስትና ስድስት ዓመት ትልቁ ያስጀመሩትና ውሃ ሀብት ላይ ሲሰራበት የቆየ ነው። ስለዚህ እነዚያን ያህል ችግኞችን በዓባይ ተፋሰስ በተከልን ቁጥር በጣም ከፍተኛ የሆነ የውሃ መጠን እንዲመነጭ እንደርጋለን። በጣም ከፍተኛ የሆነ የውሃ መጠን ሲመጣ ደግሞ በዚያ አካባቢ የሚመጣውን የአፈር መሸርሸር እንቀንሳለን። ስለዚህ ኩልል ያለ በጣም ንጹህ ውሃ ለወንድሞቻችን ይደርሳል። እኛ ስንባረክ ለእነሱም በረከት እንሆናለን። ይህ ደግሞ በማኅቀፉም ውስጥ ጭምር አለ። እና የዚህ ማኅቀፍ ስምምነት የምናወራውን እናደርጋለን ሳይሆን በጣም ብዙዎችን ተግብረን መሬት ላይ በመታየት ላይ ናቸው።

## ማሕቀፉ የታችኞቹን ተፋሰስ ሀገራት አስገዳጅ ያደርጋል?

አስገዳጅ ነው ወይ ለተባለው አንዱ የዚህ ማኅቀፍ ይዘት መረጃ መቀያየር ነው፤ መረጃ ማለት የውሃ መጠን ብቻ ሳይሆን ፕሮጀክቶችን ነው፡። መሬት ላይ ምን አለ? የምንፈልገው ምንድን ነው? በቀጣይ የምናለማው ምንድን ነው? የሚሉ መረጃዎችን መለዋወጥ የግድ ይላል። እነርሱ (የታችኞቹ ተፋሰስ ሀገራት) ወደ መድረኩ መምጣት የማይፈልጉት ለዚያ ነው። የሚፈርሙ ከሆነ ይመጣሉ። ደግሞ መረጃውን በሰጡ ቁጥር ተጠቃሚ ይሆናሉ። ምክንያቱም የሚሄድላቸው ውሃ መጠን ያላቸውን የውሃ ፍላጎት ታሳቢ ስለሚያደርግላቸው ማለት ነው። እሱ ከዚያ አኳያ የሚታይ ነው።

## የኮሚሽኑ ተጠሪነት

ከአፍሪካ ኅብረት ጋር ያለው ግንኙነት እያንዳንዱ ሀገር የትብብር ማሕቀፉን በፓርላማው ካጸደቀ በኋላ ወደ አፍሪካ ኅብረት ያመጣል። ከመጣ በኋላ ከ60 ቀን በኋላ ወደ ሕግ እየገባ ይሄዳል። የጥቅምት 3ቱ ቀን ዋና ዓላማ ሱዳን ስድስተኛ ሀገር ናት፤ ሱዳን ካስገባች በኋላ ስድስት በመሙላቱ ባለን አንቀጽ መሰረት ሕግ ይሆናል ተብሎ ስለሚታሰብ ነው። ከዚያ በኋላ የሚኖረው ማንኛውም ዓይነት ቅሬታ ማንኛውም ዓይነት ጉዳይ ካለ ወደ አፍሪካ ኅብረት ጥላ ስር መሄድን እንደ አማራጭ ማየት ይቻላል።

ትልቁ ነገር ግን በእያንዳንዱ ተፋሰስ ሀገራት መካከል ያሉ ጉዳዮች መፈታት ያለበት በኮሚሽን ደረጃ ነው። ማንም ሰው የራሱን ቅሬታና የራሱን ሃሳብ እንዲሁም የተለየ ነገር ሲያቀርብ የሚያቀርብበት ሁኔታ ሥርዓትና ሕግ አለው። ያንን ተከትሎ ወደዚያ መሄድ ይችላል።

ሀገራት ከገቡም በኋላ መውጣት ይችላሉ። በስምምነቱ ላይ ብናይ ማንኛውም ወደ ሥርዓቱ ገብቶ በሥራ ላይ ያለ ሰው ሥርዓቱን ተከትሎ ደግሞ አልፈልግም ካለ እና ካላዋጣው ያንን የማድረግ ነገሮች አሉት ማለት ነው። እዚህ ላይ ትልቁ ነገር ከመረጃ ልውውጥ ጋር ከታችኞቹም እየለማ ያለውና በቀጣይም የሚለማ ያለው የውሃ መጠን በቀጣይም ሊመጣ የሚችል የውሃ መጠንን በፕላትፎርሙ ደረጃ ይሰራል። ይህ ደግሞ ትልቁን ሥራ የሚወጣው ኮሚሽኑ ነው። በኮሚሽኑ ውስጥ ደግሞ የከፍተኛ ሥራ ባለቤቶች ሚኒስትሮች ናቸው። የአስራ አንዱ ሀገሮች የውሃ ሚኒስትሮች ካውንስል ናቸው። ስለዚህ ምክር ቤት አለው ማለት ነው። በዚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ስር ሴክተራል አድቫይዘር ኮሚቴ የሚባል አለ። ባለሙያዎች ከሁሉም ሀገር ይወጣጡና ቴክኒካሊ መታየት ያለባቸውን ጉዳይ እነርሱ ከጨረሱ በኋላ ለሚኒስትሮች ቀርቦ ለውሳኔ ይሆናል። አንዳንድ ጉዳዮች አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ወደ ሀገር መሪዎች እንዲሔዱ ሊደረጉ ይችላሉ። እሱ ግን ግዴታ ሳይሆን እንደ አስፈላጊነቱ የሚሔድ ነው።

ኮሚሽኑን ስናቋቋም የሚሆነው ዑጋንዳ ኢንቴቤ ላይ ነው። የዚህ ኮሚሽን ቅርንጫፎች የተለያየ ቦታ ይኖራሉ። ለምሳሌ አሁን ባለው ደረጃ ኢንትሮ የሚባል አለ። ኢንትሮ ማለት የምስራቅ አፍሪካ ቴክኒካል ሪጂናል ኦፊስ ማለት ነው። ስለዚህ የሱዳንም የደቡብ ሱዳንም የኢትዮጵያም የግብጽም ጨምሮ የእነሱ ባለሙያዎች የሚሳተፉበት በጋራ የምንመራው የራሱ የሆነ ቅርንጫፎች አሉት።

የቀሩት ሀገሮች ከዚህ በኋላ በርግጠኝነት ይፈርማሉ፤ ያጸድቁታልም። እኛ በዲፕሎማሲ የምንሰራው በምንገናኝበት ጊዜ ከውሃ ሚኒስትሮች ጋር እንነጋገርበታለን፤ በተለይ ከማንም በላይ የኬንያ ወገኖቻችን ተጠቃሚዎች ናቸው። ምክንያቱም የሚገኙት የላይኞቹ ላይ ነው። ስለዚህ እንደ ኢትዮጵያ ውሃ ሰጪ ናቸው እንጂ ተቀባይ አይደሉም። ወደ ዓባይ ወይም ወደ ናይል ለማጽደቅ ሲመጡ ተጠቃሚ ይሆናሉ፤ እንኳን ፊርማ ጀምረው ያላጸደቁ ቀርተው እኛ የምንጠብቀው የግብጽ ወገኖቻችንንና የሱዳን ወገኖቻችንንም ወደማሕቀፉ እንዲመጡ ነው። ምክንያቱም በቀጣናው አካባቢ በሁሉም አባል ሀገራት ላይ ያለው ሕዝብ ብዛት የምናስተዳድርበት ብቸኛው መንገድ የተፈጥሮ ሀብትን በመጠቀም ነው። ሰው ያለው አማራጭ የአየር ንብረት እየተዛባ በሄደ ቁጥር መስኖ ነው። መስኖ ለመጠቀም ሲኬድ ደግሞ የሚታየው ውሃ ነው።

## ምስጋና

በመጨረሻም ኢትዮጵያውያን በተለይም በትብብር ማሕቀፉ ስምምነት ላይ አስተዋጽኦ ሲያበረክቱ የነበሩ በሙሉ በናይል ወንዝ ተፋሰስ ውስጥ ያላችሁ ማኅበረሰብ እንኳን ደስ ያላችሁ። ምክንያቱም በናይል ወንዝ ተፋሰስ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በጣም ብዙ ሀገሮችን የሚያሳትፍ ሕግ፣ ሥርዓት፣ ማሕቀፍ መፈረም በመቻሉ ይህ ደስታ ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለሁሉም የተፋሰሱ አባል ሀገራትም ጭምር ከፍተኛ ደስታ ነውና እንኳን ደስ አላችሁ ለማለት እወዳለሁ።

# የግብር ገቢ-እያደገ የመጣና ገና ብዙ ማደግ ያለበት!

**ኃይሉ ሣህለድንግል**

የገቢዎች ሚኒስቴር ባለፉት ዓመታት እንዳደረገው ሁሉ ባለፈው ሳምንትም ስድስተኛውን ዙር የታማኝ ግብር ከፋዮች የእውቅና መርሀ ግብር አካሂዷል፡፡በዚህም 66 ኩባንያዎች በፕላቲኒየም፣ 165 ኩባንያዎች በወርቅ፣ 319 ኩባንያዎች ደግሞ የብር ሜዳሊያ ተሸላሚ ሆነዋል፤ ባለፉት አራት ዓመታት በታማኝነት ከፍተኛ ግብር በመክፈላቸው ተሸላሚ የሆኑ 20 ኩባንያዎች ደግሞ ልዩ ተሸላሚ በመባል ተሸልመዋል።

በዚህ መድረክ ላይ የተገኙት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የታማኝ ግብር ከፋዮች ሽልማት ተቋዳሾችን እንኳን ደስ አላችሁ ብለዋቸዋል፡፡«የዜግነት ግዴታችሁን ለመወጣት ያደረጋችሁት ቁርጠኝነት ምስጋና ሊቸረው ይገባል» ሲሉም አስታውቀዋል፡፡ግብር መክፈል ለታማኝ ግብር ከፋዮች ብቻ ሳይሆን ለመጪው ትውልድ የሚተርፍ ዐሻራ ማኖር ነው ሲሉ ጠቅሰው፣ ታማኝ ግብር ከፋዮች የኢትዮጵያን ክብር የሚያስጠብቁና ብልጽግናዋ እውን እንዲሆን የሚተጉ መሆናቸውን አስታውቀዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በሀገሪቱ ግብር የመሰብሰብ መጠንና የግብር ከፋዮች ቁጥር እያደገ መሆኑንም ጠቅሰው፣ ይህን ገቢ ይበልጥ ለማሳደግና የሀገርን ግንባታ ለማፋጠን በታማኝነት ግብር የመክፈል ባሕል እየዳበረ ሊመጣ እንደሚገባም አስገንዝበዋል፡፡በግብር አሰባሰቡ ላይ እየታዩ ያሉ አዎንታዊ ለውጦች ማስቀጠል እንደሚያስፈልግም አመልክተዋል፡፡በመንግሥት በኩል የገቢ አሰባሰብ አሰራር ማሻሻያን በማጠናከር ሌብነትን በመቀነስና በቴክኖሎጂ የታገዘ አሰራርን በማስፋፋት ገቢ የመሰብሰብ አቅምን ለማሳደግ እንደሚሰራ አስታውቀዋል፡፡

በቅርቡ በተካሄደው 6ኛው የሕዝብ ተወካዮችና የፌዴሬሽን ምክር ቤቶች 4ኛ ዓመት የሥራ ዘመን መክፈቻ ላይ የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ሆነው የተሾሙት አምባሳደር ታዬ አፅቀ ሥላሴ በወቅቱ ባደረጉት ንግግር የሀገር ውስጥ ገቢን ማሳደግ አስፈላጊነትን አጽንኦት ሰጥተው ጠቅሰዋል፡፡ወደ ግብር መረቡ ያልገቡትን እንዲገቡ በማድረግ እንዲሁም አዳዲስ የታክስ ዓይነቶችን በመተግበር፣ የታክስ አስተዳደር ሥርዓትን በማዘመንና ታክስ በመሰብሰብ ሂደት የሚወጣውን ወጪ ውጤታማ በማድረግ፣ በፌዴራል ደረጃ ያሉትን የታክስ ማሻሻያ ሥራዎች ወደ ክልሎችም በማውረድና በክልል ደረጃ የሚሰበሰበውን ገቢ በማሳደግ የመንግሥትን የአገልግሎት አሰጣጥ በማዘመንና በማሻሻል፣ ታክስ ካልሆኑ ምንጮች የሚሰበሰበውን ገቢ ለማሳደግ ርብርብ እንደሚደረግ አስታውቀዋል፡፡

ከግብር የሚገኘውን ገቢ የመሰብሰብ እቅምን በማሳደግ አስፈላጊነት ላይ መንግሥት ባለፉት ዓመታት ባከናወናቸው ተግባሮች ለውጥ ማምጣት እንደተቻለ ይታወቃል፡፡የገቢዎች ሚኒስቴር መረጃ እንዳመለከተው፤ ሚኒስቴሩ በ2015 በጀት ዓመት 442 ቢሊዮን ብር የሰበሰበ ሲሆን፣ ይህ አሀዝ በ2016 በጀት ዓመት 512 ቢሊየን ብር ደርሷል፡፡የ70 ቢሊየን ብር ጭማሪ አለው ማለት ነው፡፡ ቀደም ባሉት ዓመታት የተሰበሰበው ገቢም እንዲሁ እያደገ ነው የመጣው፡፡

መንግሥት በየዓመቱ ከፍተኛ መጠን ያለው ገቢ በመሰብሰቡም ሆነ ገቢ የመሰብሰብ አቅሙ እያደገ በመምጣቱ አልተኩራራም፡፡ለተገኘው ለውጥ በየዓመቱ እውቅና እየሰጠ ግብር የመሰብሰቡን አቅም እያሳደገ የበለጠ ገቢ መሰብሰብ ላይ በትኩረት እየሰራ ነው፡፡

**መንግሥት በየዓመቱ ከፍተኛ መጠን ያለው ገቢ በመሰብሰቡም ሆነ ገቢ የመሰብሰብ አቅሙ እያደገ በመምጣቱ አልተኩራራም፡፡ለተገኘው ለውጥ በየዓመቱ እውቅና እየሰጠ ግብር የመሰብሰቡን አቅም እያሳደገ የበለጠ ገቢ መሰብሰብ ላይ በትኩረት እየሰራ ነው**

በሀገር ደረጃ ሰሞኑን የተካሄደውን እውቅናና በዚያው መድረክ ላይ ከግብር የሚገኘውን ገቢ ለመሰብሰብ የሚደረገው ጥረት ተጠናክሮ እንደሚቀጥል የተገለጸበት ሁኔታ እንዲሁም ፕሬዚዳንቱ በገቢ አሰባሰቡ ላይ ያስቀመጡት አቅጣጫም ይህንኑ ያመለክታሉ፡፡ ሽልማቱ ተሸላሚዎቹ ብቻ እንዲበረታቱ የተደረገበት ሳይሆን ሌሎች ታማኝ ግብር ከፋዮች እንዲፈጠሩ የተሰራበትም ነው፡፡

የታማኝ ግብር ከፋዮች የእውቅና መርሀ ግብሩ ግብር ከፋዮቹ በታማኝነት ግብር በመክፈላቸው የተመሰገኑበትና የተሸለሙበት ነው፡፡ከእዚህ ሽልማት ሌሎች ትምህርት እንዲቀስሙ መልእክት የተላለፈበትም ነው፡፡ በሁሉም የግብር ከፋይነት ደረጃ ግብር የሚከፍሉ አካላት ከዚህ አርአያነት ያለው ተግባር በመማር ገቢ ሳይሰውሩ ያገኙትን ገቢ ታሳቢ ያደረገ ግብር ወደ መክፈል እንዲገቡ፣ ሌሎች ግብር የማይከፍሉ አካላትም ካደፈጡበት ወጥተው ግብር የመክፈል የዜግነት ግዴታቸውን እንዲወጡ የበኩሉን ሚና ይጫወታል፡፡ይህ ሲሆን ኢኮኖሚው ከሚያመነጨው ገቢ የሚጠበቀውን ግብር መሰብሰብ መቻል ይጀመራል፡፡

መንግሥት እየተሰበሰበ ባለው ገቢ ረክቶ አልተቀመጠም፡፡ከግብር የሚሰበሰበው ገንዘብ በብዙ ቢሊየን ብር እያደገም መሰብሰብ ያለበትን ያህል ገቢ እንዳልተሰበሰበ ሁሌም ይገልጻል፡፡የዚህ ምክንያቱ ደግሞ ብዙ ነው፤ ሀገር ከሚያስፈልጋት ሀብትና ኢኮኖሚው ከሚያመነጨው ሀብት አንጻር ሲታይ እየተሰበሰበ ያለው ገቢ በቂ አለመሆኑ አንዱ ነው፡፡ገቢ የመሰብሰብ ሥራው በላቀ መልኩ ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት ታምኖበት ሲሰራ የቆየውና ተጨባጭ ለውጥ እየታየ ያለውም በእዚህ መልኩ በመሰራቱ ነው፡፡

በቀጣይም በዚሁ መልኩ እንደሚሰራ መንግሥት አቅጣጫዎችን አስቀምጧል፡፡ለእዚህም ግብር በመሰብሰብ በኩል ውጤታማ መሆን ያስቻሉትን ይዞ መቀጠል አንድ ነገር ሆኖ፣ ውጤታማ ያልሆኑት ውጤታማ ሊሆኑ የሚችሉበትን መንገድ በመፈለግ መሥራት፣ አዳዲስ መንገዶችንም መቀየስ ያስፈልጋል፡፡

ግብር መረብ ውስጥ ከገቡት የሚሰበሰበው ግብር ኢኮኖሚያቸው ከሚያመነጨው ሀብት አኳያ ሲታይ በቂ እንዳልሆነ እየተገለጸ ነው፡፡ በተለይ በንግዱ ማህበረሰብ ዘንድ ገቢን አሳውቆ ግብር በመክፈል በኩል ሊጠቀሱ የሚችሉ ታማኝ ግብር ከፋዮች ቢኖሩም፣ ጥቂት የማይባሉ የንግዱ ማህበረሰብ አባላት ገቢ የሚደብቁበት ሁኔታ እንዳለም ይታወቃል፡፡እነዚህ ግብር ከፋዮች ታማኝ ግብር ከፋይ እንዲሆኑ ማድረግም ላይ በትኩረት መሥራት ይኖርበታል፡፡

ግብር ከፋዮች ታማኝ እንዳይሆኑ ያደረጋቸው ምንድነው ብሎ አጥንቶ ርምጃ መወሰድ ይገባል፡፡ይሄኔ ግብር ሰብሳቢው አካል በሚያስማራቸው ሠራተኞች ታማኝነት ላይ የመሥራት አስፈላጊነት ይመጣል፡፡ብዙ ነገሮች እዚህ አካባቢ ሲበላሹ ነው የኖሩት፡፡ይህን ጉያ ውስጥ ይዞ ስለግብር በአግባቡ አለመሰብሰብ መናገር ትክክል አይሆንም፡፡

በእነዚህ ሁለት ወገኖች መካከል በሚፈጸም መሞዳሞድ ሀገር ብዙ ገቢዋን ስትቀማ ኖራለች፡፡ብዙ ሚሊየን ብር ግብር እንዲከፈል እየጠየቁ ይህን ያህሉን ሚሊየን ብር ከሰጠኸኝ ይህን ያህሉን አቅንስልሃለሁ ብለው ቀብድ ሲቀበሉ የተያዙ ግብር ተማኞች እንዳሉ ይታወቃል፡፡ሌሎች በርካታ የመሞዳሞድ ዓይነቶችም እንዳሉ ይታወቃል፡፡እንዲህ ዓይነቱን ሕገወጥ ድርጊት የሚፈጽሙ አካላትን አጥምዶ መያዝ፣ የሚወሰድባቸው ርምጃም ጠንካራና አስተማሪ እንዲሆን ማድረግ እንዲሁም ርምጃው ሌሎች እንዲማሩበትም በመገናኛ ብዙሃንንና በመሳሰሉት ላይ መገለጽ ይኖርበታል፡፡

አዳዲስ የግብር ዓይነቶችን ማምጣት ወይም ወደ ግብር መረቡ ያልመጡትን ማምጣት ሌላው በሰፊው ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡ርግጥ ነው ቀደም ሲል ግብር የማይከፍልባቸው ወይም ጥቂት ግብር ብቻ ይከፈልባቸው የነበሩና ከጥቂት ዓመታት ወዲህ ግብር ይከፍልባቸው የጀመሩ እንደ መኖሪያ ቤት ግብር ያሉት አዳዲስ የግብር ዓይነቶች ማምጣታቸው አበረታች ተግባር ነው፡፡ከዚያም ቀደም ብሎ የቤት ባለቤቶች ከሚያከራዩት ቤት ግብር መሰብሰብ መጀመሩ ይታወቃል፡፡

በዚህ ዓይነት መልኩ ግብር ሊሰበሰብባቸው የሚችሉ በርካታ የንግድ፣ የአገልግሎትና የመሳሰሉት ሥራዎች እንዳሉ ይታወቃል፡፡እነዚያ ላይም መድረስ ያስፈልጋል። ሁለት ሺ ብር ደሞዝ የሚከፈላቸው የመንግሥት ሠራተኞች ግብር እየከፈሉ ብዙ ሺ ብር ገቢ የሚያስገኙ ሥራዎችን የሚሰሩ ምንም ዓይነት ግብር የማይከፍሉበት ሁኔታ ብዙ ነው፡፡

ከዚህ መሰሎቹ ገቢዎች ላይ ግብር መሰብሰብ ላይ ገና ብዙም ባልተሰራበት ሁኔታ ሌሎች አዳዲስ ግብር ሊሰበሰብባቸው የሚችሉ የሥራ ዘርፎች እየተወለዱ ናቸው፡፡ ዘመኑ የዲጂታል እንደመሆኑ በቴክኖሎጂ መኖሪያ ቤት ቁጭ ተብሎ የሚሰሩ ሥራዎች ጥቂት እንዳልሆኑ ይነገራል፡፡እንደዚህ ዓይነቶቹ ሥራዎች ባደጉትና በማደግ ላይ ባሉት ሀገሮች ተለምደዋል፡፡ ሥራዎቹ ባህር ማዶ ድረስ የተዘረጉና የውጭ ምንዛሬ የሚገኝባቸውም ናቸው፡፡ዜጎች በእዚህ ዓይነቶቹ ሥራዎች መሰማራታቸው ሊበረታታ ይገባል፡፡ከዚህ ገቢ ለሀገራቸው ግብር ሊከፍሉ የሚችሉበት ሁኔታ መፈጠር ግን ይኖርበታል፡፡ ለእዚህም መንግሥት ባደጉት ሀገሮች እንዲህ ዓይነቱ ሥራ እንዴት ክትትል እንደሚደረግበትና ግብር እንዲከፈልበት ማድረግ እንደሚቻል አጥንቶ በኢትዮጵያም መተግበር ይገባል፡፡

እነዚህን ግብር ሊሰበሰብባቸው የሚችሉ የሥራ ዘርፎች አጥንቶ፣ አሰራር ቀይሶ ግብር እንዲከፍሉ ማድረግ ላይ በስፋትና በትኩረት መሥራት ሲገባ ከግብር የሚገኝ ገቢን ለማሳደግ በስፋት የሚሰራበት ሥራ አንዴ ግብር መረብ ውስጥ በገቡት ላይ ጭማሪ ማድረግ ነው፡፡አንዱ ነጋዴ ተሞዳሙዶ ዝቅተኛ ግብር እንዲከፍል እየተደረገ፣ ሌላው ደግሞ ግብር መረብ ውስጥ እንዲገባ ባልተደረገበት ሁኔታ ግብር መረብ ውስጥ የገባው ነጋዴ ላይ ከልክ ያለፈ ጭማሪ እንዲከፍል የሚደረግ ከሆነ አሰራሩ ፍትሃዊ ካለመሆኑ በተጨማሪ ታማኝ ግብር ከፋዮችን ማማረርም ይሆናል፡፡ በዚህች ሀገር እየሆነ ያለው ይሄው ነው፡፡

በዚህ ዓይነቱ የግብር አሰባሰብ ግብር ከፋዩ ህብረተሰብ ክፉኛ እየተጎዳ ነው፡፡እንዲህ ዓይነቱ ግብር ከፋይ ላይ መንግሥት ብቻም ሳይሆን የሚበረታው ግብር ተማኞችም ናቸው፡፡እነሱ ይብሳሉ፤ ጥቂት አይደሉም፡፡ ጥቂት ቢሆኑ ጩኸቱ ብዙ አይሆንም ነበር፡፡

እነዚህ ግብር ከፋዮች ግብር ሲጨመርባቸው ወይ አቤቱታ ያቀርባሉ፤ አልያም ይከፍላሉ፡፡ሶስተኛው አማራጫቸው ከግብር ተማኞች ጋር ተሞዳሙደው ግብሩን ማስቀነስ ነው፡፡ይህ ችግር የነበረ፣ ያለ፣ ትኩረት ተሰጥቶ ካልተሰራበት በቀጣይም ሊኖር የሚችል የገቢ ጠንቅ ነው፡፡

በግብር ከፋዩ ላይ በየጊዜው የሚጫን ተጨማሪ ክፍያ ሀገሪቱን ግብር ተጨመረብኝ እያለ የሚያማርር እንጂ ግብር እንድከፍል ተጠየቅሁኝ የሚል ብዙም የማይሰማባት ሀገር እንድትሆን አድርጓታል፡፡ይህ በስፋት እየተፈጸመ ባለበት ሁኔታ የግብር መሰረት ማስፋት ሥራ ተሰርቶበታል የሚያሰኝ ሁኔታ አለ ብሎ ለመናገር አያስደፍርም፤ የግብር መሰረት ሲሰፋም ነው የግብር ገቢ እየጨመረ የሚመጣው፡፡ የግብር መረብ እንዲሰፋ ሲደረግም የመጀመሪያው አላማ መሆን ያለበት ወደ ግብር መረብ ማምጣት መሆን ነው ያለበት፡፡ተያዘ ተብሎ እዚህም ላይ ግብር መቆለል ተገቢ አይደለም፤ ቀስ በቀስ ግብሩን መጨመር ይቻላል፡፡

በዜጎች ዘንድም ስር የሰደደ የግንዛቤ እጥረት ችግር አለ፡፡ግብር ለአንድ ሀገር ምጣኔ ሀብታዊና ማህበራዊ ተግባሮች ወሳኝ መሆኑ አያጠያይቅም፡፡መንገዱም፣ ትምህርቱም ጤናውም ወዘተ ያለ ግብር ሊሰራ፣ ሊታደስ፣ የመንግሥት ሠራተኛውም ባለደሞዝ ሊሆን አይችልም። በመሰረቱ ዝም ብሎ መንገድ፣ ትምህርት ቤት፣ የጤና ተቋም አይጠየቅም፤ በደረቁ የውሃ አገልግሎት፣ የኤሌክትሪክ አገልግሎት፣ ወዘተ መጠየቅ የለበትም፡፡ በኛ ሀገር ግን እየሆነ ያለው ይሄ ነው፡፡ ግብር እንዲከፍሉ ሲጠየቁ ወገቤን ማለት፤ ግብር ሲጨመርብም እንዲሁ መታመም፤ መሰረተ ልማት ግን መጠየቅ፡፡

ግንዛቤው እያለም በግብር ጉዳይ ላይ ድብብቆሽ መጫወቱ ብዙም ነው፡፡የኢኮኖሚ እንቅስቃሴው ግብር እንዲከፈል የግድ የሚል ሆኖ እያለ፣ ሀገር ወደ ልማት እንድትገባ አስቀድሞ መሠረተ ልማት መዘርጋት ያለበት መሆኑን እየታወቀ የግብር ነገር ሲነሳ ፊት ማዞር ይስተዋላል፡፡«አውቆ የተኛ ቢቀሰቅሱት አይሰማም» እንዲሉ የግብር መክፈልን ፋይዳ እየተገነዘቡ ግብር ለመክፈል ምንም ዓይነት ፍላጎት የሌላቸው፣ ፍላጎት እንዲያድርባቸው በተለያዩ መንገዶች ተቀስቀሰውም፣ ማሳሰቢያ ተሰጥቷቸውም ወደ ግብር መክፈሉ ያልገቡ ጥቂት አይደሉም፡፡ለእዚህም ነው መንግሥት በእዚህ ላይ በስፋት እንዲሰራ እየጎተጎተ ያለው፡፡

በዚህች ሀገር ግብር መክፈል ሲገባቸው ጨርሶ የማይከፍሉ ሞልተዋል፡፡እነዚህ በአነስተኛ ንግድ ሥራዎች፣ በድርጅቶችና በመሳሰሉት ተቀጥረው የሚሰሩ ነገር ግን ምንም ዓይነት ግብር የማይከፍሉ፣ ቤት እያከራዩ የኪራይ ግብር የማይከፍሉ፣ በአንድ ምርት የንግድ ፈቃድ አውጥተው በተጓዳኝ ብዙ ነገሮችን የሚነግዱ፣ ወዘተ፣ ግብር ግን የማይከፍሉ በርካታ ናቸው፡፡

መክፈል ያለባቸውን ያህል የማይከፍሉትም ጥቂት አይደሉም፡፡እነዚህ ግብር ከፋይ ተብዬዎች ብዙ ገቢ እያገኙ ትንሽ እንዳገኙ አርገው ሂሳብ አሰርተው በማቅረብ መንግሥትን ያጭበረብራሉ፡፡ይህ ዓይነቱ ሕገ ወጥነት በተላልቆቹ የንግድ ድርጅቶች ሳይቀር የተለመደ ነው፡፡የሚያገኙት ገቢና የሚከፍሉት ግብር ጨርሶ እንደማይደራረስ ይነገራል፡፡

በተጨማሪ እሴት ታክስ የሚከፈል ገንዘብ መንግሥት ዘንድ የማይደርስበት ሁኔታም ብዙ ነው፡፡ደረሰኝ ሳይቀበሉ ገንዘብ አይክፈሉ ቢባልም ክፍያው ያለ ደረሰኝ የሚፈጸምበት ሁኔታ እጅግ ብዙ ሆኗል፡፡ነጋዴዎቹ ደረሰኝ አልቆረጡም ማለት ተጨማሪ እሴት ታክስ አልሰበሰቡም ማለት አይደለም፡፡ሰብስበው ለራሳቸው ያውላሉ፡፡ በዚህም ለመንግሥት ገቢ መደረግ ያለበት ሀብት በከፍተኛ ደረጃ ለሕገ ወጦች እየዋለ ይገኛል፡፡

ሀገሪቱ የምትሰበስበውን ገቢ ከትሪሊየን ብር በላይ ለማድረስ ታቅዷል፡፡ይህን ሁሉ ለማሳካት ሙሉ አቅምን ግብር መሰብሰብ ላይ ማድረግ ይገባል፡፡ በሀገሪቱ ግብር በስፋት ለመሰብሰብ የሚያስችል ምቹ ሁኔታ ስለመኖሩ በተደጋጋሚ ተገልጿል፡፡በአጭበርባሪዎች ወይም ገቢ ደባቂዎች የተነሳ ያልተሰበሰበ፣ አዳዲስ የገቢ ምንጮችንና ከእነዚህ ምንጮች ገቢ እንዴት መሰብሰብ እንደሚቻል ባለማወቅ ሳቢያ ያልተሰበሰበ ሀብት ብዙ ነው፡፡

ከሌላ ነገር አይደለም ግብር መሰብሰብ የተፈለገው። ይህን ሀብት ለመሰብሰብ የሚያስችል አቅም መፍጠር ከመንግሥት ይጠበቃል፡፡መንግሥት በተደጋጋሚ እንደሚገልጸውም ዘንድሮም እንደገለጸው ይህን አቅም ማሳደግ ላይ ይሰራል፤ ግብር የመሰብሰብ አቅም የማሳደጉ ሥራ የራሱን የግብር ቀበኞች ቆርጦ እስከ መጣል ገቢ ሰዋሪ እንዳይኖር እስከ ማድረግ መዝለቅ የሚደርስ መሆን ይኖርበታል፡፡

ሀገራችን በአፍሪካ ዝቅተኛ የግብር ገቢ ከሚሰበስብባቸው ሀገሮች መካከል መሆኗ በተደጋጋሚ ይገለጻል፡፡ በግብር አሰባሰቡ እነዚህ ሀገሮች ላይ መድረስ ባይቻል እንኳ ለመቀራረብ መሰረት ይኖርበታል፡፡ የእነዚህ ሀገሮች ግብር አሰባሰብ ግብር በሚገባ ለመሰብሰብ ሌላ መነሻ ሆኖ ማገልገል ይችላልና ተሞክሯቸውን ቀስሞ መተግበርም ያስፈልጋል፡፡

ሀገር ለምታካሂደው ልማትና የመሳሰሉት ተግባሮች የውጭ ገንዘብ ሊገኝ ይችላል፡፡ ዋናው ሀብት ግን በሀገር የሚሰበሰበው ገቢ መሆኑ ስለመሆኑ ለዜጎች ማስተማር ላይ አጥብቆ መስራት ይኖርበታል፡፡ ከውጭ የሚገኝ ሀብት አስተማማኝ ሊሆን ስላለመቻሉ ያለፉት ዓመታት የሀገራችን ተሞክሮ ያመለክታል፡፡

አስተማማኝ ገቢ ተብሎ ሊወሰድ የሚችለው ኢኮኖሚው ከሚያመነጨው ሀብት ሊሰበሰብ የሚችለው ገቢ ብቻ ነው፡፡ ይህን ገቢ ዜጎችን በማስተማር፣ በማስገንዘብ፣ ግብር በታማኝነት ለከፈሉት ደግሞ በቅርቡ እንደተደረገው እውቅና በመስጠት ፣ ይህን እውቅና በየደረጃው አውርዶ ከትንሽ ገቢ ጥሩ ግብር ለከፈሉትም እውቅና በመስጠት ዜጎች በግብር አሰባሰቡ አምነው፣ ግብር መክፈል የዜግነት ግዴታ መሆኑን ተረድተው ግብር በታማኝነት የሚከፍሉበትን አሰራር መዘርጋት ያስፈልጋል፡፡

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

## የቻይናውያን ሰፊ የኢንቨስትመንት ተሳትፎ ማሳያው ኢንዱስትሪ ፓርክ

አንተነህ ቸሬ




የኢትዮጵያ ሰላምና መረጋጋት፣ በመሠረት ልማት ዝርጋታ ዘርፍ የተከናወኑ ውጤታማ ተግባራት፣ የኢንቨስትመንት ዘርፍ ማበረታቻዎች እንዲሁም ሀገሪቱ ያላት እምቅ የተፈጥሮ ሀብት እና ሰፊ የገበያ እድል፤ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን በመሳብ በአፍሪካ ደረጃ ቀዳሚ ከሚባሉ ሀገራት መካከል አንዷ እንድትሆን አስችለዋታል። ይህም ለኢንቨስትመንት ዘርፍ ማደግ ዓይነተኛ ሚና የተጫወተ ሲሆን፣ ለሀገሪቱ የምጣኔ ሀብት እድገትም ትልቅ ድርሻ አበርክቷል።

የሀገሪቱ የኢንቨስትመንት ዘርፍ በየጊዜው ከፍተኛ መሻሻልና እድገት ካስመዘገቡ ዘርፎች መካከል አንዱ ነው። ይሁን እንጂ ባለፉት ጥቂት ዓመታት በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች የተፈጠሩት የፀጥታ ችግሮች በዓለም አቀፍ ደረጃ ከተፈጠሩት የኮቪድ ወረርሽኝ፣ የምጣኔ ሀብት ቀውስና ጦርነቶች ጋር ተደምረው በሀገሪቱ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴዎች ላይ ተፅዕኖ አሳድረው ነበር።

በመንግሥት የተወሰዱ ልዩ ልዩ ርምጃዎች የኢንቨስትመንት ዘርፉ መልሶ እንዲያንሰራራ አስችለዋል። በኢንቨስትመንት ዘርፉ ላይ ጫና አሳድረው የነበሩ ችግሮች ደረጃ በደረጃ መፍትሔ እያገኙ በመምጣታቸው በዘርፉ መነቃቃት እየታየ እንደሚገኝ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ገልጿል። ለአብነት ያህልም ባለፈው የበጀት ዓመት ሦስት ነጥብ 82 ቢሊዮን ዶላር የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት መሳብ ተችሏል። 329 አዳዲስ የኢንቨስትመንት ፈቃዶች ተሰጥተዋል። ከሁሉም ኢንዱስትሪ ፓርኮች 115 ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ዶላር የውጭ ምንዛሬ ተገኝቷል። ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ለመግባት ፍላጎት ካሳዩ 70 ድርጅቶች ጋር የመግባቢያ ስምምነቶች ተፈርመዋል። በዘጠኝ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ በሚገኙ 205 ፕሮጀክቶች ላይ የክትትልና ቁጥጥር ሥራዎች ተከናውነዋል።

ወቅታዊ ሀገራዊና ዓለም አቀፍ ነባራዊ ሁኔታን ከግምት ውስጥ ባስገባና የሀገርን ጥቅም በሚያስጠብቅ መልኩ የሁለትዮሽ የኢንቨስትመንት ስምምነቶች ክለሳዎች ተጠናቀው አዳዲስ ድርድሮች ተደርገዋል። ከአዳዲስ ቀጣናዊና ክልላዊ የንግድና ኢንቨስትመንት እድሎች ተጠቃሚ ለመሆን የሚያስችሉ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ተከናውነዋል። የኢትዮጵያ የኢንቨስትመንት አቅሞችና መልካም እድሎች በበርካታ ዓለም አቀፍ የኢንቨስትመንት ፎረሞችና ኤግዚቢሽኖች ላይ እንዲተዋወቁ ተደርጓል። ከዚህ በተጨማሪም በዘንድሮው የበጀት ዓመት አራት ነጥብ አምስት ቢሊዮን ዶላር የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ለመሳብ እንዲሁም ለ341 ፕሮጀክቶች (ከኢንዱስትሪ ፓርኮች ውጭ) አዳዲስ የኢንቨስትመንት ፈቃዶችን ለመስጠት ታቅዷል።

ኢንቨስትመንትን ለማሳደግ የሚደረጉ ጥረቶች በመቀጠላቸው፣ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት (Foreign Direct Investment - FDI) እየጨመረ ይገኛል። ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚገቡ የሀገር ውስጥና የውጭ ባለሀብቶች ቁጥር በከፍተኛ ደረጃ አድጓል። በኢንቨስትመንት ሥራዎች ላይ የተሰማሩ ድርጅቶች ለምርት እድገት፣ ለውጭ ምንዛሬ ግኝት፣ ለሥራ እድል ፈጠራ፣ ለቴክኖሎጂ ሽግግርና ለገበያ ትስስር ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያደረጉ ይገኛሉ።

የኢትዮጵያን መዋቅራዊ የምጣኔ ሀብት ሽግግርን እውን ለማድረግ አስተዋጽኦ ይኖራቸዋል ተብለው ትኩረት ከተሰጣቸው ተግባራት መካከል የኢንዱስትሪ ፓርኮች (Industrial Parks) ልማት አንዱ ነው። የኢንዱስትሪ ፓርኮች የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት የመሳብ፣ የሥራ እድል ፈጠራን የማስፋት እና የቴክኖሎጂ ሽግግርን እውን የማድረግ ዋና ዋና መሠረታዊ ተልዕኮዎች አሏቸው። ፓርኮቹ በሚገነቡባቸው አካባቢዎች ለሚኖረው የኅብረተሰብ ክፍል ሥራ በመፍጠርና ከአካባቢ ጋር ተስማሚ የሆነ የሥራ ከባቢ እውን በማድረግ ለሀገራዊ የምጣኔ ሀብት እድገት ትልቅ አስተዋጽኦ ይኖራቸዋል።

በመንግሥት ተገንብተው በኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽንና በክልል መንግሥታት ከሚተዳደሩት 12 የኢንዱስትሪ ፓርኮችና የድሬዳዋ ነፃ የንግድ ቀጣና በተጨማሪ በግል ባለሀብቶች የተገነቡና የሚተዳደሩ የኢንዱስትሪ ፓርኮችም በተለያዩ የኢትዮጵያ አካባቢዎች ይገኛሉ። ከእነዚህ የግል ኢንዱስትሪ ፓርኮች መካከል አንዱ «ኢስተርን ኢንዱስትሪ ፓርክ» (Eastern Industry Park) ነው። ኢንዱስትሪ ፓርኩ ዱከም አካባቢ የሚገኝ ሲሆን፣ በፓርኩ ውስጥ 153 ኩባንያዎች በምርት ሥራዎች ላይ ተሰማርተው ይገኛሉ። ከኩባንያዎቹ መካከል 95 በመቶ የሚሆኑት በቻይናውያን ባለሀብቶች ባለቤትነት የተያዙ ሲሆኑ፣ ቀሪዎቹ ደግሞ የህንድ፣ የእንግሊዝና የሌሎች ሀገራት ኩባንያዎች ናቸው። እነዚህ አምራቾች በሥራ እድል ፈጠራ፣ በውጭ ምንዛሪ ግኝት እንዲሁም በቴክኖሎጂና እውቀት ሽግግር ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከቱ ይገኛሉ።

በፓርኩ ውስጥ ከሚገኙ ፋብሪካዎች መካከል አንዱ «ዲ ዩዋን ሴራሚክስ» (Di Yuan Ceramics) ነው። የፋብሪካው ሥራ አስኪያጅ ሹ ቦ ፋብሪካው በ50 ሚሊዮን ዶላር ኢንቨስትመንት ከሰባት ዓመታት በፊት እንደተቋቋመ ጠቁመው፣ የግድግዳና የወለል ሴራሚክስ ምርቶችን እንደሚያመርት ይገልጻሉ። ለ800 ኢትዮጵያውያንና ለ50 ቻይናውያን የሥራ እድል ፈጥሯል። ኢትዮጵያውያን የክህሎትና የቴክኖሎጂ ሽግግር ተጠቃሚ እንዲሆኑ እያደረገ እንደሚገኝም ያስረዳሉ። የመንግሥት ድጋፍ ለፋብሪካው ሥራ መቃናት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳለውም ሥራ አስኪያጁ ይናገራሉ።

የ«ሁዋጂያ አሉሚነም ኢንዱስትሪ» (Huajia Aluminum Industry PLC) ዋና ሥራ አስኪያጅ ደቪድ ዡ እንደሚናገሩት፣ ፋብሪካው በ181 ሚሊዮን ብር የኢንቨስትመንት ካፒታል ከስምንት ዓመታት በፊት ሥራ የጀመረ ሲሆን፣ ከ170 በላይ ለሚሆኑ ኢትዮጵያውያን የሥራ እድል ፈጥሯል። ፋብሪካው 16 ዓይነት የአሉሚንየም ፕሮፋይል ምርቶችን (Aluminum Profiles) አምርቶ ለሀገር ውስጥ ገበያ እያቀረበ ይገኛል። በኢንዱስትሪ ፓርኩ ውስጥ ያለው የፋብሪካዎች ኢንቨስትመንት የኢትዮ-ቻይና የኢኮኖሚ ትስስር እንዲጠናከርና የሁለቱ ሀገራት መልካም ግንኙነትም ለፋብሪካዎቹ ውጤታማነት አስተዋጽኦ እያበረከተ እንደሚገኝ ያስረዳሉ። የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽንም ከመጀመሪያው ጀምሮ ለፋብሪካው ዘርፈ ብዙ ድጋፎችን ሲያደርግ እንደቆየና ፋብሪካው ከአካባቢው ኅብረተሰብ፣ ከክልሉና ከፌደራል መንግሥት ጋር በትብብር እንደሚሰራም ይገልፃሉ።

የ«ሊንደ ኢትዮጵያ» ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ (Linde Ethiopia Garment PLC) ዋና ስራ አስኪያጅ ጂ ዩፋን በበኩላቸው፣ ፋብሪካው የተለያዩ ብራንድ ያላቸውን የጨርቃ ጨርቅ ምርቶችን አምርቶ ለገበያ እንደሚያቀርብ ጠቁመው፣ ከአንድ ሺ በላይ ኢትዮጵያውያን በፋብሪካው ተቀጥረው እየሰሩ እንደሚገኙ ይናገራሉ።

በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን የኢንዱስትሪ ፓርኮችና ፕሮሞሽን ዘርፍ ምክትል ኮሚሽነር ዶክተር ዘለቀ ተመስገን፣ «ኢስተርን ኢንዱስትሪ ፓርክ» በኢትዮጵያ ከሚገኙ የግል ኢንዱስትሪ ፓርኮች መካከል ተቀዳሚው መሆኑን ይገልፃሉ። እሳቸው እንደሚሉት፣ በፓርኩ ውስጥ ያሉት አምራቾች ለሥራ እድል ፈጠራ፣ ለወጪ ንግድ እና ለውጭ ምንዛሪ ግኝት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከቱ ይገኛሉ። በፓርኩ ውስጥ ባሉት ፋብሪካዎች ውስጥ አብዛኞቹ የምርት ሥራዎች የሚከናወኑት በኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች ነው። ይህም የክህሎትና የቴክኖሎጂ ሽግግር እቅዱ በጥሩ ሂደት ላይ የሚገኝ መሆኑን ያመለክታል። ከዚህ በተጨማሪም የውጭ ባለሀብቶች ከሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ጋር ትስስር ፈጥረው እየሰሩ ይገኛሉ።

እንደ ዶክተር ዘለቀ ማብራሪያ፣ በአሁኑ ወቅት ከስምንት ነጥብ አምስት ቢሊዮን ዶላር በላይ ካፒታል ያላቸው 3309 የቻይና የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች በኢትዮጵያ ይገኛሉ። እነዚህ ፕሮጀክቶች ከ325ሺ በላይ ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ እድል ፈጥረዋል። የቻይና ባለሀብቶች በኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ብዛት፣ በካፒታል አቅም፣ በሥራ እድል ፈጠራ እንዲሁም በቴክኖሎጂና እውቀት ሽግግር ቀዳሚውን ሚና እየተጫወቱ ይገኛሉ።

በፓርኩ ውስጥ ያሉት አምራቾች ለሥራ እድል ፈጠራ፣ ለወጪ ንግድ እና ለውጭ ምንዛሪ ግኝት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከቱ ይገኛሉ:: ከፓርኩ ፋብሪካዎች የአብዛኞቹ የምርት ሥራዎች የሚከናወኑት በኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች ነው

በኢንቨስትመንት ዘርፍ የተወሰዱ የኢኮኖሚ ማሻሻያ ርምጃዎች የዘርፉን እድገት ለማፋጠን አስተዋጽኦ እያደረጉ እንደሚገኙ የሚያስረዱት ምክትል ኮሚሽነሩ፣ ምቹ የሆነ የኢንቨስትመንት ከባቢ ለመፍጠር በማሰብ የሕግ ማሻሻያዎች ስለመደረጋቸው ይገልፃሉ። እንደሳቸው ገለፃ፣ የኢንቨስትመንት አዋጁ የኢንቨስትመንት ፍሰትን ሊያሳድግ በሚችል መልኩ ተሻሽሏል። የልዩ ኢኮኖሚ ቀጣና አዋጅም ጸድቋል። ይህን ተከትሎ ኮሚሽኑ መመሪያዎችን አዘጋጅቶ ወደ ሥራ ገብቷል።

በተሟላ የማክሮ-ኢኮኖሚ ማሻሻያው የሚተገበሩ አሰራሮች ለውጭና ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ምቹ የኢንቨስትመንት እድሎችን የሚፈጥሩ እንደሆኑ የሚገልጹት ዶክተር ዘለቀ፣ የዘንድሮው የበጀት ዓመት የመጀመሪያ ሦስት ወራት የኢንቨስትመንት ፍሰት ካለፈው የበጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር በ12 በመቶ እድገት እንዳሳየ ይናገራሉ።

የኢንቨስትመንት ከባቢውን የበለጠ ምቹ ለማድረግ የተወሰዱ ርምጃዎች ለዚህ እድገት አስተዋጽኦ አበርክተዋል። ኮሚሽኑ ከሚያከናውናቸው ሥራዎች መካከል አንዱ ለባለሀብቶች ክትትልና ድጋፍ ማድረግ ነው። የክትትልና ድጋፍ ሥራዎቹ ኢንቨስተሮች ሥራቸውን እንዲያስፋፉ እና ሌሎች ባለሀብቶችም ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጡ ስለማድረጋቸውም ያስረዳሉ።

«በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ በምስራቅ አፍሪካ ተቀዳሚ የውጭ ኢንቨስትመንት መዳረሻ ናት። ይህም ቢሆን ኢትዮጵያ ካላት እምቅ አቅም አንፃር ተጨማሪ ኢንቨስትመንቶችን ለመሳብ መሰራት ያለባቸው ብዙ ሥራዎች አሉ። የሀገሪቱ አቅም በመንግሥት በኩል እየተወሰዱ ካሉ የኢኮኖሚ ማሻሻያዎች ጋር ሲደመሩ በዓለም አቀፍ ደረጃም ተመራጭ የኢንቨስትመንት መዳረሻ እንድትሆን ያስችላታል። በተለያዩ ዘርፎች ያለው የኢንቨስትመንት ፍሰት በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ ነው። በተለይ ስትራቴጂካዊ ተብለው በተለዩት ዘርፎች (በማኑፋክቸሪንግ፣ በግብርና፣ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ፣ በማዕድን፣ በቱሪዝም) ከፍተኛ የኢንቨስትመንት ፍሰት እየታየ ነው» ይላሉ።

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር ዳጋቶ ኩምቤ የኢንቨስትመንት ፍሰቱ እንዲጨምር ካደረጉት ምክንያቶች መካከል የሀገሪቱ እምቅ የኢንቨስትመንት አቅም እና የመንግሥት የኢኮኖሚ ማሻሻያ ርምጃዎች ተጠቃሽ እንደሆኑ ይገልፃሉ። አቶ ዳጋቶ እንደሚሉት፣ የኢኮኖሚ ማሻሻያ ርምጃዎቹ ባለሀብቶች ወደ ኢትዮጵያ መጥተው በኢንቨስትመንት ላይ እንዲሰማሩ እድል የሚፈጥሩ ናቸው።

«ባለሀብቶቹ ከውጭ ሲመጡ የተለያዩ አማራጮችን ታሳቢ አድርገው ነው። እኛ ደግሞ ባለሀብቶቹን ለመሳብ የተሻለ አማራጭ ማቅረብ አለብን። ከባለሀብቶች ከሚቀርቡ ጥያቄዎች መካከል አንዱ የውጭ ምንዛሪ እጥረት ነው። የውጭ ምንዛሪው ጥሬ እቃ ለመግዛትም ሆነ ሌሎች ግብዓቶችን ለማሟላት እጅግ አስፈላጊ ነው። በቅርቡ ሥራ ላይ የዋለው የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ማሻሻያ የውጭ ምንዛሪ እጥረትን ለማቃለል በጎ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ተስፋ ሰጭ ጅምሮች እየታዩ ነው» ይላሉ።

አቶ ዳጋቶ እንደሚገልፁት፣ የኢንቨስትመንት ከባቢን ለማሻሻል ከተወሰዱ ርምጃዎች መካከል አንዱ ከዚህ ቀደም ለውጭ ባለሀብቶች ዝግ የነበሩ የንግድ ዘርፎች ክፍት እንዲሆኑ መደረጋቸው ነው። በዚህም የውጭ ባለሀብቶች በወጪ፣ በገቢ፣ በጅምላና በችርቻሮ ንግድ ሥራዎች ላይ እንዲሰማሩ ተወስኗል። ከውሳኔው በኋላ ከሐምሌ 2017 ጀምሮ 72 ጥያቄዎች ቀርበዋል። ከእነዚህ መካከል 41 የሚሆኑት በገቢ እንዲሁም 31 ደግሞ በወጪ ንግድ ላይ ለመሳተፍ የቀረቡ ጥያቄዎች ናቸው። ፕሮፖዛል ካቀረቡ 22 ኩባንያዎች መካከል የ12 ኩባንያዎች ጥያቄ በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ይሁንታ አግኝቷል። ጥያቄያቸው ተቀባይነት ካገኘላቸው መካከል ስምንቱ የቻይና ኩባንያዎች ናቸው።

ፖለቲካ እና ወቅታዊ

# ጎሜ

# ኢትዮጵያን ያገለለ ውይይት ውጤቱ የዜሮ ድምር ነው

**እስማኤል አረቦ**

የኢትዮጵያን እድገትም ሆነ ውድቀት የሚወስኑ ሁለት ዋነኛ ጉዳዮች አሉ፡፡ አንደኛው በዓባይ ወንዝ ላይ ግድብ ገድቦ ኃይል ማመንጨት አንዱ ሲሆን ሌላኛው ደግሞ የባህር በር ጉዳይ ነው፡፡ሁለቱን በተናጥል እንመልከታቸው፡፡

በዓለም ላይ ወደ 276 የሚጠጉ ድምበር ተሻጋሪ ወንዞች አሉ። እነዚህን ወንዞች 145 የሚሆኑ ሀገራት ይጋራሉ። አንዳንድ ሀገራት ወንዞቹን የሚመለከት ሕግ አላቸው። አንዳንዶቹ ደግሞ የጋራ የውሃ አጠቃቀም ሕግ የላቸውም። ነገር ግን ሕጉ ያላቸው ሀገራት ውሃን ዘላቂና ፍትሐዊ በሆነ መንገድ ተጠቃሚነታቸውን እያረጋገጡ ይገኛሉ።

ወደ እኛ ጉዳይ ስንመጣ ግን በዓባይ ወንዝ አጠቃቀም ላይ በርካታ መሰናክሎች እና እልህ አስጨራሽ ክርክሮች ሲደረጉበት ቆይቷል፡፡ ኢትዮጵያ ከ86 በመቶ በላይ የናይል ወንዝ ምንጭ ብትሆንም በቅኝ ግዛት ውሎች የተነሳ መብቷ ለዘመናት ተጥሶ ኖሯል፡፡ ከ86 በመቶ በላይ የውሃ ባለቤት እየሆነች 1 በመቶ እንኳን የመጠቀም መብት አልነበራትም፡፡

ግብጽ እና ሱዳን የ1929 እና የ1959 የቅኝ ግዛት ውሎችን ምክንያት በማድረግ ከቀሪዎቹ የተፋሰሱ ሀገራት ጋር ውዝግብ ውስጥ ከገቡ ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡ ግብፅና ሱዳን የፈረሙት የቅኝ ግዛት ውሎች የዓባይን ውሃ ሀብት ከአሥር የተፈሰሱ ተጋሪ ሀገሮች ለሁለቱ ብቻ የሚያከፋፍል በመሆኑ ጊዜያዊ መፍትሔ እንጂ ዘላቂ ስምምነት ሆኖ ሌሎቹን ተጋሪ ሀገሮች ለማስገደድ እንደማይችል የሕግ ሊቃውንቱ እና ጸሐፍት ሲወተውቱ ኖረዋል፡፡ ዛሬም ድረስ ኢትዮጵያ ጨምሮ በሁሉም ዘንድ የሚነሳ ነው፡፡

ኢትዮጵያም ይህንኑ መነሻ በማድረግ ከግብጽ እና ሱዳን ጋር ተከታታይነት ያላቸውን ድርድሮች በማድረግና በጋራ ተጠቃሚነት ላይ የተመሰረተ አካሄድን በመከተል ዛሬ ላይ ደርሳለች፡፡ እግረ መንገዷንም የሕዳሴ ግድብ ግንባታን ወደ ማገባደዱ በማድረስ መጪውን ብሩህ ተስፋ በመጠባበቅ ላይ ትገኛለች፡፡ በተለይም የናይል የትብብር ማሕቀፍ ወደ ኮሚሽን ደረጃ መሸጋገሩ የኢትዮጵያ ጉዳይ ብቻ መስሎ የቆየው ውዝግብ ሁሉም የተፋሰሱ ሀገራት በእኔነት ስሜት እንዲሚገቱበት እና እንዲከራከሩበት እድል የሚሰጥ ነው፡፡

አንዱ ሕጋዊ ማሕቀፍ ሆኖ በቀጣይ የናይልን የውሃ አጠቃቀም ፍትሃዊነትን የሚያረጋግጠው የናይል የትብብር ማሕቀፍ ነው፡፡

የናይል የትብብር ማሕቀፍ ስምምነት የዓባይን ውሃ በጋራ፣ በእኩልነትና ምክንያታዊ በሆነ ሁኔታ ውሃውን መጠቀምና አብሮ መንከባከብ የሚያካትትና የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የድንበር ተሻጋሪ ወንዞች የሚተዳደሩባቸውን መርሖችን ጭምር ያካተተ ማሕቀፍ ነው። ይህም በአሥራ አንድ ሀገራት መካከል የሚደረግ ስምምነት ነው።

ጉዳዩን የኢትዮጵያ መንግሥት የቅርብ ክትትል ያደረገበት በመሆኑ የተሳካ እየሆነ መጥቷል። በተለይም ጠቅላይ ሚኒስትሩ የተለያዩ ሀገራት መሪዎችን በሚያገኙበት አጋጣሚ የውሃ ሀብትን በጋራ ማልማትና መጠቀም የሚቻልባቸውን መንገዶች ያነሳሉ። ይህም የኢትዮጵያ የውሃ ዲፕሎማሲ ሥራ ማሳያ ነው።

ኢትዮጵያ ቀድማ ማሕቀፉን ያጸደቀች ሲሆን ከዛ በኋላ ሩዋንዳ፣ ታንዛኒያ፣ ዩጋዳንዳ ገብተውበት በጥሩ ደረጃ ላይ ይገኛል። ይህ የመጣውም በጋራ ለመልማት ካለ ፍላጎት አንፃር ነው። በቅርቡ ደግሞ ብሩንዲና ደቡብ ሱዳን በምክር ቤቶቻቸው አጽድቀውታል።

ይህ መሆኑ ደግሞ ለዘመናት እንደ ኢትዮጵያ ያሉ የላይኛው ተፋስስ ሀገሮች ከውሃው በፍትሃዊነት የመጠቀም መብታቸውን ከማረጋገጡም ባሻገር ኢትዮጵያ ከሱዳንና ከግብጽ ጋር ስታደርገው የነበረውን ፍጥጫ ሌሎች ሀገራት እንዲቀላቀሉና ክርክሮችንም የሚያካሂዱት ሀገራት ሳይሆኑ ኮሚሽኑ እንዲሆን ያስችላል፡፡ ይህ ማለት ጉዳዩ የኢትዮጵያ እና የግብጽ ብቻ ሳይሆን የ11ዱም ሀገራት ጉዳይ እንዲሆን ያስገድዳል፡፡ በአጠቃላይ የናይል ትብብር ማሕቀፍ ወደ ኮሚሽን ማደጉ የሚከተሉትን ጥቅሞች ይዞ ይመጣል፡፡

የመጀመሪያው እና ዋናው ነገር የናይልን ውሃ በትብብር ለመጠቀምና ለማልማት ያስችላል፡፡ በቅኝ ግዛት ውሎች ውሃውን ከመጠቀም ተገለው የነበሩ የታችኞቹ ተፋሰስ ሀገራት ውሃውን በፍትሃዊነት የመጠቀም መብት ይጎናጸፋሉ፡፡

የናይል የትብብር ማሕቀፍ ወደ ኮሚሽን ደረጃ ማደጉ በአጠቃላይ በተፋሰሱ ሀገራት ዘንድ የሚታየውን አለመግባባት እና ውዝግብ የሚያረግብ ይሆናል፡፡ የዓባይ ግድብ ጉዳይ ከሶስቱ ሀገራት እና አህጉር አልፎ ዓለም አቀፍ መወያያ አጀንዳ እስከ መሆን ደርሷል፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜም በጸጥታው ምክር ቤት የታየ አነጋጋሪ አጀንዳ ለመሆን በቅቷል፡፡

ይህ ጉዳይ ከባህሪው በላይ ተለጥጦ ዓለም አቀፋዊ የጸጥታ ችግር ጭምር ተደርጎ ከመወሰዱም በላይ የአንዳንድ ሀገራት መሪዎች ጭምር በቦንብ እንዲመታ ምክር እስከ መስጠት ደርሰዋል፡፡ ይህ እንግዲህ ውዝግቡ የደረሰበትን ጡዘት የሚያሳይ ነው፡፡

ሆኖም የተፋሰሱ ሀገራት አሁን በደረሱበት ደረጃ ችግራቸውን ሁሉ በኮሚሽኑ በኩል የሚፈቱ በመሆኑ ወደ ሰላምና ትብብር የሚመጡበት አጋጣሚን ይፈጥራል ተብሎ ይታሰባል፡፡

ከዚህም በዘለለ የሚቋቋመው ኮሚሽን የናይልን ውሃ ከብክነት በጸዳ መልኩ በዘላቂነት ለመጠቀም የሚያስችል ስትራቴጂ ያወጣል ተብሎ ይታሰባል፡፡ የናይል ወንዝ የአፍሪካን 1/10 የቦታ ስፋት የሚሸፍን ነው፡፡ አስራ አንድ ሀገራትም በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የተፋሰሱ ሀገራት ተብለው ይጠራሉ፡፡ አጠቃላይ በዚህ ቤዚን ውስጥ እስከ 300 ሚሊዮን የሚጠጋ ሕዝብ ይኖራል ተብሎ የሚታሰብ ሲሆን የዚህ ወንዝ ልማት በቀጥታ ከነዋሪዎች ሕይወት መሻሻል ጋር የሚያያዝ ነው፡፡

በአጠቃላይ የናይል የትብብር ማሕቀፍ እዚህ ደረጃ እስኪደርስ ድረስ ኢትዮጵያ በፍትሃዊነት መርህ የዓባይን ውሃ መጠቀም ብቻ ሳይሆን የማልማትም ሥራ እያከናወነች ነው። ከዚህም ባሻገር የወንዙን ጤናማ የፍሰት ሂደት ለመጠበቅና ዘላቂ በሆነ መልኩ ለሁሉም ሀገራት በቂ ውሃ እንዲኖር በማሰብ በአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብር በቢሊዮን የሚቆጠሩ ችግኞችን በመትከል ላይ ትገኛለች፡፡ የአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብር ለውሃ መጠን መጨመር ጉልህ ሚና አለው። ችግኞች በተተከሉ ቁጥር አካባቢ ላይ የሚደርሰውን የመሬት መራቆት ይቀንሳል። የደን ሽፋንን ያሻሽላል። የግድቦችንም እድሜ ያረዝማል። የተፋሰሱ ሀገራትም በቂ ውሃ በዘላቂነት ማግኘት ይችላሉ፡፡

ባለፉት አምስት ዓመታት ኢትዮጵያ በአረንጓዴ ዐሻራ በተከለቻቸው ከ40ቢሊዮን በላይ ችግኞች ውስጥ ወደ ስምንት ነጥብ ሁለት ቢሊዮን የሚሆነው የተተከለው በዓባይ ተፋሰስ ነው። የዓባይን ውሃ በማልማት የሚመጣው ጠቀሜታ ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለታችኛው ተፋሰስ ሀገሮችም ጭምር ጠቀሜታው የጎላ ነው። ይህም ጉልህ እንቅስቃሴ ኢትዮጵያ የናይልን ውሃ በፍትሃዊነት የመጠቀም ፍላጎቷን የሚያመላክት ነው፡፡

ሁለተኛው የኢፍትሃዊነት መገለጫ ደግሞ ኢትዮጵያ ከባህር በር የራቀችበት ሁኔታ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ከጥንት ጀምሮ በቀይ ባህር ላይ ይዞታ የነበራትና ቀይ ባህርንም ስታዝበት የኖረች ሀገር ነች፡፡ 1ሺ800 ኪሎ ሜትር የሚረዝመውን የቀይ ባህር ይዞታ በቁጥጥሯ ሥራ ያኖረችና ለወጪና ገቢ እቃዎች ሁለት ወደቦች የምታስተዳደር ሀገር ነበረች፡፡ ኢትዮጵያን ከቀይ ባህር ውጭ ቀይ ባህርንም ከኢትዮጵያ ውጭ ማሰብ አይቻልም ነበር፡፡

ሆኖም የኢትዮጵያን ማደግ በማይፈልጉ ኃይላት ኢትዮጵያ ከቀይ ባህር እንድትወገድ ተደርጓል፡፡ ለዘመናትም ኢትዮጵያ ከቀይ ባህር ምንም ድርሻ እንዳልነበራት ሆን ተብሎ በተሰራጨው ትርክት ኢትዮጵያና ቀይ ባህር ተቆራርጠው ኖረዋል፡፡

የኢትዮጵያ ወደብ አልባ መሆንም ከሥነ ልቦናዊ ቀውስ ባሻገር ለበርካታ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ዲፕሎማሲያዊ ጫና ሕዝቡ እንዲጋለጥ አድርጎታል፡፡ የኢትዮጵያን ክብርና ዝና ዝቅ እንዲል ከማድረጉም ባሻገር በኢኮኖሚ ረገድም ተጎጂ እንድትሆን አድርጓታል፡፡ ለበርካታ መሠረተ ልማቶችና ለድህነት መቀነሻ ልማቶችን ይውል የነበረውን ከ1ነጥብ 6 ቢሊዮን ዶላር በላይ በየዓመቱ ለወደብ ብቻ በማዋል በድህነት ውስጥ እንድትማቅቅ አድርጓታል፡፡ ኢትዮጵያ ወደብ አልባ በመሆኗ ለኪራይና ለመጓጓዣ ከፍተኛ ዶላር ስለምታፈስ የሸቀጦች ዋጋ እንዲንርና የኑሮ ውድነትም እንዲባባስ ምክንያት ሆኗል፡፡ በዲፕሎማሲ እና በተጽዕኖ ፈጣሪነትም ረገድ የኢትዮጵያ ሚና አሽቆልቁሏል፡፡

በኢትዮጵያ አዲስ የመንግሥት ለውጥ ከመጣ ጀምሮ በትኩረት ከሰራባቸውና ለውጥ ካመጣባቸው ጉዳዮች አንዱ የባህር በር ጥያቄ ነው፡፡ መንግሥት በኢትዮጵያውያን ዘንድ ለዘመናት ቁጭት ፈጥሮ የነበረውን የባህር በር ጥያቄ በመመለስና ስብራትን በመጠገን ታሪካዊ ሚናውን እየተወጣ ይገኛል፡፡ ለ27 ዓመታት ያህል ፈርሶ የቆየውን የባህር ኃይል እንደገና በማደራጀት ኢትዮጵያ እንደገና የባህር ኃይል እንዲኖራት አድርጓል፡፡

ከዚሁ ጎን ለጎንም ኢትዮጵያ ከ33 ዓመታት በኋላ የባህር በር የምታገኝበት አማራጭ ተገኝቷል፡፡ ሰላማዊ አማራጭን ሲከተል የቆየው የኢትዮጵያ መንግሥት ሰሞኑን ከሶማሊ ላንድ ጋር የባህር በር የሚገኝበትን መግባቢያ ሰነድ (Memorandum of understanding) ተፈራርሟል፡፡

ይህ የመግባቢያ ሰነድ ሲተገበር አካባቢያዊ መረጋጋት የሚያመጣና ኢትዮጵያም በቀጣናው ላይ አለኝ የምትለውን የባለቤትነት ጥያቄ መልስ እንዲገኝ በር የሚከፍት ነው፡፡ ቀጠናዊ ሰላምን በማስፈን የአፍሪካ ቀንድ አካባቢ የተረጋጋ እንዲሆን በር ይከፍታል፡፡

የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ፖሊስ ቅድሚያ ትኩረት የሚሰጠው ለጎረቤት ሀገሮች ነው፡፡ በተለይም ለቀጠናዊ ግንኙነት የመጀመሪያውን ትኩረት በመስጠት ኢትዮጵያ ከጎረቤት ሀገራት ጋር የጠበቀ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት እንዲኖራት ተደርጓል፡፡ የኢትዮጵያ ልማት በአስተማማኝ መሠረት የሚቆመው የኢትዮጵያ የውስጥ ሰላምና መረጋጋት ሲረጋገጥ እንደሆነ እና ይኸው ሰላምና መረጋጋት የሚጸናው ደግሞ ከጎረቤት ሀገራት ጋር ሰላማዊ ግንኙነትን በማዳበርና የሀገራቱ ሰላምና መረጋጋት ሲረጋገጥ ነው፡፡ ለዚህም ከጎረቤት ሀገራት ጋር በወዳጅነት፣ በትብብርና ኢኮኖሚያዊ ትስስርን በሚያመጣ መልኩ የተቃኘ ዲፕሎማሲ ኢትዮጵያ በመከተል ላይ ትገኛለች፡፡

ሆኖም የኢትዮጵያን ማደግና መበልጸግ የማይፈልጉ ሀገራት ዘወትር የያዘቻቸው የልማት ዕቅዶች እንዲሰናከሉ ጥረት ሲያደርጉ ይታያሉ፡፡ ኢትዮጵያን ወደኋላ ለመጎተት በርካታ ሴራዎች ሲሸርቡ ማየትም የተለመደ ነው፡፡ ሰሞኑንም የሆነው የዚሁ ሴራ አንዱ ማሳያ ነው፡፡

የግብጽ፤ የሶማሊያ እና የኤርትራ መሪዎች በአስመራ ተገናኝተው ውይይት አድርገዋል፡፡ ውይይቱ በምስራቅ አፍሪካ ጉዳይ ነው ቢባልም በተዘዋዋሪ የኢትዮጵያን ጉዳይ መንካቱ አይቀሬ ነው፡፡ ይህ እንኳን ባይሆን ኢትዮጵያን ባገለለ መልኩ ስለምስራቅ አፍሪካ እና ቀይ ባህር ጉዳይ መወያየቱ የማያስገኘው ፋይዳ የለም፡፡

ይልቁንም ለምስራቅ አፍሪካ መረጋጋት ዓይነተኛ ሚና እየተጫወተች ያለችውን ኢትዮጵያን አግልሎ ሰላምና ልማት አመጣለሁ ማለት ከንቱ መሆኑን መረዳት ይገባል፡፡ ኢትዮጵያ በምስራቅ አፍሪካ ሰፊ የሕዝብ ቁጥር ያላት፤ ግዙፍ ኢኮኖሚ እየገነባች ያለች እና አስተማማኝ የጸጥታ ኃይል ያላት ሀገር ነች፡፡ ስለዚህም በየትኛውም መስፈርት ይህችን ሀገር ገለል አድርጎ የሚከወኑ የልማትም ሆነ የጸጥታ ጉዳዮች ሁሉ ውጤት አልባ ናቸው፡፡

**ኢትዮጵያ በምስራቅ አፍሪካ ሰፊ የሕዝብ ቁጥር ያላት፤ ግዙፍ ኢኮኖሚ እየገነባች ያለች እና አስተማማኝ የጸጥታ ኃይል ያላት ሀገር ነች። ስለዚህም በየትኛውም መስፈርት ይህችን ሀገር ገለል አድርጎ የሚከወኑ የልማትም ሆነ የጸጥታ ጉዳዮች ሁሉ ውጤት አልባ ናቸው**

ስፖርትና መዝናኛ

# የዘመን ጥበብ

# ማዕበል ጠሪ ወፍ

**ሙሉጌታ ብርሃኑ**




የማዕበል ወፎችን የቀሰቀሰው ሞገደኛ ራሱ የማዕበል ወፍ ነበር። አንዱ ተነስቶ ሌሎቹን ሁሉ ከፍ ባደረገበት መጽሐፍ ውስጥ፤ ጸሐፊው ከመሃከል አንደኛው መሆኑን አሳይቶበታል። እድሜ ልኩን የብዕር በትሩን ይዞ በምድረበዳና በለምለም መስክ ላይ ሲያዘግም የቆየው ደራሲና ሃያሲ ዓለማየሁ ገላጋይ ከሰሞኑ ለረዥም ጊዜያት ከገበያ ላይ ርቀው የነበሩ ሦስት የመጽሐፍት እርግቦቹን በድጋሚ አሳትሞ ከመጽሐፍቱ ፊላ በላይ ለቋቸዋል።

ከእነዚሁ ሦስቱ ጋር በአራተኛነት ለዳግም ሕትመት የበቃች ሌላ አንድ ነጭና ውብ እርግብም አለችበት። ለአሁኑ ስንቅ የሆነችውን "ማዕበል ጠሪ ወፍ"ን ጨምሮ "ቤባኒያ"፣ "በፍቅር ስም" እና "ወሪሳ" የተሰኙት መጽሐፍቶቹ በአንድ ጀንበር እንደ አዲስ ተወልደው ብቅ ብለዋል። ሦስቱ በግብግፕ ይያዙና ከ"ማዕበል ጠሪ ወፍ" ጋር የቻልነውን ያህል አብረን ለመብረር ድግ! ድግ! ብንል ይሻላል።

ብዕሩ ከቶ የማይቋረጥ፣ ብራናው የማይከደን ምትሀተኛው ደራሲ ዓለማየሁ ገላጋይ "ማዕበል ጠሪ ወፍ" ሲል ይህን መጽሐፍ ጽፏል። ደራሲው ሁሌም በአንድ ዓይነት መንገድና እይታ ውስጥ መቆየት የማያስለቸው ስለመሆኑ ሥራዎቹ ይናገራሉ። ግራ ቀኝም፣ ኋላ ፊትም እያለ አዳዲስ ሥነ ጽሑፋዊ ፍኖቶችን በመቅደድ ከማስደመም ስለማይመለስ ከፊቱ ቆመን በገፍ አድናቆትና ክብር እንድንሰጠው ግድ ይለናል።

በእርሱ የድርሰት ሥራዎች ውስጥ ከዚህ ቀደም በርከት ያሉትን እንግዳ ብዕሮችን ተመልክተናል። አሁን 18ኛው መጽሐፍ ላይ ደርሷል። 18ኛው የብዕር ልጁም ማዕበል ጠሪ ወፍ ነው። እንዲሁ በጥቃቅኑና በስሱ ካልሆነ በስተቀር በመጽሐፍ ደረጃ ማንም ያልደፈረውን ደፍሮና ተጠቦ በአዲስ ጭብጥና አቀራረብ አሳምሮ ጽፎታል።

በመጀመሪያ ዓለማየሁ ጋር ሃሳብ ነበር። ሃሳቡ ውስጥ ብዙ ትዝታ ነበር። በትዝታዎቹ ውስጥ ደግሞ ቁጭት፣ ብዙ መብከንከንና የለውጥ ድኋ ነበር። ባለፈው ዘመን ውስጥ በሀገራችን አንቱ ከተባሉ ደራሲያንና የሥነ ጽሑፍ ሰዎች ጋር ሁሉ ለማለት በሚቻል ደረጃ አብሯቸው አሳልፏል። በአንድ ማዕድ ላይ ተቋድሰዋል። በአንድ ጠረጴዛ ዙሪያ ተቀምጠው ስለ ሀገራችን ሥነ ጽሑፍ እያወጉ ተጨዋውተዋል። ወግ ቢጤ ይዘው፣ ቀልዱንም ጣል አድርገዋል። እናም ያ ዘመንና የዘመኑ ፈርጥ ጸሐፊያን ልቡ ውስጥ አሉ።

አሁንም በዚህኛው ዘመን ካሉት ጋርም በወዳጅነትም በሙያዊ ደቀመዝሙርነትም አብሯቸው አለ። ከእነዚህ ሁሉ ጋር ያሳለፈው ሕይወትና ሥራዎቻቸው ማዕበል ጠሪ ወፍን እንዲከትብ አድርጎታል። ሁሉንም በወግ በወጉ አሰናድቶ ለመጽሐፍነት ካበቃው በኋላ፤ ለመጀመሪያ ጊዜ ያስነበበው ከዓመት በፊት ነበር። ይሁን እንጂ መጽሐፉ ግን ቀድሞውን ለዓመታት በልቡ አዝሎት የኖረው ነው። ባያስነብበውም እርሱ ግን በውስጡ ደጋግሞ ሲያነበው ቆይቷል። ከዛሬ 20 ዓመት በፊት ሊጽፈው ጀምሮ መልሶ ብዕሩን ከድኖ አስቀመጠው። ተከድኖ በልብ የቆየ ነገር ሙክክ ብሎ መብሰሉ አይቀርምና በርግጥም በስሎ ነበር የወጣው።

መጽሐፉ ከውስጥም ከውጭም በብዙ አዳዲስ ነገሮች የተከበበ ነው። የሄደበትና በረዥሙ በተጓዘበት መንገድ ብቻም ሳይሆን አቀባበሉም የሚለይ ነበር። ለመጀመሪያ ጊዜ በመጋቢት 28/2016 ዓ.ም ተመርቆ በዚያው ዕለት ከአንባቢያኑ ጋር ተገናኘ። በተመረቀበት ዕለት ለንባብ የበቃ የመጀመሪያው መጽሐፍም ጭምር ያደርገዋል።

ከዚህም ከዚያም የሚያውቃቸው በርካታ ነገሮች ቢኖሩም በቂና የልብ የሚያደርስ መስሎ አልታየውምና አስቀድሞ ጥቂት ምርምር አዘል ጥናቶች አድርጎበታል። ከዚህ ስር የወጣው መጽሐፉ አሁንም ለሌላ የምርምር ፈለግ ዱካውን ያስቀመጠና መንገዱን አመልካች ሆኖ የቆመ ሥራ ነው። በመጽሐፉ ውስጥ የተካተቱት ሃሳቦች "ፍየል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ" መስለው ብትንትን ያሉና ከአንዱ ወደ አንዱ የሚዘሉ በመሆናቸው፤ ኧረ እንዴትስ አድርጎ ለመጽሐፍነት አበቃው? የሚያስብል ነው። እነዚህን በጊዜና ቦታ፣ በታሪክና ባለታሪክ ፍርስርስ ብለው በየፊናው የተበተኑትን ጉዳዮች ገጣጥሞ ወደ አንድ ሙሉዕ አካልነት ለማምጣት የተለየ ችሎታና ተሰጥኦ የሚጠይቅ ነበርና በሚገባ አሳክቶበታል። የማዕበል ጠሪ ፍኖት ቀያሽና ዘዋሪ ብዕሩን በሁለት አቅጣጫዎች ላይ አሳርፎታል። በሁለት ጎራዎች ለይቶ በምዕራፎች ከፋፍሎታል።

ያስቀመጣቸው ተደራሲያን እጅግ በርካታና እጅግ ብዙ ጉዳዮቻቸውን እያነሳ የሚዳስስላቸው ናቸው። የታላላቅ ደራሲያኑን ሕይወት ደርሶ ሳይሆን አጠገባቸው ሆኖ ከተመለከታቸውና ከተጋራቸው ነገሮች ዳራ ላይ ተንጠላጥሎ እናገኘዋለን። በፈጠራና በገጸ ባህሪያት የተጎነጎነ ልቦለድ ባይሆንም የዚያኑ ያህል ስሜትን ቁጥርጥር አድርጎ መያዝ የሚችል አድርጎ ሰርቶታል።

በእነዚያ ያለፉ 20 ዓመታት ውስጥ ከሚያየውና ከሆኑ ነገሮች ውስጥ ቆንጠር አድርጎ ሲጽፋቸው የነበሩትን ነገሮች አሰናስኖ ዛሬ "ማዕበል ጠሪ ወፍ" ሲል ለማወቅ የምንፈልጋቸውንና የሚያስፈልገንን አስነብቦናል። አለማየሁ ገላጋይ ለዚህ መጽሐፍ መሠረትና ምሰሶ ወጋግራ የሆኑት ማዕበል ጠሪ ወፎች በዓይነ ህሊናው ውስጥ ነበሩ። ከሥነ ጽሑፍ እስከ ደራሲያኑ ድረስ ብዕሩን ሲያስረዝም እያንዳንዱ የሚያነሳቸው ሰዎችና ልዩ ልዩ ሥራዎች ማዕበል ጠሪ ወፍ ተደረግው ተሰይመዋል።

በማዕበል የተከበበ ደራሲ፣ በማዕበል የተከደኑ የሥነ ጽሑፍ ሥራዎች ከዚያ ዓይነ ህሊናው ውስጥ ቁልጭ ብለው ይታዩታል። ሥራዎቻቸውን ምናልባትም አንዳንዶቻችን እናስታውስና እናነሳቸው ይሆናል። ነገር ግን በእሳት ነበልባል ውስጥ እየነደዱ፣ እረመጡ እየፈጀቻቸውም በእሳት በጋመው የባህር ማዕበል ላይ ሆነው ሥራውን ያበረከቱልንን ጀግኖች ከስማቸው በዘለለ ማናቸውንም ዘንግተነዋል። ሻማ እየቀለጠ ስለሰጠን ብርሃን እንጂ ስለሻማው ከናካቴው ትዝም አላለን።

ማዕበል ጠሪዎቹ እነርሱ ናቸው። መጽሐፉ ፈትፍቶ እያነሳ የሚያጎርሰን አንድም ስለ እነርሱ ነው። ምናልባት ስለ ስብሐት ገ/እግዚአብሔር አውቃለሁ እንል ይሆናል፣ ጸጋዬ ገ/መድህንን አልረሳሁትም ብለን እናስብ፣ በዓሉ ግርማንም እንጠቅስ ይሆናል...ግን ከማዕበሉ ወዲያ አለማወቃችንን እናውቀው ይሆናል።

በሁለት ክፍሎች የተሰናዳው ማዕበል ጠሪ ወፍ፤ በመጀመሪያ ክፍሉ ውስጥ ሥነ ጽሑፋዊ ዳሰሳና ጉብኝቶች ናቸው። የግዕዝ ቋንቋን ጫፍ ይዞ እስከ አማርኛው ሥነ ጽሑፍ ድረስ በምልከታ ይጓዛል። በሀገራችን የድርሰት ሥራዎች ብቅ ማለት ከጀመሩበት ጊዜ አንስቶ የተከሰቱ ጣጣና የተንሸዋረሩ እይታዎች በሥነ ጽሑፍ ውስጥ የከሰቱትን አንዳንድ ጉዳዮችንም ያነሳል።

በአሮጌውና በአዲሱ ትውልድ መካከል የተፈጠረው ጭንጋፍና ግርዶሽ ምን መልክ እንዳሳየ ያስመለክተናል። በሁለቱ ዘመን ደራሲያን ሰንሰለታማ ተራራዎች ላይ እየዳኸና እየቧጠጠ ውስጥ ውስጡን ከጥያቄ ጋር ሲሄድ እንመለከታለን።

ጸሐፊው ስለ ደራሲያኑና ሥራዎቻቸውን ብቻ ሳይሆን ሲጽፉበት ስለነበረው ቋንቋና ስለ ቋንቋው ሁዳዴ እያበጠረ ያስቀምጠዋል። በጥንታዊቷ ኢትዮጵያ ውስጥ እልፍ የብራና ላይ ጽሑፎች የተከተቡት በግእዝ ቋንቋ ነው። ለዛሬው የአማርኛ ሥነ ጽሑፍ መሠረትና መነሻውም ይኸው የግእዝ ቋንቋ ነው። ከኛ አልፎም ለብዙ የውጭ ሀገር ጸሐፊያን ማማውን መወጣጫ ሆኖላቸዋል።

ዓለማየሁ በማዕበል ጠሪ ወፍ ውስጥ በሌላኛው ምዕራፉ የሚጀምረው ከዚሁ ሃሳብ ላይ ነው። ግእዝን ከአማርኛው ጋር መሳ ለመሳ አቁሞ ያላወቅናቸውን አሊያም ልብ ያላልናቸውን ነገሮች ከማወቅም እንድንመሰጥባቸው አድርጎ ይነግረናል። በአንድ የሥነ ጽሑፍ ሥራ ውስጥ ደራሲው እስከቻለበት ድረስ ውብ በሆነ መልኩ ከመደበኛው የቋንቋው አጠቃቀም የማፈንገጥ መብትና ነፃነት አለው። በየዘመናቱ ጉምቱ ብዕረኛ የነበሩትን የአብዛኛዎቻቸውን ሥራ ከተመለከትን በዚህ መብትና ነፃነት ውስጥ እየተንሳፈፉ አዳዲስ ነገሮችን ለመፍጠር የቻሉ ናቸው። በራሳቸው የአጻጻፍና የቋንቋ ፍኖት ውስጥ ፈሰው እናገኛቸዋለን። ታዲያ ከምን ተነስተው ወዴትና ምን አዳዲስ ነገሮችን ለመፍጠር እንደቻሉ እያነሳሳ ይበልጥ ሥራዎቻቸውን እንድንወድና እንድናደንቃቸው ያደርገናል።

በ250 ገጾች የተዋቀረው መጽሐፍ ሁለተኛው ክፍል ማዕበል ጠሪዎቹን ይዞ ይነሳል። በኢትዮጵያ የሥነ ጽሑፍ ታሪክ ውስጥ እንደ ፀሐይ ሲያበሩ ከፍ ብለው በዘመናት ሁሉ ከወዲያኛው እስከዚህኛው ትውልድ የነገሱትን ደራሲያንን ሥራዎች መራርጦ ያነሳል። አብዛኛዎቻችን ሠሪውን ተመልክተን ስለሥራው የምናወራ ነን። ያ የእኛ እውነታ ቢመስልም፤ እውነታው ግን ሠሪውን መግለጥ ያለበት ሥራው ነው። ሠሪውን እየተመለከትን ስለ ሥራው ባወራን ቁጥር ሁሉ አንዲቷን ጫፍ ብቻ ይዘን ከማይወጡበት የስህተት መቀመቅ እንወርዳለን።

ዓለማየሁ ገላጋይም ይህን አሰቦ ይመስላል ከጸሐፊያኑ አስቀድሞ ሥራዎቻቸውን በክፍል አንድ ማስነበቡ። ቀጥሎም በሁለተኛው ክፍል ራሳቸውን ይዞ መጣ። ከሥራዎቻቸውና ካላቸው የታላቅነት ማዕበል በመነሳት እንዴት ያሉ ድንቅ ወፎች መሆናቸውን ያሳየናል። ሥራዎቻቸውን እያጣቀሰ አቁሞ ምስክሮች ያደርጋቸዋል። በዚህ ምልከታው ውስጥ ቀደም ሲል በሥራ ያየናቸው ሰባቱ ጉምቱ ደራሲያን ተካተውበታል።

ከግጥም ሥራዎቹ እስከ ቲያትር መድረኮች ድረስ የነገሰው ሎሬት ጸጋዬ ገ/መድህን አንደኛው ነው። እንደ ሻማ ቀልጦ፣ እንደ ጧፍ ነዶ ከሞት በላይ ስምና ሥራውን ያኖረው በዓሉ ግርማ በዓለማየሁ ገላጋይ ብዕር ውስጥ ምስሉ ተስሏል። ለሥነ ጽሑፍ እንደኖረላት ሳይኖር የሄደው ደበበ ሰይፉ ከማዕበሉ ላይ ቆሞ ታንኳዋን በግጥሞቹ ሲጨብጥ እንመለከታለን። ከሰለሞን ደሬሳ የብዕር ጫፍ ላይ አዲስ መልክና ቀለም ያለው መስመር ተሰምሮ ይታያል።

በሀገራችን የልቦለድ ታሪክ ውስጥ ምሁራኑን ሳይቀር በጎራ ለይቶ እስከማሟገት ያደረሰውን "አደፍርስ"ን የጻፈው ዳኛቸው ወርቁ ሌላኛው ማዕበል ጠሪ ወፍ ነው። አፈወርቅ ገ/ኢየሱስም በሌላ አቅጣጫ ከተፍ ይላል። ስሎ በስዕሉ፣ ጽፎ በግጥሙ ዛሬም ድረስ አፍ የሚያስከፍተን ገ/ክርስቶስ ደስታን በዚህ መጽሐፍ ውስጥ እጅ እንነሳዋለን። ሰባቱ የማዕበል ወፎች ከፍ ብለው ሲበሩ እየተመለከትን ፈገግ እንላለን። ደግሞ ክንፉቸው እየተሰበረ መሃል ላይ ለመውደቅ ቁልቁል ሲምዘገዘጉ እንደ አዲስ እንደነግጣለን። ከባህሩ ማዕበልና ሞት ጋር ፊት ለፊት እየተያዩ ለመዳን ሲውተረተሩ እናዝናለን። የሆነው ሁሉ ሆኗልና መጥፎውንም ጥሩውንም ትዝታ ከእውነታው ጋር እንቀበለዋን። ዓለማየሁ ከልቡ ጽፎታል። ከልባችን እናነበዋለን።

ጸሐፊው ግን አሁንም ይቀጥላል። ያልታዩ ምስሎች፣ ያልተነበቡ ገጾችን ይገልጥልናል። ምን ትልቅ ብንሆን፣ ምን ተራራ ንደን ባቢሎን በጥበብ ብንገነባ ማናችንም ፍጹማን አይደለንም። የማይሳሳቱም የማይሰሩ ብቻ ናቸው። እስከሰራን ድረስ አንዲት ጉድለት፣ ጥቁር ነጥብ አይታጣም። ምን ቢጠቁር ግን የሠራነውን አያደበዝዘውም። ከሳትነው የሰጠነው ይበልጣል። ያቺን ጥቁር ነጥብ አግዝፈን እንደ ተራራ ከተመለከትናት አልፈን መቼም አንሻገረውም። በይሉኝታና ቸልታ ለማለፍ ስንሞክርም የዋዛ አይደለምና አደናቅፎ ይጥለናል። ሥራውን በቀኝ ይዘን፣ በግራ ነጥቧን ነቅሰን ለማረም ስንወድ ግን ጉዟችን ሁሉ የሰመረ ይሆናል። በውዳሴና እልልታ ብቻ ገነት አይገባም። ጉምቱዎቹን ከፍ አድርጎ የሰቀላቸው ዓለማየሁ ገላጋይ በከፍታው ውስጥ ሊያስመለክተን የወደደው ነገር ነበረው።

በውዳሴ ታላቅነታቸውን ጽፎ ጽፎ ሲያበቃ ነጥቧን ነካ አደረጋት። የያዘው አንድም የሥነ ጽሑፍን መንገድ ጥርጊያ ነውና እንደምን ለማለፍ ይቻለዋል? በሙግት ራሱን አሞግቶ ቢኖሩ ኖሮ አሜን ብለው ሊቀበሉት የሚችሉት ትችት ውስጥ ይሸጎጥባቸዋል። ያልደፈርነውን አጥር ዘሎ ያሳየናል። ይህን ሲያደርግ "ሙት አይወቀስም" ስለሚባል ብቻ ሳይሆን በነገሮቹ ውስጥ የሚያነሳቸው የእውነትም ያለ ወቀሳ ነው። አውቀንም ሆነ ሳናውቅ አለባብሰን ያለፍነውን በማረም መንፈስ ውስጥ ሆኖ ነው። ሥነ ጽሑፋችን ከረዥም እንቅልፉ ውስጥ እንዲነሳ ከወደድን ይህን ማድረግ ግድ ነው። ጥበብ ያለ ሂስ የምትገነባው ኃያል ቅጥር አይኖራትም። ያለ ቅን ትችት ሠርታ የምታቆመው ቤት የላትም። ከመሰለንም የገባን ዕለት ተንዶ በላያችን የፍርስራሽ ክምር ይሆናል።

ዓለማየሁ ይህን ለመጻፍ ስለምን ወደደ? ከማንበባችን መልስ መጽሐፉን ከድነን ይህን ጥያቄ ለራሳችን መጠየቅ ይኖርብናል። ጸሐፊው ለመጻፍ የነሸጠውን ጉዳይ እንድናነበው ካስነሸጠን ነገር ውስጥ ፈልገን ማግኘት ይኖርብናል። የጻፈው ስለ ደራሲያኑ፣ ያስነበበን ስለ ሥራዎቻቸው ቢሆንም፤ ውስጡ ግን እነርሱ ብቻቸውን አይደሉም። እኛ አንባቢዎችና ስለ ሥነ ጽሑፍ ያገባኛል የምንል ሁሉ አለንበት። የቱ ጋር ነኝ? ብሎ መጠየቅና መምረጥ ግን የኛ ፋንታ ነው። ሁላችንም ለማወቅ የሚገባን አንድ ነገር ቢኖር ግን፤ "ማዕበል ጠሪ ወፍ" መጽሐፍ ስለሆነ ብቻ አንስተን የምናነበውና ከደነን የምናስቀምጠው አለመሆኑን ነው። እንደ ልቦለድ ተመስጠንበት ስናበቃ "ይገርማል!" ብለን ብቻ አናስቀምጠውም። እንደ አንዳንድ ኢ-ልቦለዶችም ዕውቀት ሸምተንበት እንደምንወረውረው ፌስታል አይደለም። ይልቅስ በክብር ከግርግዳው ላይ የምንሰቅለው ዘንቢል እንጂ። እንደገና ነገም የምንፈልገው ንብረታችን ነው። ስለምንወዳቸው ደራሲያንና ሥራዎቻቸው ማወቅ ብቻ በቂ አይደለምና ተዝናንተንም ሆነ ሸምተን ስናበቃ ብዙ ጥያቄ፣ ብዙ ምላሽ ፍለጋ መውጣት ግድ ይለናል። ወርቁን እስከምናገኘው ድረስ ሳንታክት መቆፈር ይኖርብናል።

የሀገራችን ሥነ ጽሑፍ እንደ ግመል ሽንት ስለምን ወደኋላ አፈገፈገ? ለምንል ምላሹ ከማዕበል ጠሪ ወፍ ላይ ተጀምሯል። ጸሐፊው ስለ ሀገራችን የሥነ ጽሑፍ እድገትና መቀጨጭ ግድ ብሎት ማሰላሰል የጀመረው በዚህ መጽሐፍ ውስጥ አይደለም። ከወዳጆቹም ጋር ይሁን በየሚዲያው ስለዚህ ጉዳይ ሳያነሳ አያልፈውም። ማሰስና መጠየቁም አይሰለቸውም። ስለ ሥነ ጽሑፍ እድገት በመጨነቅ እንቅልፍ ከማይወስዳቸው ደራሲያን መሀከል አንደኛው ነው። እናም በውል የሚያውቃቸውን 20 ዓመታትን በልቡ አዝሎ መኖሩም ለዚሁ ነው። ለመጻፍ ሲል ብቻ አልጻፈውምና ለማንበብ ብቻ ስንል አናነበውም። ስናነበው እንጠይቃለን። እንፈትሻለን። ዘመንን ከዘመን፣ ትውልድን ከትውልድ ጋር እያነጻጸርን "የቱ ጋር ነው የተሰበርነው?" ብለን እንጠይቃለን። አንወቅስም፤ ግን እየተቸን ስብራቱን እንጠግናለን። ወደቀልባችን ተመልሰን ራሳችንን እንጠይቃለን። የእውነትን ዳና ተከትለን እንወጣለን። መዓዛዋን እያሸተትን እንሄዳለን። እየሄድን ከሥነ ጽሑፍ ማማ ላይ እንደርሳለን። ደርሰን ከከፍታው ሰገነት ላይ እንቆማለን። ቆመንም፤ ያለፍነውን ትናንት፣ የቆምንበትን ዛሬ እየተመለከትን "አበጀን!" እንላለን። ያን ጊዜ፤ ሥነ ጽሑፋችን ዓለምን ሁሉ አሸንፋ በጥበብ ኒሻን ትንቆጠቆጣለች።

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## ለሠላም ግንባታ ተስፋ የተጣለበት ስትራቴጂ

**አስናቀ ፀጋዬ**

የምሥራቅ አፍሪካ ቀጣና ወትሮም ቢሆን የርስ በርስ ጦርነትና ግጭት አያጣውም። በቀጣናው በሚገኙ ሀገራት በየጊዜው ጎሣን፣ ድንበርን፣ ፖለቲካን ሌሎች የተፈጥሮ ሀብቶችን መሠረት አድርገው በሚቀሰቀሱ ግጭቶች ምክንያት በርካታ ሠላማዊ ዜጎች ለሠላም እጦት፣ ለስደት፣ መፈናቀል፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውሶች ሲጋለጡ ይስተዋላል። ይህ ሁኔታም ከመለዘብ ይልቅ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ መጥቷል።

በቀጣናው ሠላምና መረጋጋት ለማምጣት ብርቱ ጥረት ሲደረግ የቆየ ቢሆንም ጥረቶቹ ሁሉ ትርጉም ያለው ለውጥ ሊያመጡ አልቻሉም። ለእስካሁኑ ጥረት ፍሬ አልባ መሆን የቀጣናው ሀገራት መንግሥታት ሠላምና መረጋጋትን ለመፍጠር የሚያደርጉት ጥረት አናሳ መሆን፣ በሠላም ግንባታ ሂደት ውስጥ የሲቪል ማኅበራት፣ የተገፉ የኅብረተሰብ ክፍሎች፣ አካል ጉዳተኞችና ሌሎችም አለመካተትና በጥናት ላይ የተመረኮዙ የሠላምና መረጋጋት ሥራዎችን አለመከናወንና ሌሎችም በምክንያትነት ይጠቀሳሉ።

ይሁንና በቀጣናው አሁን ላይ የሚታየውን የሠላም እጦትና አለመረጋጋት በዘላቂነት ለመፍታት በሚደረገው ጥረት እገዛ ሊያደርግ የሚችል /African Strategic Plan For Peace and Security/ የተሰኘ ስትራቴጂ ተዘጋጅቷል። ይህ ስትራቴጂ እ.ኤ.አ ከ2024 እስከ 2033 የሚቆይ ሲሆን ኢትዮጵያን ጨምሮ በኬንያ፣ ጅቡቲ፣ ኤርትራ፣ ሶማሊያ፣ ሱዳንና ደቡብ ሱዳን ይተገበራል። ስትራቴጂውም Bread for the World (BftW) እና The American Friends Service Committee (AFSC) በተሰኙ ዓለም አቀፍ የልማትና ግብረሠናይ ድርጅቶች እንደተዘጋጀ ታውቋል።

ወይዘሪት ሳምራዊት ወርቁ በአሜሪካን ፍሬንድስ ሰርቪስ ኮሚቴ ስር በሚገኘውና ተቀማጭነቱን በአዲስ አበባ ባደረገው ሰላማ ኸብ ፕሮግራም ቢሮ ፕሮጀክት ፎካል ፖይንት ሆነው ያገለግላሉ። እርሳቸው እንደሚሉት፣ ስትራቴጂው የአፍሪካ ቀንድ ቀጣና ለአስርት ዓመታት በተለያየ ምክንያት በተፈጠሩ ግጭቶችና ጦርነቶች ጉዳት እንደደረሰበት ይታወቃል። ይህ ግጭትና ጦርነት አንዴ ጋብ ሌላ ጊዜ ደግሞ ዳግም ሲያገረሽ ቆይቷል። ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር በተያያዘም ከፍተኛ ጉዳት ሲያስተናግድና የአካባቢውም ማኅበረሰብ የጉዳቱ ሰለባ ሲሆን ይታያል።

> **«አካል ጉዳተኞች በርካታ እምቅ ችሎታ ያላቸው እንደመሆኑ በስትራቴጂው ትግበራ ሂደት በተለይ በአካል ጉዳተኙነት ረገድ የሚታዩ ችግሮችን ለመቅረፍ በሚደረገው ጥረት የራሳቸውን አስተዋፅዖ እንደሚያበረክቱ ይጠበቃል»**

ከዚህ አኳያ በአፍሪካ ቀንድ ሀገራት ውስጥ ያሉ የሚመለከታቸው አካላት ባለፉት ዓመታት ሠላምና መረጋጋትን ለማስፈን የተቻላቸውን ሁሉ ጥረት ሲያደርጉ የቆዩ ቢሆንም ጥረቱ ግን በቂ አይደለም። ምክንያቱም አሁንም ቢሆን በቀጣናው ግጭቶችና የእርስ በርስ ጦርነቶች እየቀጠሉ በመምጣታቸው ነው። ከዚህ በመነሳት ነው ሁለቱ አጋር ድርጅቶች የአፍሪካ ቀንድን እያስጨነቁ ባሉ ጉዳዮች ላይ አስተዋፅዖ ያበረክታል ተብሎ የሚጠበቀውን ይህን ስትራቴጂ በመረጃ ላይ ተንተርሰው ያዘጋጁት።

ይህ ስትራቴጂ አምስት መሠረታዊ ምሶሶዎች ያሉት ሲሆን እነዚህም በጥናት ላይ የተመሠረተ ሙግት ማድረግ፣ አካቶነት፣ የሽግግር ፍትሕና ፈውስ፣ አስተዳደርና የአየር ንብረትና የአካባቢ ጥበቃ ፍትሕ ናቸው። በነዚህ ምሶሶዎች ላይ መሠረቱን ያደረገው ስትራቴጂው ይህ ተዓማኒነት ላለውና ተፅዕኖ ፈጣሪ ቅስቀሳ ቅድሚያ በመስጠት ብሎም የተለያዩ ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ የግጭት መከላከል እና አፈታትን ለመደገፍ ያለመ ነው።

ወይዘሪት ሳምራዊት እንደሚናገሩት፣ በዚህ የምሥራቅ አፍሪካ ቀጣና ውስጥ የሚገኙ ሕዝቦች በተለያየ መልኩ የብዙ ችግሮች ገፈት ቀማሽ ሆነው ቆይተዋል። አንዳንድ የማኅበረሰብ ክፍሎች ደግሞ የከፋ ጉዳት አስተናግደዋል። ከዚህ አንፃር ስትራቴጂው ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍሎች ሰብዓዊ ክብራቸውን መልሰው እንዲያገኙ ዕድል የሚሰጥና አካታች ሂደት ላይ ያተኮረ ነው። በዚህም ስትራቴጂው የተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች በሠላም ግንባታና መረጋጋት ሂደት ውስጥ ተሳታፊ እንዲሆኑ ዕድል ይሰጣቸዋል። በተለይ ሴቶች፣ ወጣቶች፣ አካል ጉዳተኞች፣ ሌሎች የተገፉ የማኅረሰብ ክፍሎች፣ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች መሪዎችና የሃይማኖት መሪዎች በስትራቴጂው ትግበራ ይበልጥ የሚሳተፉ ይሆናል።

በአሜሪካን ፍሬንድስ ሰርቪስ ኮሚቴ ስር በሚገኘውና ተቀማጭነቱን በአዲስ አበባ ባደረገው ሰላማ ኸብ ፕሮግራም ቢሮ ዳይሬክተር ሚስተር ሞሰስ ቻሲህ በበኩላቸው እንደሚናገሩት፣ በዚህ ስትራቴጂ ትግበራ ሂደት በሁለተኛው የስትራቴጂው ምሶሶ ውስጥ አካል ጉዳተኞች እንዲሳተፉ ተካተዋል። የአካል ጉዳተኞች ባላቸው ጉዳት ምክንያት ሁኔታዎችና መሠረተልማቶች ለእነርሱ በምን መልኩ አመቺና ተደራሽ መሆን እንዳለባቸውና በሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ላይ ውይይቶች ይካሄዳሉ። ስለዚህ አካል ጉዳተኞች በዚህ ስትራቴጂ ትግበራ ሂደት በውይይቶቹ ላይ በመሳተፍ እየገጠሟቸው ያሉ ችግሮች ያወራሉ፤ ለችግሮቹ መፍትሔ እንዲገኝም ጥያቄያቸውን ያቀርባሉ።

ሁኔታው መዋቅር የመፍጠር ከሆነ ደግሞ አካል ጉዳተኞች በስትራቴጂው ትግበራ ሂደት ተሳትፈው መዋቅር የመገንባት እውቀት እንዲኖራቸው ያስችላቸዋል። በሚፈጠረው መዋቅር ውስጥም አካል ጉዳተኞች በሁለንተናዊ መልኩ ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉባቸው ሁኔታዎች ይፈጠራሉ። አካል ጉዳተኝነት አለመቻል አለመሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። ምክንያቱም ግጭት በበዛበት በምስራቅ አፍሪካ ቀጣና ውስጥ አካል ጉዳተኝነት ምንም ነገር ከማድረግ እንደማያግድ ማየት ተችሏል። የአካል ጉዳተኝነት ጉዳይ የፖለቲካ አጀንዳ እንዲሆን የመንግሥት አመራሮችንና ሌሎችን ባለድርሻ አካላት ማሳመን ያስፈልጋል። ለዚህ ስትራቴጂው ጥሩ አጋጣሚ ይፈጥራል።

በዚህ አጋጣሚ ከአካል ጉዳተኝነት ጋር በተያያዘ ለማኅበረሰብ ሰፊ ግንዛቤ መፍጠር፣ ተሳትፎን ማሳደግ ይገባል። ስለዚህ በስትራቴጂው ትግበራ ሂደት አካል ጉዳተኞች እንዲሳተፉ ይፈለጋል። ሚናቸውንም መጫወት ይጠበቅባቸዋል። አካል ጉዳተኞች በርካታ እምቅ ችሎታ ያላቸው እንደመሆኑ በስትራቴጂው ትግበራ ሂደት በተለይ በአካል ጉዳተኝነት ረገድ የሚታዩ ችግሮችን ለመቅረፍ በሚደረገው ጥረት የራሳቸውን አስተዋፅዖ እንደሚያበረክቱ ይጠበቃል።

በምሥራቅ አፍሪካ ቀጣና ሠላምና መረጋጋትን ለማምጣት ቁልፍ ሚና እንደሚኖረው የታመነበት /African strategic plan for Peace and security/ ስትራቴጂ ‹‹The Africa WE Want›› በሚል መሪ ቃል ዛሬ በሂልተን ሆቴል የኢትዮጵያ የመንግሥት ተወካዮችና፣ ባለድርሻ አካላት እንዲሁም ሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት በተገኙበት እንደሚካሄድ ይጠበቃል።

# ዓለም አቀፍ

## ሐሰተኛ የቦንብ ሽብሮች ከ10 በላይ የሕንድ በረራዎችን አስተጓጎሉ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

በሕንድ አየር መንገድ ጉዳዩ የተለመደ ቢሆንም ባለፉት ሁለት ቀናት በተደጋጋሚ እየቀረቡ የሚገኙ ጥቆማዎች ምንጭ ምን እንደሆነ አልታወቀም።

ባለፉት 48 ሰዓታት በሕንድ በረራዎች ላይ የቀረበውን ሐሰተኛ የቦንብ ሽብር ጥቆማዎችን ተከትሎ 10 በረራዎች እንደተስተጓጎሉ ተነገረ።

በትላንትናው እለት የሲንጋፖር አየር ኃይል ቦንብ ተጠምዶባቸዋል የተባሉትን አውሮፕላኖች በተዋጊ ጄቶች በማጀብ ሕዝብ ከሚሰበሰብባቸው አካባቢዎች ራቅ ብለው እንዲቀመጡ አድርጓል፡፡

ይህ ከመሆኑ ከሰዓታት በፊት የኢንዲያ ኤክፕረስ ንብረት የሆነ ከደልሂ ወደ አሜሪካ ቺካጎ ሲጓዝ የነበረ አውሮፕላን የቦንብ ስጋቱን ተከትሎ በካናዳ እንዲያርፍ ተገዷል፡፡

ሆክስ ቦምብ ትሬት ወይም ሐሰተኛ የቦምብ ማስፈራሪያዎች በብዛት ሕዝብ በሚበዛባቸው አካባቢዎች ፈንጂዎች ስለመጠመዳቸው ለፀጥታ አካላት የሚደረጉ ጥቆማዎች ናቸው።

በሕንድ አየር መንገድ ጉዳዩ የተለመደ ቢሆንም ባለፉት ሁለት ቀናት በተደጋጋሚ እየቀረቡ የሚገኙ ጥቆማዎች ምንጭ ምን እንደሆነ አልታወቀም፡፡

የአሁኑ ጥቃት ለየት የሚያደርገው ኤር ኢንዲያን ጨምሮ በሦስት የተለያዩ የአየር ትራንስፖርት በሚሰጡ ድርጅቶች ንብረት በሆኑ አውሮፕላኖች ላይ ተደጋጋሚ ጥቆማ መድረሱ ነው፡፡

በኤክስ (ትዊተር) ገጽ ላይ በአውሮፕላኖች ላይ ቦምብ ስለመጠመዱ አንድ ማስፈራሪያ ከተለጠፈ በኋላ መነሻቸውን ከሕንድ ሙምባይ ያደረጉ 3 ዓለም አቀፍ በረራዎች እንዲዘገዩ የተደረገ ሲሆን፤ ከጉዳዩ ጋር በተገናኘ የተጠረጠረ አንድ ታዳጊ በፖሊስ ተይዞ ምርመራ እየተደረገበት እንደሚገኝ ቢቢሲ ዘግቧል፡፡

በተመሳሳይ በኤር ኢንዲያ ንብረት በሆነ አውሮፕላን ላይ




የበረራ ቁጥሩ ተጠቅሶ በተለጠፈ የቦምብ ስጋት 7 በረራዎች እንዲሰረዙ ተደርጓል፡፡

በበረራዎቹ መዘገየት እና መሰረዝ ከፍተኛ ኪሳራ እንደደረሰባቸው ያስታወቁት አየር መንገዶቹ ከሲቪል አቪዬሽን ደኅንነት ባለሥልጣናት እና ከፖሊስ ጋር በመተባበር ጉዳዩን ለማጣራት እየሠሩ እንደሚገኙ ገልጸዋል፡፡

የቀረበውን ስጋት ተከትሎ ተሳፋሪዎች ከነሻንጣቸው እና በካርጎ ከተጫኑ ጭነቶች ጋር እንዲወርዱ ከተደረገ በኋላ የኢንጂነሪንግና የደኅንነት ቡድኖች አውሮፕላኑ ድጋሚ ወደ አየር ላይ ከመውጣቱ በፊት አስፈላጊውን ማጣሪያ የሚያደርጉ ሲሆን በዚህ ሂደት አየር መንገዶች በሺህ ዶላሮች የሚቆጠር ኪሳራ ያጋጥማቸዋል፡፡



## ሰሜን ኮሪያ 1 ነጥብ 4 ሚሊዮን ዜጎቿ ጦሩን ለመቀላቀል ማመልከታቸውን አስታወቀች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ደቡብ ኮሪያን በድሮን ድንበር ጥሳ ትንኮሳ ፈጽማለች የሚል ክስ ያቀረቡት የሰሜን ኮሪያ መገናኛ ብዙኃን 1 ነጥብ 4 ሚሊዮን ገደማ ወጣት ሰዎች ጦሩን ለመቀላቀል መመዝገባቸውን በዛሬው እለት ገልጸዋል።

ጦሩን ለመቀላቀል ማመልከቻ ያስገቡት ተማሪዎችን እና የወጣቶች ማኅበር አመራሮችን ጨምሮ ወጣቶች ጠላትን ለመደምሰስ በሚደረገው “የተቀደሰ ውጊያ” ለመሳተፍ ቁርጠኛ መሆናቸውን ሮይተርስ ኬሲኤንኤን ጠቅሶ ዘግቧል።

ኬሲኤንኤ ይፋ ባልሆነ ቦታ ወጣቶች ማመልከቻቸውን ሲፈርሙ የሚያሳዩ ፎቶዎችን ለቋል። ሰሜን ኮሪያ በርካታ ወጣቶች እንዳሏት ይፋ ያደረገችው በኮሪያ ባሕረሰላጤ ያለው ውጥረት ከፍተኛ ደረጃ ላይ ከደረሰ ከሁለት ቀናት በኋላ ነው።

ሰሜን ኮሪያ ከዚህ በፊትም በቀጣናው ውጥረቶች በሚያይሉበት ወቅት እንዲህ አይነት መረጃዎችን በመልቀቅ ትታወቃለች። ባለፈው ዓመት የሀገሪቱ መንግሥት መገናኛ ብዙኃን አሜሪካን ለመዋጋት 800ሺ ወጣቶች መመዝገባቸውን ይፋ አድርጋ ነበር።

የስትራቴጂክ ስተዲስ ዓለምአቀፍ ኢንስቲትዩት መረጃ እንደሚያመለክተው ከሆነ ሰሜን ኮሪያ 1 ነጥብ 28 ወታደሮች እና 600ሺህ ተጠባባቂዎች አሏት።

ሰሜን ኮሪያ በድንበር አካባቢ ያለውን ምሽጓን ለማጠናከር ሁለቱን ኮሪያዎች የሚያገናኘውን ሙሉ በሙሉ እንደምታፈርስ አሳውቃ ነበር።

# ስፖርት





# ኢትዮጵያ የአፍሪካ ዋንጫን ለማዘጋጀት በይፋ ጥያቄ አቅርባለች

**ዓለማየሁ ግዛው**

ኢትዮጵያ የ2029 አፍሪካ ዋንጫን ለማዘጋጀት ለአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌዴሬሽን (ካፍ) በይፋ ጥያቄ ማቅረቧ ታውቋል:: ኢትዮጵያ በቅርቡ 46ኛውን የካፍ ጠቅላላ ጉባኤና የአፍሪካ ከ20 ዓመት በታች የእጅ ኳስ ሻምፒዮናን ለማስተናገድ እያደረገች የሚገኘውን ዝግጅት በተመለከተ የባሕልና ስፖርት ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽንና የእጅ ኳስ ፌዴሬሽን ከትናንት በስቲያ መግለጫ ሰጥተዋል::

የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት አቶ ኢሳያስ ጂራ በመግለጫው ላይ እንደተናገሩት፣ መንግሥት የ2029 የአፍሪካ ዋንጫን ለማዘጋጀት ፍላጎት እንዳለው ለካፍ በደብዳቤ ጠይቋል:: ካፍ የኢትዮጵያን ጥያቄ መቀበል አለመቀበሉንም በሚቀጥለው ዓመት ሞሮኮ በሚያካሂደው ጠቅላላ ጉባኤ ላይ እንደሚወሰን አቶ ኢሳያስ ጠቁመዋል::

ካፍ በቀጣዩ ሳምንት ጠቅላላ ጉባዔውን አዲስ አበባ ላይ ሲያደርግ ኢትዮጵያ በመድረኩ የ2029 የአፍሪካ ዋንጫን የማዘጋጀት ፍላጎትን በማሳየት ዕድሉ እንዲሰጣት ቅስቀሳ እንደሚደረግም አቶ ኢሳያስ ገልጸዋል:: የካፍ ፕሬዚዳንትና ምክትሎቻቸው በዚህ ጉባኤ ለመታደም ሲመጡም በተናጠል ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር ውይይት እንደሚያደርጉም ተጠቁሟል::

አቶ ኢሳያስ የዘንድሮውን የካፍ ጠቅላላ ጉባዔ በተመለከተ በሰጡት ማብራሪያ፣ ጉባዔው ወደ አዲስ አበባ የመጣው የኢትዮጵያ መንግሥት የአፍሪካ ዋንጫውን ለማዘጋጀት እንቅስቃሴ ከጀመረ በኋላ መሆኑን አስረድተዋል:: 46ኛው የካፍ ጠቅላላ ጉባኤ ኮንጎ ኪንሻሳ ላይ እንዲካሄድ በሥራ አስፈጻሚ ተወስኖ





**ኢትዮጵያ የአፍሪካ ዋንጫን ለማዘጋጀት ለካፍ በደብዳቤ ጥያቄ ማቅረቧን አቶ ኢሳያስ ጅራ ገልፀዋል፣**

እንደነበር እና በወረርሽኝ ምክንያት ተሰርዞ መንግሥት ባሳየው ፍላጎት ወደ ኢትዮጵያ ሊመጣ እንደቻለም አቶ ኢሳያስ ተናግረዋል::

ጉባኤውን ለማዘጋጀት በቀረበው ጥያቄ መሠረት ናይሮቢ በተካሄደ የካፍ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ስብሰባ የተወሰነ ሲሆን፣ የጉባኤውን ወጪ የሚሸፍነው መንግሥት ቢሆንም ኢትዮጵያ የሌላ ሀገር ዝግጅት በመውሰዷ፣ መንግሥትና ካፍ ግማሽ ወጪ በመጋራት ጉባኤው በአዲስ አበባ እንደሚካሄድ ፕሬዚዳንቱ ገልጸዋል::

ኢትዮጵያ በዚህ ወር የካፍን ጠቅላላ ጉባዔና የአፍሪካ ከ20 ዓመት በታች የእጅ ኳስ ሻምፒዮናን ለማስተናገድ ዝግጅቷን እያጠናቀቀች እንደምትገኝም በጋዜጣዊ መግለጫው ላይ ተጠቁሟል:: የካፍ ጠቅላላ ጉባኤና ከጥቅምት 10 ጀምሮ እስከ 12 በስካይ ላይት ሆቴል እንደሚካሄድ የተገለፀ ሲሆን፣ የአፍሪካ ከ20 ዓመት በታች እጅ ኳስ ሻምፒዮና ደግሞ ከጥቅምት 23 እስከ 27/2017 ዓ.ም ድረስ ይደረጋል::

የሁለቱም ስፖርታዊ ኩነቶች የቅድመ ዝግጅት ምዕራፍ የሚገኝበትን ደረጃ አስመልክተው ባሕልና ስፖርት ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን እንዲሁም የእጅ ኳስ ፌዴሬሽኖች መስተንግዶዎቹ ስኬታማ እንዲሆኑ በቅንጅት እየሠሩ እንደሚገኙ አስታውቀዋል::

የባሕልና ስፖርት ሚኒስቴር ሚኒስትር ሻዊት ሻንካ እንደገለፁት፣ በዚህ ዓመት ከስፖርት ዲፕሎማሲ አኳያ ስኬታማ ሥራዎች ተሠርተዋል:: ካለፈው ዓመት ጀምሮ ኢትዮጵያ ትልልቅ ዓለም አቀፍና አሕጉር አቀፍ ውድድሮችን ማስተናገዷን በማስታወስም በዚሁ ጥቅምት ወር መጀመሪያ አንስቶ ኢትዮጵያ የአፍሪካ ጠረጴዛ ቴኒስ ሻምፒዮና እና ጠቅላላ ጉባኤን እያስተናገደች እንደምትገኝ ተናግረዋል:: በተጨማሪም የካፍ ጠቅላላ ጉባኤና የአፍሪካ ከ20 ዓመት በታች እጅ ኳስ ሻምፒዮናንም ለማስተናገድ ዝግጅቶች መጠናቀቃቸውን አክለዋል::

እንደ ሚኒስትሯ ማብራሪያ፣ ስፖርታዊ ዝግጅቶቹ በኢትዮጵያ መካሄዳቸው በሀገር ገጽታ ግንባታና በኢኮኖሚ ረገድ የውጭ ምንዛሪ ለማመንጨት ትልቅ ሚና አላቸው:: ለዚህም ዝግጅቶቹን የተሳካ ለማድረግ በመንግሥት ከፍተኛ አመራሮች የሚመራና የቴክኒክ ባለሙያዎችን ያካተተ ዐቢይ ኮሚቴ ተቋቁሞ ሥራዎችን እያከናወነ ይገኛል:: የሚሠሩት ሥራዎች በልዩ ሁኔታ እየተገመገሙም ይገኛሉ:: በተለይም የካፍ ጠቅላላ ጉባኤን ስኬታማ ለማድረግ በጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት የሚመራና የተለያዩ ሚኒስትር መሥሪያ ቤቶች የተካተቱበት ኮሚቴ ተቋቁሞ እየተሠራ ይገኛል:: በተመሳሳይ የአፍሪካ ከ20 ዓመት በታች እጅ ኳስ ሻምፒዮናን የተሳካ ለማድረግ ከሚኒስትር መሥሪያ ቤቱና ብሔራዊ ፌዴሬሽኑ የተውጣጣ ኮሚቴ ተዋቅሮ አስፈላጊው ዝግጅት እየተደረገ ነው::

በካፍ ጠቅላላ ጉባኤ ለመታደም ከ400 በላይ እንግዶች የሚመጡ ሲሆን ከፊፋና ከሌሎች አሕጉራት ኮንፌዴሬሽኖችም እንግዶች ተጋብዘዋል:: እንግዶቹ ከሀገራቸው ለጉባኤው ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡም የቪዛ ወጪ ከክፍያ ነፃ የተደረገ ሲሆን፣ ሥራዎችም በተቋቋመው ኮሚቴ እየተገመገሙ ነው::

የቴክኒክ ቡድኑ ሥራውን ቀደም ብሎ በመጀመሩ እንግዶቹ ነገና ከነገ በስቲያ ወደ አዲስ አበባ እንደሚገቡ ይጠበቃል:: ከዋናው የካፍ ጉባኤ አስቀድሞ እሁድ ቀኑ ሙሉ እና ሰኞ ጠዋት የየዞኑ ኮንፌዴሬሽኖች ስብሰባዎች በተናጠል ከካፍ ፕሬዚዳንት ፓትሪስ ሙሴፔ ጋር ይካሄዳሉ:: በመቀጠልም ሰኞ ከ4፡00 ሰዓት ጀምሮ እስከ ቀን 7፡00 ሰዓት የካፍ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ስብሰባ ከተደረገ በኋላ በተሳታፊዎች መካከል የወዳጅነት ጨዋታ በአዲስ አበባ ስታዲየም ይደረጋል::

ማክሰኞ ከ4፡00 ሰዓት እስከ 7፡00 ሰዓት ድረስ ዋናው የ46ኛው የካፍ ጠቅላላ ጉበኤ የሚካሄድ ሲሆን፣ ከተጠናቀቀ በኋላም የካፍ ፕሬዚዳንት ፓትሪስ ሙሴፔ ለመገኛ ብዙኃን መግለጫ የሚሰጡ ይሆናል::


## የጨረታ ማስታወቂያ

የጋሞ ዞን ፋይናንስ መምሪያ በ2017 በጀት ዓመት ግዥ 1-የፅ/መሣሪያ 2- ኤሌክትሮኒክስ 3-ፈርኒቸር 4- ጽዳት ዕቃዎች 6-የሞተር ሳይክል ጎማ 7- ሞተር ሳይክል 8- ፖሊቲን ቲዩብ በጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል፡፡

ስለሆነም በጨረታው በመሳተፍ የሚትፈልጉ ተጫራቾች ከዚህ በታች በተገለጸው መሠረት ቀርበው መወዳደር ይችላሉ::

1. በዘርፉ ህጋዊ የንግድ ፍቃድ ያላቸውና ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ፣
2. የዘመኑ ግብር የከፈሉበትን ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉና፤ የግብር ከፋይነት መለያ ቁጥር ያላቸው፡፡
3 . የተጨማሪ እሴት ታክስ /ቫት/ ከፋይ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ፣
4. የአቅራቢዎች የምዝገባ ምስክር ወረቀት ኦን ላይን ያላቸው፡፡
5. ተጫራቾች በጨረታው በመሳተፍ ከላይ በተራ ቁጥር 1-4 የተጠቀሱትን ማስረጃዎች ፎቶ ኮፒ ከመጫረቻ ሰነዶች ጋር አያይዘው ማቅረብ አለባቸው፡፡
6 .ተጫራቾች ዝርዝር የመጫረቻ ሰነድ ጋዜጣው አየር ላይ ከዋለበት እስከ 15 ባሉት ቀናት ብር 200 / ሁለት መቶ ብር/ በመክፈል ከጋሞ ዞን ፋይናንስ መምሪያ ቢሮ ቁጥር 5 መውሰድ ይችላሉ፡፡
7 .ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና እያንዳንዱ ሎት ብር 20,000 /ሃያ ሺህ ብር/ በባንክ በተረጋገጠ የክፍያ ትዕዛዝ /CPO/ ማስያዝ አለባቸው፡፡
8.ማንኛውም ተጫራች የጨረታ ሰነዱን በማዘጋጀት በፖስታ በጥንቃቄ በማሸግ የሚወዳደሩበትን ዓይነት በፖስታው ላይ በመለየት በግዥና/ን/አስ/ ዳይሬክቶሬት ቢሮ ቁጥር 5 በተዘጋጀው ሳጥን ማስታወቂያው በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ 16ኛው ቀን እስከ 3:30 ሰዓት ድረስ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡
9. ጨረታው ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ማስታወቂያው በጋዜጣ ከወጣበት በ16ኛው ቀን በ3:30 ታሽጎ በዕለቱ 4፡00 ሰዓት ቢሮ ቁጥር 5 ይከፈታል፡፡
10. ማንኛውም ተጫራች ያሸነፈበትን ዕቃ ያለተጨማሪ ወጪ እስከ ቢሮአችን በማምጣት የማስረከብ ኃላፊነት አለበት፡
11.የጨረታ መክፈቻ በበዓላት ወይም በሥራ ቀን ካልሆነ በሚቀጥለው የሥራ ቀን ይሆናል፡፡
12. መ/ቤቱ የተሻለ ዘዴ ካገኘ ጨረታውን በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
13. ስለጨረታው ዝርዝር መረጃ ከፈለጉ ቢሮ ቁጥር 5 በአካል በመቅረብ ወይም በስልክ ቁጥር- 0468813338/ በመደወል መረጃዎችን ማግኘት ይችላሉ፡፡

**በደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግሥት የጋሞ ዞን ፋይናንስ መምሪያ**
**አርባምንጭ**



## የደረሰኝ መጥፋት ማስታወቂያ

በአዲስ አበባ ከተማ ቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 04 የቤት ቁጥር038/07-ለ ግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) 0024817930 የሚታወቀው መርሃዊት ኪዳነ ሐድጉ በግብር/ታክስ ከፋይነት ከተመዘገብኩበት አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች የቦሌ ክፍለ ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት የህትመት ፍቃድ በማግኘት የተጨማሪ እሴት ታክስ/ቫት የእጅ በእጅ ሽያጭ ደረሰኝ ከቁጥር 001 እስከ 0050 ያልተሰራበት ስለጠፋብኝ በማንኛውም አካል እጅ ውስጥ ገብተው ወንጀል እንዳይሰራበት እና የጠፋ መሆኑ የሶስተኛ ወገን እንዲያውቀው ይህ ማስታወቂያ እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡ ይሁንና ከደረሰኙ ውስጥ ተሰርቶበት ያገኘ ወይም ከድርጅቱ ግዥ በማከናወን ክፍያ ለመፈፀም በማስረጃነት የተቀበለ ማንኛውም ሰው ከላይ ለተጠቀሰው በግብር/ታክስ ከፋይነት ለተመዘገቡበት አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች የቦሌ ክፍለ ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ወይም በአቅራቢያ የሚገኝ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት በማሳወቅ በግብር/ታክስ አሰባሰብ ላይ ትብብር እንዲያደርግ አስታውቃለሁ፡፡

**የግብር ከፋይ ስም፡ መርሃዊት ኪዳነ ሐድጉ**



## የደረሰኝ መጥፋት ማስታወቂያ

በአዲስ አበባ ከተማ ቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 የቤት ቁጥር 313/10 ግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) 0083378941 የሚታወቀው አርላንዳ ሂል ላውንጅ ኃላ/የተ/የግ/ማህበር በግብር/ታክስ ከፋይነት ከተመዘገብኩበት ለገቢዎች ሚኒስቴር ምስራቅ አዲስ አበባ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት የህትመት ፍቃድ በማግኘት የእጅ በእጅ የተሰራበት ከቁጥር 002451 እስከ 002458 እና ያልተሰራበት 002459 እስከ 002500 ስለጠፋብኝ በማንኛውም አካል እጅ ውስጥ ገብተው ወንጀል እንዳይሰራበት እና የጠፋ መሆኑ የሶስተኛ ወገን እንዲያውቀው ይህ ማስታወቂያ እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡ ይሁንና ከደረሰኙ ውስጥ ተሰርቶበት ያገኘ ወይም ከድርጅቱ ግዥ በማከናወን ክፍያ ለመፈፀም በማስረጃነት የተቀበለ ማንኛውም ሰው ከላይ ለተጠቀሰው በግብር/ታክስ ከፋይነት ለተመዘገቡበት ለገቢዎች ሚኒስቴር ምስራቅ አዲስ አበባ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ወይም በአቅራቢያ የሚገኝ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት በማሳወቅ በግብር/ታክስ አሰባሰብ ላይ ትብብር እንዲያደርግ አስታውቃለሁ፡፡

**የግብር ከፋይ ስም፡ አርላንዳ ሂል ላውንጅ ኃላ/የተ/የግ/ማህበር**